በፎሊክ አሲድ እጥረት የሚከሰት “ የነርቭ ዘንግ ክፍተት” ን ለመከላከል
ገጽ 10

የትዳር አጋርን ነፍስ የነጠቀው የንዋይ ጥማት
ገጽ 12

ከህሊና ጋር ትንቅንቅ
ገጽ 14

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 124 ጥር 4 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ

## የሕዝቦችን ነጻነት ለማረጋገጥ ቀዳሚውን የዲፕሎማሲ ሚና እየተወጣች ነው

### - የዲፕሎማሲ ሳምንትን መነሻ ያደረገ የፓናል ውይይት ተካሂዷል

አዲሱ ገረመው


አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ የሕዝቦችን ነጻነት ለማረጋገጥና ግጭቶችን በሰላም ለመፍታት ቀዳሚውን የዲፕሎማሲ ሚና እየተወጣች ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ተናገሩ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ያዘጋጀው “ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም ያዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት አካል የሆነው የፓናል ውይይት ትናንት ተካሂዷል፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ የትውልድ፣ የትምህርትና የእውቀት ሽግግርን ለመሙላት በዲፕሎማሲ መስክ ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ግዛት የሕዝቦችን ነጻነት ለማረጋገጥ ከሚደረጉ ትግሎች ቀዳሚውን ሚና በመጫወት በአህጉር ደረጃም ግጭቶችን በሰላም ለመፍታት በአብነት የሚጠቀስ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን እየሠራች መሆኗንም ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ




## ብሔራዊ ጥቅም

### ማስከበር ላይ ያተኮረው ዲፕሎማሲ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ ፡- ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር ላይ ያተኮረው የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በተለያዩ መንገዶች ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተገለጸ።

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውና

ብሔራዊ ጥቅም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

## “የማዕድን ዘርፉ ለኢኮኖሚው እድገት እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው”

### -ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ የማዕድን ሚኒስትር

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ሀብት ቢኖራትም ዘርፉ ለኢኮኖሚው እያበረከተ ያለው

—የማዕድን ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “የኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ ፍትሐዊ ሂደትንና የታሪክ መነሾን የተከተለ ነው”

### - የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪዎች

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ ፍትሐዊና ሕጋዊ ማዕቀፍን የተከተለ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና የብሔራዊ ደህንነት አማካዎች ገለጹ።

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም ያዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት አካል የሆነው የፓናል ውይይት ላይ አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ስለወደብ ጉዳይ ገለጻ አድርገዋል።

ኢትዮጵያውያን የወደብ ጥያቄ መሻታችን የቅኝ ግዛት ታሪክን የምንታገልበት ሂደት አካል ነው ያሉት አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ፤ ጥያቄው ፍትሐዊና ታሪካዊ መነሻ ያለው መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛትን ስትታገል ዋጋ መክፈሏን አስታውሰው፤ የወደብ ጥያቄ መሻታችን በተመሳሳይ ቅኝ

“የኢትዮጵያ የወደብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አምባሳደር ታዬ አስቀስላሴ


አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን









አቶ ብሩክ ሀብቴ

# ብሔራዊ የደረጃዎች

## ምክር ቤት ጉባኤ 385 ደረጃዎችን አጸደቀ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት ጉባኤ ታኅሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 38ኛ መደበኛ ስብሰባው በ6 ዘርፎችና በ24 የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የቀረቡለትን 385 ደረጃዎች መርምሮ አጽድቋል።

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ብሩክ ሀብቴ እንደተናገሩት፤ የፀደቁት ደረጃዎች በ6 ዘርፎች 233 አዲስ እና 132 የተከለሱ ደረጃዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ ከፀደቁት ደረጃዎች ውስጥም 12ቱ አስገዳጅ ደረጃዎች መሆናቸውን አብራርተዋል።

የጸደቁደረጃዎችምበኤሌክትሮሜካኒካል፣ በጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ፣ በአካባቢ ጤናና ደህንነት ፣ በግንባታና ሲቪል ምህንድስና ፣ በኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች፤ በግብርናና ምግብ ዘርፍ መሆናቸውን ተናግረዋል።

12 የሚሆኑ አስገዳጅ ደረጃዎች ውስጥም ከኤሌክትሪክ ቁሳቁሶችና ኃይል አስተላላፊዎች፤ ከአስፈላጊ መድኃኒቶች ፣ ከህክምና ሳይንስ እና የጤና ጥበቃ ተቋማት እና ከቀለምና ቫርኒሽ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን አክለዋል።

እነዚህ የጸደቁ ደረጃዎች ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት ከጸደቁና ሥራ ላይ ከዋሉ ደረጃዎች በተጨማሪ የዝግጅት ሂደታቸው ፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ተገምግሞ ከጥራት፤ የሰውና የእንስሳት ደህንነት ከአካባቢ ጥበቃ እና ንግድን ከማቀላጠፍ አኳያ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ይታመናልም ነው ያሉት።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ የጸደቁት ደረጃዎች የምርቶችና የቁሳቁሶች ተያያዥነት ያላቸው ነገሮችን ጥራት ከማሻሻልና ከማረጋገጥ አንጻር ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪንና የተወዳዳሪነትን አቅም ለማጎልበት እንደሚረዱ ይጠበቃል። ለምርምርና ለዕውቀት ሽግግር በመሳሪያነት በማገልገልም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ግብአት ይሆናሉ።

በተጨማሪም ደረጃዎቹ ክህሎትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ያበረክታሉ፤ ከኀብረተሰቡ ጤናና ደህንነት ፣ ከአካባቢ ጥበቃ እና የሸማቾችን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ተቆጣጣሪ አካላት የክትትልና ቁጥጥር እና ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉም ብለዋል።

# በየዓመቱ ለግብር ከፋዮች የሚሰጠው እውቅና የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን አጠናክሯል

## - የላቁ ግብር ከፋዮች ነገ እውቅና ይሰጣቸዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በየዓመቱ ለላቁ ግብር ከፋዮች የሚሰጠው እውቅና የመዲናዋን የገቢ አሰባሰብ ሂደት ማጠናከሩን የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ። ነገ የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ 562 የመዲናዋ ግብር ከፋዮች እውቅናና ሽልማት እንደሚሰጥም ገልጿል።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የህግ ተገዢነት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኮማንደር አህመድ መሀመድ የዕውቅና መድረኩን በሚመለከት በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ ቢሮው በየዓመቱ ግብር ከፋዮቹን በህግ ተገዢነታቸው ጥሩ የሆኑና ታማኝ እና በገቢ አከፋፈላቸው የተሻሉ የሚባሉትን በማወዳደርና በመለየት እውቅናና ሽልማት ሲሰጥ ቆይቷል።

ቢሮው በዘንድሮ ዓመትም በተመሳሳይ መልኩ “ግብር ለሀገር ክብር” በሚል መሪ ቃል በ2015 ዓመተ ምህረት የግብር ማሳወቂያ ወቅት ለህግ ተገዢ የሆኑና የላቀ ገቢ አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግብር ከፋዮች እውቅና ይሰጣል ያሉት ኮማንደር አህመድ፤ ይህም የተሻለና ለህግ ተገዢ የሆነ ታማኝ ግብር ከፋዮች ማፍራት እንዲቻል፣ ተሸላሚ ግብር ከፋዮች ለሌሎች አርዓያ እንዲሆኑ እና የመዲናዋን የገቢ አሰባሰብ ሂደት እንዲጠናከር ማድረጉን ተናግረዋል።

እንደ ኮማንደር አህመድ ገለፃ፤ የሽልማትና እውቅና መርህ ግብሩ ዋና ዓላማ ለሀገር ልማት የሚሰሩ ታማኝ ግብር ከፋዮችን ለማበረታታት እና በወቅቱ ግብር እንዲከፈል ለማድረግ ነው። ይህም በግብር ከፋዮች መካከል አወንታዊ ውድድር እንዲፈጠር ትልቅ ሚናም ይኖረዋል። ይህም የገቢ አሰባሰብን እና የቢሮ የአሰራር ሥርዓት እንዲሻሻል አድርጓል።



ኮማንደር አህመድ መሀመድ

በ2015 በጀት ዓመት የላቀ ግብር የከፈሉ እና ተወዳድረው አሸናፊ ለሆኑ 562 የመዲናዋ ግብር ከፋዮች የፊታችን እሁድ እውቅናና ሽልማት እንደሚሰጣቸው የገለጹት ኮማንደር አህመድ፤ ቢሮው በየዓመቱ የእውቅና መርሀ ግብር ማድረጉ የነጋዴዎች ቁጥር እንዲጨምር፣ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱ ዘመናዊ እንዲሆን እና የተሻለ እቅድ ማቀድ እንዲቻል አድርጓል ብለዋል።

በ2015 ዓመተ ምህረት የላቀ ግብር ለከፈሉ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በመጪው እሁድ እውቅና ይሰጣል። ይህም ሌሎች ግብር ከፋዮች በ2016 ዓመተ ምህረት ተሸላሚ ለመሆን እንዲነሳሱ ያደርጋል። ይህ መድረክ ሲዘጋጅ በቢሮው ለአራተኛ ጊዜ ነው።

# በመዲናዋ በከተማ ግብርና ስድስት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ባለፉት አምስት ወራት ዉስጥ በከተማ ግብርና ስድስት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የስራ እድል መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ። በሚቀጥሉት ሶስት ወራት ውስጥ በንቅናቄ ለአስር ሺህ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ውጥን መያዙ ተገልጿል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ፋሩቅ ጀማል ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ግብርና ዘርፍ ለ23ሺህ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆን፤ ባለፉት አምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለ5ሺህ 981 ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል።

የስራ ዕድሉ የተፈጠረው በእንስሳት እርባታ፣ በጓሮ አትክልት እና ሌሎች የግብርና ስራዎች ላይ ሲሆን፤ በክህሎት መር፣ አርሶ አደርን መልሶ በማቋቋምና በመደበኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ፋሩቅ ገለጻ፤ የስራና ክህሎት ቢሮ በሶስት ወራት ውስጥ 36ሺህ ዜጎችን በተለያዩ መስኮች ወደስራ ለማስገባት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ በንቅናቄ አስር ሺህ ወጣቶችና ሴቶች በማህበር ተደራጅተው በከተማ ግብርና የስራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ይሆናል።

ይህም የሚሆነው በዶሮ፣ በወተት፣ ከብት ማደለብ፣ በአትክልት፣ በችግኝ ማፍላትና በሌሎች የስራ መስኮች ዜጎች በምርጫቸው ወደቴክኒክና ሞያ ኮሌጆች በመግባት የክህሎት መር ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ወደስራ እንደሚገቡ ጠቁመዋል።

በዚህም ለዜጎቹ የመስሪያ ቦታ፣ የገበያ ትስስርና በስኬት ባንክ አማካኝነት የገንዘብ ብድር አገልግሎት የሚመቻች ሲሆን፤ በአዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክስዮን ማህበር በኩል ደግሞ የተለያዩ ማሽኖችን በብድር እንዲያገኙ እንደሚደረግ ምክትል ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።



አቶ ፋሩቅ ጀማል

የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽንም ለዜጎቹ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን ያደርጋል ነው ያሉት።

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ልየታ ሲደረግም ዜጎቹ የአዲስ አበባ ከተማ መታወቂያ የሌላቸው ከሆነ በሚኖሩበት አካባቢ የብሎክ ነዋሪነታቸውና ስራ አጥነታቸው የሚረጋገጥ ይሆናል፤ የስራ ዕድሉ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ መስፈርቱን በማሟላት ተደራጅቶ በመምጣት እድሉን ሊጠቀም እንደሚገባ አውስተዋል።

ዝቅ ተብሎ ካልተሰራ ድህነትን ማሸነፍ አይቻልም ያሉት አቶ ፋሩቅ፤ የከተማ ግብርና አዋጭ በመሆኑ በተለይም ወጣቶች በዘርፉ በመሰማራትና ጠንክሮ በመስራት በፍጥነት ወደኢንቨስትመንት የሚሸጋገሩበት እድሉ ስላላቸው ወደዘርፉ እንዲገቡና ከገቡም ጠንክረው ሊሰሩ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# 50 ሚሊዮን ዜጎችን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዳማ፡- ወደ 50 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገሪቱ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ተጠቃሚ ባለመሆናቸው በእያንዳንዱ ቤት ተደራሽ ለማድረግ እየሠራን ነው ሲል ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን የንጹህ ውሃ መጠጥና የኤሌክትሪክ ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ ባለው የዋተር ፎር ላይፍ ፕላስ ፕሮጀክት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት በትናንትናው ዕለት ቀርቧል።

በክንዋኔ ኦዲቱ ሪፖርት ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ እንደገለጹት፤ ወደ 50 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገሪቱ ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽ አልሆነላቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ ለነዚህ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው።

ማኅበረሰቡን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ 71 ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ወደ 50 ሚሊዮን የሚደርሱ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ አይደሉም ብለዋል።

ንጹህ የመጠጥ ውሃን በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ተቋማትና በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ቤት ተደራሽ ለማድረግ በስፋት እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

"መንግሥት በሁሉም የልማት ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው፤ እየተሠራ ካሉትም የልማት ሥራዎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ይገኝበታል" ሲሉም ሚኒስትሩ አብራርተዋል።


ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ

ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለሀገሪቱ ዜጎች በእያንዳንዳቸው ቤት ተደራሽ ለማድረግ በጀት ተበጅቶ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በዘርፉ የማሳተፍ ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ተቋማት ተገንብተው ለማኅበረሰብ አገልግሎት ክፍት ሲሆኑ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽ ሊሆንላቸው ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህንንም ለማድረግ በትምህርት ቤቶችና በጤና ተቋማት ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ተቋሙ ለማኅበረሰቡ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ ፕሮጀክቶችን የመገንባትና ነባሮችን የማደስ ሥራ እየሠራ ነው ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ፤ ዜጎችን የንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተጠቃሚ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የመጠጥ ውሃን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ስምምነት የሀገሪቱን ፖሊሲዎችንና ሉዓላዊነት የጠበቀ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ዜጎችን የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ የሚገጥሙ ተግዳሮቶች ይኖራሉ፤ ተግዳሮቶችን በማጤንና በመፍታት ማኅበረሰቡን የመጠጥ ውሃ ተደራሽ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ ፕሮጀክቶችን የመገንባት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም አመላክተዋል።

የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ አበራ እንዳሻው በበኩላቸው፤ ለማኅበረሰቡ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ 71 ሚሊዮን ዜጎችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በጦርነት የወደሙትን ፕሮጀክቶችንና ተጠቃሚዎችን ሳያካትት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ለማኅበረሰቡ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ በውሃ መሰረተ ልማቶች ላይ ጥናት ይደረጋል፤ የግንባታ ሥራዎችን የማስፋፋት፣ የመቆጣጠርና የመከታተል ሥራም ይከናወናል ሲሉ ገልጸዋል።

ተቋሙ የሀገሪቱን ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ ያለውን ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም አመላክተዋል።


ሙፍሪሃት ካሚል

# ከሁለት ሺህ በላይ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የሥራ አጥ ምዝገባ እያካሄዱ ነው

## - 20 ሚሊዮን ዜጎች ለመመዝገብ ታቅዶ 500 ሺህ ብቻ ተመዝግበዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁለት ሺህ 200 ገደማ የሚሆኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የሥራ አጥ ምዝገባ እያካሄዱ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ። በዚህ ዓመት ለመመዝገብ በዕቅድ ከተያዘው 20 ሚሊዮን ዜጎች ውስጥ በሥራ አጥነት የተመዘገቡት 500 ሺህ ብቻ መሆናቸው ተነግሯል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሙፍሪሃት ካሚል እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁለት ሺህ 200 ገደማ የሚሆኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የሥራ አጥ ምዝገባ እያካሄዱ ነው። ማዕከላቱ በትንሹ 53 ዓይነት አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ተደርገው የተሰናዱ ናቸው።

አገልግሎቱ ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ያሉት ሚኒስትሯ፤ የኢትዮጵያ የገበያ መረጃ ሥርዓትን በቴክኖሎጂ መደገፍ የሚችል መሆኑን አንስተዋል።

ሚኒስትሯ ለአብነት እንዳነሱት፤ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ ሲገቡ ይመዘገባሉ። የተደራጁ ወጣቶችም የአሻራና ሌሎች መረጃዎችን ስለሚሰጡ ደግመው መመዝገብ የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ማዕከላቱ ተመዝጋቢዎች ሥራ ሲቀይሩ መረጃዎችን በወቅቱ በመቀበል ማስተካከል የሚቻልባቸው ናቸው።

ይህ የአንድ መስኮት አገልግሎት በተለይ ከብድር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተግዳሮቶችን ማቃለል እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ በዘርፉ ተደጋጋሚ ብድር በመውሰድ የሌሎችን ዕድል የሚዘጉትን እና የሚያጭበረብሩትን ለመከላከል እንደሚረዳ ጠቁመዋል።

ከብድር አመላለስ ጋር በተያያዘ በቂ መረጃ የሚያዝበት የአንድ ማዕከል ሥርዓት በመሆኑ የሚሠሩትን ለማበረታታት ያግዛል። ለአምስት ወራት ውስጥ የተመዘገቡት 500 ሺህ ብቻ መሆናቸውን ሚኒስትሯ ተናግረዋል።

የዚህ ማዕከል ዋና አገልግሎት ሁሉም ዜጋ የት ቦታ ሥራ እንዳለው እና እንደሌለው የሚያሳይ ነው፤ በመሆኑም በዝምድና እና በሽርክና የሚፈጠሩ ያልተገቡ ሥራዎችን ለማስቀረት ይረዳል ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህ ዘርፍ ፍትሐዊ አገልግሎት ይስፈን፤ የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት ይኑር ከተባለ ተረባርቦ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል።

ዕድሜያቸው ለሥራ የደረሱ ዜጎች ሁሉ በዚህ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መመዝገብ እንደሚችሉ የገለጹት ሚኒስትሯ፤ የምዝገባ ሥራው ቀላል በመሆኑ ዜጎች በተንቀሳቃሽ ሥልክ ምዝገባውን አከናውነው አሻራውን ወደማዕከሉ በመሄድ መስጠት ይችላሉ ብለዋል።



# የጥምቀት በዓል ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የፀጥታ ኃይሉ በቅንጅት ይሠራል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- መጪው የጥምቀት በዓል ፍጹም ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የጸጥታ ኃይሉ በቅንጅት እንደሚሠራ ተገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ከማዕከል እስከ ወረዳ ከሚገኙ አመራሮች ጋር የጥምቀት በዓል አከባበርን አስመልክቶ በትናንትናው እለት ውይይት አድርገዋል።

በውይይቱ የዘንድሮው የጥምቀት በዓል ፍፁም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የፀጥታ ኃይሉ በንቃት ሊሠራ እንደሚገባ ተጠቁሟል።

የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊዋ ወ/ሮ ሊዲያ ግርማ የፀጥታ ሥራ ወቅታዊና ተለዋዋጭ በመሆኑ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ቅንጅትና የመረጃ ቅብብሎሽ በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሁሉም አመራር የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በተለይ ታቦታት በሚያድሩባቸው፣ ጥምቀት በሚካሄድባቸውና በሌሎችም የከተማዋ አካባቢዎች የተቀናጀና የነቃ ጥበቃ ለማድረግ መላው የፀጥታ አካል ዝግጁ ሊሆን እንደሚገባ ያሳሰቡት ኃላፊዋ፣ በዓሉ በሰላም እንዲከበር ከማድረግ አንጻር፣ በየደረጃው ያለው የሰላምና ፀጥታ አደረጃጀት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ሲሠሩ መቆየታቸውን አንስተዋል።

ከዚህ ቀደም በነበረ ልምድ ሃይማኖታዊ በዓሉን በሰላምና በደስታ ከማክበር ይልቅ ፖለቲካዊ የማድረግ፣ የፀጥታ ኃይሉን የመተንኮስና ሌሎችንም ወንጀሎች የመፈጸም ሁኔታዎች እንደነበሩ አስታውሰው፤ የፀጥታ ኃይሉ ዝግጅት ያለፉ ልምዶችን ታሳቢ ያደረገ መሆን እንደሚገባው አመላክተዋል።

አዲስ አበባን የዲፕሎማቲክ ከተማ ለማድረግ እየተሰሩ ባሉ ሥራዎች በርካታ ውጤቶች መገኘታቸውን የጠቀሱት ኃላፊዋ፣ የሀገራችንንና የከተማዋን ስኬት የማይፈልጉ አካላት የአደባባይ በዓሉን አጋጣሚ አድርገው የመጠቀም ፍላጎት ስለሚኖራቸው የፀጥታ ኃይሉ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ለከተማዋ ሰላም በንቃት እንዲቆም አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በበኩላቸው፤ የዘንድሮውን የጥምቀት በዓል ሠላማዊ በሆነ ሁኔታ ለማክበር ያለፈውን ዓመት እንዴት ነበር ያከበርነው የሚለውን ማስታወስ እንደሚያሻ አንስተዋል።

ባለፈው ዓመት የገጠሙንና ያለፍንባቸውን መንገዶች፣ ችግሮችን ከስሩ የፈታንባቸውን አሰራሮች በዘንድሮውም የጥምቀት በዓል በተሻለ መልኩ በመድገም በትኩረት መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የጥምቀት በዓል በዓለም አቀፉ የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በቅርስነት የተመዘገ ትልቅ የአደባባይ በዓል እንደመሆኑ ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ጠብቆ እንዲከበርና በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፀጥታ ኃይሉ ጎን የበዓሉ ባለቤት የሆነው ሕዝብም ለሰላሙ ዘብ መቆም እንዳለበት በመድረኩ ተገልጿል።

ዜና

# ብሔራዊ ጥቅም...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የዲፕሎማሲ ሳምንት አካል የሆነው የፓናል ውይይት ትናንት ተካሂዷል።

በፓናል ውይይቱ ሁለተኛ ምዕራፍ በዲፕሎማሲው መንገድ ያገለገሉት አምባሳደር ተሾመ ቶጋ፣ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና፣ በዲፕሎማትነት ያገለገሉት አምባሳደር ማህሙድ ድሪር፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን የመወያያ ጽሑፍ አቅርበዋል።

አምባሳደር ተሾመ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በ2010 ዓ.ም ሀገራዊ ለውጥን ተከትሎ የተሠሩ ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብሩ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ለአጋሮቻችን ተስፋ ሰጥቷል። ለውጡን ተከትሎ የተለያዩ የሕግና የውጭ ግንኙነት ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ በዚህም በርካታ የዲፕሎማሲ ድሎች ተመዝግበዋል ብለዋል።

"አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሔ" የሚለው የኢትዮጵያ መርህ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን አመላክተው፤ በቀጣይም የዓለምን ተለዋዋጭ ሁኔታ ያገናዘበና ብሄራዊ ጥቅምን ያስከበረ ሚናዋን አጠናክራ መቀጠል እንደሚገባት ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና በበኩላቸው፤ ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የዲጂታል ዲፕሎማሲን በስፋት እንድንጠቀም የሚያስገድድ ዘመን ላይ ነን ብለዋል።

ለዲጂታል ዲፕሎማሲው ውጤታማ ለመሆን የማኅበራዊ ሚዲያው ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ያስፈልጋል ያሉት ኢንጂነር ወርቁ፤ በተለያዩ ዓለማት ከሚገኙ 52 የኢትዮጵያ ኤምባሲና ቆንስላዎች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት 50ዎቹ የፌስቡክ ገጽ እንዳላቸውና 47ቱ ደግሞ የትዊተር ገጽ ኖሯቸው መረጃ እያስተላለፉ መሆኑን አስታውቀዋል።

አብዛኛዎቹ የማኅበራዊ ገጾች ግን ማረጋገጫ ያልተሰጣቸው ወይም "ቬሪፋይድ" ያልሆኑ ናቸው ሲሉ ኢንጂነር ወርቁ ተናግረዋል። በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ አምባሳደሮቻችን ፌስቡክና የትዊተር ገጾቻቸውን "ቬሪፋይድ" በማድረግ መረጃዎችን ማስተላለፍ እንዳለባቸው አመላክተዋል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የጂጂታል ዲፕሎማሲ ጅማሮው መልካም ቢሆንም ብሔራዊ ጥቅምን ከማስጠበቅ አኳያ ይበልጥ ማደግ አለበት ብለዋል።

ለብዙ ዓመታት በዲፕሎማትነት ያገለገሉት አምባሳደር ማህሙድ ድሪር በበኩላቸው፤ በርካታ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን በተቀናጀ መንገድ ኢትዮጵያን የማጠልሸት ዘመቻና የተለያዩ ሀገራትን ጫና በምን ተቋቁሞ ማለፍ በራሱ ድል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ከሰሜኑ ጦርነት ባለፈ በዓባይ ግድብ ውይይት ላይ ዶናልድ ትራምፕ ግድቡን ግብጾች መምታት ይችላሉ ብለው በአሜሪካ የተጻፈው ሰነድ ላይ እንድትፈርም ያስፈራሩበትን መንገድ አስታውሰው፤ ጫናውን አልፈን ዓላማችንን ማሳካት የቻልንበት ሂደት ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር መሆኗን ያሳያል ብለዋል።

የብሪክስ አባልነት ውስጥ ከገባን በኋላ ያሉ ጉዳዮች፣ ኢጋድን እንዴት ማጠናከር እንችላለን የሚሉ ጉዳዮች ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚረዱ በመሆናቸው ቀሪ የቤት ሥራዎች ናቸው ሲሉ ጠቁመዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ፤ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማግኘት እንደምትሠራና የባህር በር ማግኘቷ ለጋራ ተጠቃሚነት ነው የሚለው አዎንታዊ ትርክት ተቀባይነት እያገኘ መሆኑን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ አማራጭ የባህር በር ለማግኘት እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ካላት ፍላጐት አንጻር መሆኑ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ላይ መቀመጡን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት እድል ያላት በሰሜኑ በኩል ብቻ አለመሆኑንና በዙሪያዋ ካሉ ሁሉ የመጠቀም አቅም እንዳላት ያሳያል ብለዋል።

# "የኢትዮጵያ የወደብ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ግዛትን የምንታገልበት አካል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

"የመገፋትና የመበደል ማዕበል ሲነሳ ታሪክና ተስፋ ይነሳል፤ የኢትዮጵያን የወደብ ጥያቄን በዚህ አግባብ ነው የማየው" ብለዋል። "የምንሰራው የኢትዮጵያን ኃይል መገንባት ነው። ዓለም የባህታውያን ስብስብ አይደለም። ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የምናከናውናቸው የራሳችን ስራዎች አሉ" ሲሉም ተናግረዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘቷ ለጋራ ተጠቃሚነት ነው የሚለው አዎንታዊ ትርክት ተቀባይነት እያገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

አምባሳደር ሬድዋን በመድረኩ ባደረጉት ንግግር፣ ኢትዮጵያ አማራጭ የባህር በር ለማግኘት እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ካላት ፍላጐት አንጻር መሆኑን በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ላይ መቀመጡን አስረድተዋል።

በወደብ ጥያቄ ጉዳይ ላይ አልተገመትንም ፤ ሌሎች አካላት ስለወደብ ጦርነት ውስጥ ይገባሉ ብሎ ሲገምት እኛ ግን በሰላማዊ መንገድ ነው የመጣነው ብለዋል።

ለምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በበቂ ሁኔታ አስረድተናል። ዩጋንዳና ኬንያን ጨምሮ የተለያዩ የኢጋድ አባል ሀገራት ጋር ቀርበናል። ታንዛኒያና ጂቡቲ ስለጉዳዩ በአግባቡ ያውቃሉ፤ ጉዳዩን የኢጋድ አጀንዳ እናደርገዋለን በሚል የገለጹ ሀገራት አጋር ነበሩ ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር ሬድዋን ገለጻ፤ ጂቡቲ ስለወደብ ድርድሩ ሂደት ጭምር በአግባቡ ታውቅ ነበር። አሜሪካ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ እንግሊዝ፣ ዩናይትድ አረብ ኤምሬቶችም በተመሳሳይ ያውቃሉ። የማያውቁት የሶማሊላንድን የሀገርነት ዕውቅና እና የሼር ኢኮኖሚ ጉዳይ ነው።

ለሚመለከተው መንግሥት ካስረዳን በኋላ የራሳችንን ድርድር በማድረግ ነው እያስፈጸምን ያለነው ሲሉም አስረድተዋል።

የመንግሥት ፍላጐት በወረራና በጉልበት የባህር በር ማግኘት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድና በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑን በቅርቡ የተደረገው ስምምነት ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት እድል ያላት በሰሜኑ በኩል ብቻ አለመሆኑንና በዙሪያዋ ካሉ ሁሉ የመጠቀም አቅም እንዳላት ያሳያል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የባህር በር ማግኘት አለባት የሚለው አዎንታዊ አጀንዳ ሆኖ ብዙዎች እየደገፉት እንዳለም አምባሳደር ሬድዋን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፍላጐት ለራስ ዋስትናና ለጋራ ጥቅም እንደሆነ ጠቁመው፤ በዚህም ተያይዘን እንደግ የሚለው አዎንታዊ ምልከታ እየተንጸባረቀ ነው ብለዋል።

# ኢትዮጵያ በአፍሪካ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ነጻነታችንን አስከብረን ለመኖር በትምህርትና በሳይንስ እድገት ለማሳየት ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነት ለማድረግ የዲፕሎማሲ መንገዱን ከፍተናል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ በዲፕሎማሲው ረገድ ንቁ ተሳትፎ እንዳላት ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ሀገሪቷን በመሩ በሁሉም መንግሥታት ቅብብሎሽ የቀጠለ መሆኑን ጠቅሰው፤ የተዘጋጀው የፓናል ውይይት ያለፈውን ጉዞና ለወደፊቱ ምን ይጠበቃል የሚለውን ለማመላከት ትልቅ ግብዓት የተገኘበት መሆኑንም ተናግረዋል።

በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የዲፕሎማሲ ሳምንት በቴክኒክና በበሳል አመራር እንዲሳካ ላደረገው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ምስጋና አቅርበዋል።

በመድረኩ በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ላይ ያተኮረ የመወያያ ጽሁፍ ያቀረቡት አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካን የነጻነት እንቅስቃሴዎች በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካና በተለያዩ መስኮች ደግፋለች። የአፍሪካ ኅብረትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች ምስረታ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦም አበርክታለች። ይህም ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል ነው።

በሀገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከናወኑ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ዛሬ ላይ አንገታችንን ቀና አድርገን እንድንሄድ ያስቻሉን ናቸው ያሉት አምባሳደር ዲና፤ ኢትዮጵያ በዓለም ሰላም ጥበቃ ረገድ በኮሪያ፣ በላይቤሪያ፣ በሩዋንዳ፣ በሱማሊያና ሌሎች ሀገራት ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቷን ገልጸዋል። ይህንን ትልቅ ገድል ለዲፕሎማሲ ግንኙነት መጠቀም እንደሚገባም መክረዋል።

በፓናል ውይይቱ ረጅሙን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ታሪክ ያነሱት ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በበኩላቸው፤ በየክፍለ ዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች የተለያየ የዲፕሎማሲ ሥራ ቢኖራቸው በአፍሪካ ኅብረትና በዓለም አቀፍ ተቋማት ላይ ያከናወኑት ሥራ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ ያጎላ ነበር ብለዋል።

በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመንና በየጊዜው የነበሩ መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በነበሩ ጦርነቶችና መድረኮች ላይ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሚና በመጫወት የሀገራቸውን ሚና አጉልተዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ለ53 ዓመት በዲፕሎማትነት ያገለገሉት አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በዘመናት መካከል ብትፈተንም በዲፕሎማሲው የደረሱባትን ጫናዎች በውጤታማነት ያለፈች ሀገር ናት ሲሉ ተናግረዋል።

በጣሊያን ወረራ ወቅት በሊግ ኦፍ ኔሽን ብትፈተንም በኋላ ሊግ ኦፍ ኔሽን እንዲፈርስ ዋና ጉዳይ የሆነው የኢትዮጵያ መወረር ነው ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ ከዚያም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) መመስረቱንና፤ ኢትዮጵያ የተመድ 57ኛ አባል ሆና መፈረሟን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በእስራኤልና በአረብ ሀገራት ጉዳይ፤ እንዲሁም በኮሪያ ዘመቻ ወቅት በተመድ ጉባኤዎች ብትፈተንም በኮሪያ ጭምር ወታደሮቿን በመላክ ጉዳዩን በብቃት ተወጥታዋለች ሲሉም ገልጸዋል።

በአፍሪካ ኅብረት ምስረታ የካዛብላንካና የሞኖሮቪያን ቡድን በማግባባትና ቻርተሩ እንዲፈረም በማድረጉ ሂደት ከፍተኛ ጫና ቢኖርም በብልጠትና በዲፕሎማሲ ጥረት ውጤታማ ሆኖ ማለፉን ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ የኅብረቱ መቀመጫ እንዲሆን የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ነበር ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ በኋላም የኅብረቱን መቀመጫ ወደሌሎች ሀገራት ለመውሰድ ሰፊ ደባ ሲሰራ እንደነበርም ጠቁመዋል፤ ያም ሆኖ ግን በዕውቀትና በጥበብ አልፈነዋል ብለዋል።

በፓናል ውይይቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንን ጨምሮ፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ አንጋፋ ዲፕሎማቶችና ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆኑ የተለያዩ ሀገራት ሚሲዮኖች የተሳተፉ ሲሆን፤ በሁለትዮሽና በባለ ብዙ ወገን የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ጉዞ የተመለከቱ የተለያዩ ጽሑፎች በአንጋፋ አምባሳደሮችና ምሁራን ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

# "የማዕድን ዘርፉ ለኢኮኖሚው...

አስተዋጽኦ ዝቅተኛ መሆኑን የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ ገለጹ።

ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አስመልክተው ትናንት ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ የማዕድን ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚገባውን ያህል አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በትኩረት እየተሠራ ነው።

የማዕድ ዘርፍ ያልተጠቀምንበትና እንደ አዲስ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ምሰሶ ሆኖ የመጣ ስለሆነ ቀድሞ መሠራት የነበረባቸው ሥራዎች ጭምር አሁን ላይ እየተሠሩ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን መተካትና የሥራ እድል መፍጠር ዋንኛ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ተደርገው ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ብለዋል።

ዘርፉ የሚፈልገው ከፍተኛ ካፒታል፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ምርት ለማስገኘት የሚወስደው ጊዜ መርዘም በአጭር ጊዜ ውጤታማ ለማድረግ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አስታውሰው፤ በተጨማሪም የኮንትሮባንድ ንግድና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮችም ትልቅ እንቅፋት ፈጥረዋል ሲሉ አስረድተዋል።

የማዕድን ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ብዙ ተቋማትን ያቀፈ ብሔራዊ የማዕድን ካውንስል ተቋቁሟል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህም በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በቅንጅት ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነ አብራርተዋል።

ማዕድን ከራሱ አልፎ ሌሎች ዘርፎችንም ለማገዝ የሚችል አቅም ያለው መሆኑን የጠቆሙት ኢንጅነር ሀብታሙ፤ ኮንስትራክሽንን ጨምሮ ለሌሎችም ዘርፎች በግብዓትነት የሚያገለግሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን የማዳን ሥራ እየተሠራ ነው። በተጨማሪም የማዕድን ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር የሚያስገኙትን የውጭ ምንዛሪ መጨመርም ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከል የሚጠቀስ ነው ብለዋል።

ዘርፉ ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት በሰፋ ቁጥር የሚፈጥረው የሥራ እድል አብሮ እንደሚጨምር ገልጸው፤ በባህላዊ መንገድ በሚደረገው የማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተሠማርተው ይገኛሉ ሲሉም ገልጸዋል።

ያሉ ሀብቶችን በአግባቡ በማስተዋወቅና ባለሀብቶችን በመሳብ የዘርፉን አቅም ያህል ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ በኩልም በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ዘርፉ ላይ ቀድሞ የተሠራ ብዙ እርሾ አለመኖሩና ባህሪውም በአጭር ጊዜ ምርት መስጠት የሚችል ባለመሆኑ እስካሁን ድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት አልተቻለም። ይሁን እንጂ በቀጣይነት ዘርፉ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ዘርፉ በሚፈለገው ልክ እንዲያድግ አስተማማኝ ሀገራዊ ሰላም አስፈላጊ በመሆኑ ለሰላም መስፈን ሁላችንም በትብብር መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

# አገልግል

**የቅዳሜ መጽሔት**

የውስጥ ገጾች



## ‹‹ስተጎጂዎች በሶስት ዙሮች በመንግሥት ድጋፍ ባይደረግ ሊፈጠር ይችል የነበረውን አደጋ መገመት አይከብድም››

- አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

ገጽ 6



የትዳር አጋርን ነፍስ የነጠቀው የንዋይ ጥማት

ገጽ 12



ያልታየችው ጥበበኛ ትጣራለች

ገጽ 16

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ስተጎጂዎች በሶስት ዙሮች በመንግሥት ድጋፍ ባይደረግ ሊፈጠር ይችል የነበረውን አደጋ መገመት አይከብድም››

አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

**አስቴር ኤልያስ**

የዛሬው የዘመን እንግዳችን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) ናቸው፡፡ አምባሳደር ሽፈራው፣ ከዚህ ቀደም የፌዴራል ጉዳዮች እንዲሁም የትምህርት ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል፡፡ አሁን ወዳለቡት የአመራርነት ቦታ ከመምጣታቸው አስቀድሞ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ፤ በሌሴቶ እና ናሚቢያ የኢትዮጲያ አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል፡፡ የዛሬው የዘመን እንግዳችን በኮሚሽኑ እየተከናወነ ስላለው እንቅስቃሴ በተለይም በአንዳንድ አካላት መንግሥት ድጋፉ የተቀዛቀዘ ነው በሚል በሚነገረው እና በሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከሠብዓዊ ድጋፉ ጋር ተያይዞ አንዳንዶች ከረሃብ የተነሳ የሰው ሕይወት አልፏል በማለት ላይ ይገኛሉ፤ በእርግጥ በድጋፍ በእጦት የሞተ ሰው አለ?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** የአየር ንብረት ለውጡ በድርቅም በጎርፍም በመሬት መሸንራተትም ሆነ በተለያየ መንገድ በሚከሰትበት ጊዜ በአንድ በኩል የሰውን የኑሮ መሠረቱ የማናጋት ነገር ሊኖር ይችላል። በሌላ በኩል ለሕይወትም አደጋ የሚሆኑ ነገሮችን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች በኑሮ መሠረትም በሰው ሕይወትም ላይ የሚያስከትላቸው ጫናዎች ይኖራሉ፡፡

ከድርቅና ከጎርፍ ጋር በተያያዘ መንግሥት በሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፡፡ አንደኛው ድርቅ ወደረሃብ ተቀይሮ ሰው እንዳይጎዳ መከላከል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ይህንን አጋጣሚ ማለትም የድርቁን ሁኔታ ወደመልካም አጋጣሚ ፤መቀየር የሚያስችሉ ዘላቂ ልማት ሥራዎች መሥራት ነው፡፡

ይህ ሥራ የሚሠራው በሁሉም ደረጃ ነው። በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በኮሚሽን ይሠራል፤ በተመሳሳይ በክልሎችም ይሠራል፡፡ የክልሎች የተዋረድ መዋቅሮች አሉ፤ በእዛ ውስጥ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ይሳተፉበታል። ሌላውና ትልቁ ደግሞ በየደረጃው የሚሳተፈው ሕዝቡ ራሱ ነው፡፡ የተቸገረውን የኅብረተሰብ ክፍል የመደገፍ ሥራ ይሠራል፡፡

ይህንን ዘርዘር አድርገን ስናይ፤ ከታች እስከ ላይ ያለው የመንግሥት መዋቅር የሚያደርገው ርብርብ ሰዎች በድርቁ ምክንያት በግብርና ሆነ በእንስሳት ውጤትና በመሳሰሉት ላይ ጉዳት ስለሚደርስ ፤ በበቂ ደረጃ ተመጣጣኝ ምግብ የማግኘት ችግር ያጋጥማል። የውሃ እና የጤና አገልግሎት በሚስተጓጎልበት ጊዜም ሰዎች ተጓዳኝ ለሆኑ ችግሮች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

በእርግጥ ሞት ተፈጥሯዊ ጉዳይ እና ሁሌም ከማኅበረሰባችን ጋር አብሮ ያለ ነገር እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ “የሞተው በዚህ ጉዳይ ነው” በሚል ማረጋገጫ በመስጠት በእርግጠኝነት መናገር እጅግ በጣም አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ቀበሌ ወይም በአንድ ድርቁ ባለበት አካባቢ ሰው ቢሞት፤ ይህን ሰው የገደለው ድርቁ ወደረሃብ ተቀይሮ ነው የሚል አይነት መደምደሚያ መስጠት አግባብነት የለውም፡፡ የሞቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ከመረዳት ጋር የሚያያዝ ነው። የሞቱ ምክንያት የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረ ሕመም አሊያም በሌላ ሌላ ምክንያት ሞት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዙሪያ ያሉ የጤና ችግሮች አጋጥመውትም ሊሆን ይችላል። ድርቁ ምንም ዋጋ የለውም ማለት ግን አይቻልም፡፡ በድርቁ ምክንያቱም የተመጣጠነ ምግብ በመደበኛነት ካለማግኘቱ የተነሳ የመከላከል አቅሙም ተዳክሞ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ሁሉ በተለያየ መንገድ ተደራርበው የሚፈጥሩት ጫና ሊኖር ይችላል፡፡

**ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት የሚለዩት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንጂ በግምት አሊያም ሰዎች ስለፈለጉ ወይም ስላልፈለጉ አይደለም**


ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

በእኛ ስሌት እና አረዳድ ግን “ድርቁ ወደረሃብ ተቀይሮ ነው ዜጋውን ለሕልፈት ያበቃው” የሚለው መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የራሱ የሆነ ክትትል እና የራሱ የሆነ ማረጋገጫ መሥራትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ስናይ እስካሁን የፌዴራል መንግሥት በኮሚሽን ደረጃ ድርቁ ወደ ረሃብ ተቀይሮ ሰዎችን ለሞት እየዳረገ ነው በሚል የሚያናፍሱ ዘገባዎች ትክክል ናቸው ብሎ አይወስድም፡፡

“ድርቅ ወደረሃብ እየተቀየረ ነው” በሚል የተነገረው ጉዳይ የተሳሳተ ድምዳሜ ነው፡፡ ሞትን የመሰለ ነገር “የገደለው ይህ ነገር ነው” ብሎ ለማለት እና ለመለየት የራሱ የሆነ ደረጃዎች አሉት፡፡ በዚያ መንገድ የሚቀርበው አቀራረብ የተሠሩ ነገሮችን በጣም አቅልሎ ለማሳየት የተደረገ ነው ባይ ነን፡፡ የተሠራውን ሥራ ተቧድነው አቅልሎ የማየት ሁኔታ ስለሆነ በእኛ በኩል በዚህ መንገድ የተደመደመ ነገር አለመኖሩን መግለጽ እወዳለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች እስከተጠናቀቀው ታህሣሥ ወር ድረስ ያቀረበው ርዳታ ምን ያህል ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** ባለፈው በ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር ጀምሮ እስካለፈው ታህሣሥ ወር ድረስ የመጣንበትን ሒደት ስናይ የአጋር ድርጅቶች በተለይም የአሜሪካ ልማት ድርጅት ድጋፍ የሚያደርጋቸው የዓለም ምግብ ፕሮግራምና ሌሎች ተቋማት ለስድስት ሰባት ወር ያህል ሠብዓዊ ድጋፋቸውን አቋርጠው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

በዚያን ጊዜም ጭምር እነዛን ክፍተቶች ለመሙላት በመንግሥት በኩል ሰፊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በዚህም ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ወር 2016 ዓ.ም ድረስ በሶስት ዙር ድጋፎች ተደርገዋል፡፡

ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት የሚለዩት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንጂ በግምት አሊያም ሰዎች ስለፈለጉ ወይም ስላልፈለጉ አይደለም፡፡ የመጀመሪያው የሚታወቀው የቤተሰብ ሕይወትን የመታደግ ምጣኔ ምንድን ነው የሚመስለው? የሚለውን የሚለይ ጥናት (House hold Economic Analysis) በሚባል ነው፡፡

በየአካባቢው ምን ያህል ተጎጂ ሊኖር ይችላል? ከዚያ ደግሞ ያንን መነሻ በማድረግ በየቀበሌው እያንዳንዱ ቤተሰብ ላይ ተጋላጭ የሆነ ቤተሰብ ማን ነው? የሚለው ጥናት ይደረጋል፡፡ ማን ነው ተጎጂ የሚለውም የሚለየው በዚያ አይነት መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛው የተፈናቀሉ ማኅበረሰቦችን መለየት ነው። ይህ አሁን ላይ በአይ.ኦ.ኤም እና በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በጋራ የሚሠራው ነው።

ከእዚህ ውጭ በበርካታ ባለድርሻ አካላት እኛንም ክልሎችንም ጨምሮ ምን አይነት ሁኔታዎች አሉ? የሰብል ሁኔታ ምን ይመስላል? የእንስሳቱ ሁኔታ ምን ይመስላል? የጤና፣ የውሃ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚል ግምገማ ይካሄድና ከዚያ ክልሎች ደግሞ እንደነባራዊ ሁኔታው የሚያመጡት ነገር ተጨምሮ ነው ይህ ውጤት የሚገኘው፡፡

የወቅቱ ተደጋፊ አካል ማን ነው? ምንስ ያህል ሊሆን ይችላል? እና የት ነው ያለው? እያጋጠመው ያለው ምን አይነት ጉዳት ነው? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ጥናቶች ሲደረግ በመጀመሪያዎቹ ዙር ላይ ሰባት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን፤ በሁለተኛ ዙር ላይ ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን እንዲሁም በመጨረሻ ላይ ያለው ሶስተኛው ዙር ላይ ደግሞ ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ድጋፍ ፈላጊዎች ተለይተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

ሶስተኛው ዙር ድጋፍ ላይ አጋሮችም ተሳትፈውበት ስለነበር በጥቅሉ የነበረው ሲታይ የመንግሥት አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እንዳልኩት ሶስተኛው ዙር ላይ አጋሮችም ተቀላቅለው ስለነበር አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል እንዲደደርስ አድርጓል። በዚህ ውስጥ ደግሞ የሁለት ቢሊዮን ብር የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ነበር፡፡ እነዚህ ተደማምረው ሲታዩ በዚያን ወቅት መንግሥት ለብቻው ያደረገው ድጋፍ 11 ቢሊዮን ብር ነበር። የአጋሮቹ ሲጨመር ደግሞ ወደ 15 ቢሊዮን ብር ይሆናል፡፡

በዚህ ጊዜ ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች ከነበረው የጸጥታ ችግር የተነሳ በእኛ ዘንድ የርዳታ ክምችት ቢኖርም ለተረጂዎች ማድረስ አልተቻለም፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር፣ ዋግ ኽምራ፤ በኦሮሚያ ክልል ደግሞ ምዕራብ ወለጋ ዞን አካባቢ ድጋፉን የተፈለገውን ያህል በማንቀሳቀስ ሒደት ላይ የተፈጠሩ ክፍተቶች አሉ፡፡

እነዚያ ክፍተቶች ቢኖሩም በተለይ ወደኋላ አካባቢ ከታህሣሥ አጋማሽ ጀምሮ አጋሮችም በተቻላቸው መጠን በኮሚሽኑም በኩል በተቻለ መጠን ለማዳረስ የሚሞከር አለ፡፡ እንዲያም ሆኖ በእነዚህ ምክንያት የሚንጠባጠቡ ቦታዎች እንዳሉ ለመግለጽ እወዳለሁ። ከዚህ ጋር አያይዘን በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ዙር ለመሥራት በዝግጅት ላይ ነን፡፡ ክምችቱም ያለው በእጃችን ነው፡፡ በዚያ መንገድ ወደ ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎቻችን ይታገዛሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በእስካሁኑ የሠብዓዊ ርዳታ ድጋፍ የቀረበው በየትኞቹ አካባቢ ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** አስቀድሜ ባነሳኋቸው መስፈርቶች መሠረት ይህ ጥናት የሚካሄደው በሀገሪቱ በሙሉ ነው፡፡ አንዳንድ የማይደረስባቸው ቦታዎች ቢቀሩም በጥናቱ በተለየው መሠረት ለምሳሌ ከድርቅ ጋር በሚያያዝ በአማራ ክልል ወደ ስምንት ዞኖች ያህል፣ ትግራይ አራት ዞኖች እና አፋር ላይ ወደ ሶስት ዞኖች ከዚያ ኦሮሚያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም የደቡብ ኢትዮጵያ አንዳንድ ኪስ ቦታዎች አሉ።

እነዚህ በአንድ ላይ ተደምረው ወደ አራት ሚሊዮን አካባቢ የሚሆኑ ተጎጂዎች ተለይተዋል፡፡ አስቀድሜ የጠቀስኳቸውን ቦታዎች ጨምረን ወደ አራት ሚሊዮን የሚጠጋ ማኅበረሰብ በድርቅ አደጋ የተጎዱባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ ይህ ማለት ካለፈው ዓመት ሐምሌ ወር እስከ አሁኑ ታህሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ያለው ነው፡፡

በፊትለፊታችን ባሉ ወራት ደግሞ ወደ ስድስት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ስተጎጂዎች በሶስት ዙሮች በመንግሥት ድጋፍ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የተለዩ ተረጂዎች ይኖራሉ:: ይህ ከድርቁ ጋር ተያይዞ ያሉትን ጨምሮ በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች በግጭትም ሆነ በጎርፍ ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍል አካቶ ማለት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቁጥራቸው ከፍ ያለ እንደመሆኑ መንግሥት በወቅቱ ድጋፉን ባያቀርብ ኖሮ ሊከሰት የሚችለው አደጋ ምን ይመስል ነበር ይላሉ?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** እንደሚታወቀው የድርቅ መጨረሻው ነገር በዙሪያው ካሉ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተቧድኖ ኅብረተሰቡን ለጉዳት ሊዳርግ ይችላል። እንዲህም ሲባል የኅብረተሰቡ የመከላከል አቅሙ እንዲዳከም፣ በዙሪያው ካለው ከንጹህ ውሃ ከማጣት የተነሳ ለበሽታ ሊጋለጥ ይችላል:: ይህ ሲደራረብ ደግሞ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ምንም ጥያቄ የለውም::

ስለዚህም አስቀድሜ ባነሳሁት በሶስት ዙሮች ሲደረግ የነበረው ድጋፍ ድርቅ ወደረሃብ እንዳይቀየር ከፍተኛ የሆነ ድርሻ የነበረው ነው ማለት እንችላለን። ይህ ድጋፍ ሲደረግ የነበረው እነዚህ አጋር ተቋማት ድጋፋቸውን አቋርጠው በነበረበት ጊዜ ነው ። በዚህ ወቅት እኛ ወደ ሰባት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ቀጥሎም ሶስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሕዝብ ለመደገፍ እንቅስቃሴ አድርገናል :: ይህ ድጋፍ ባይደረግ ኖሮ ሊከሰት የሚችለውን ችግር መገመት ይቻላል::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የአጋር ድርጅቶች ሚና እንዴት ይገለጻል? በቀጣይ ከእነርሱ ጋር ስላለው ግንኙነት የታሰበው ምንድን ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** አጋር ድርጅቶች በአብዛኛው አሜሪካ የልማት ድርጅት የሚያግዛቸው ናቸው:: አጋር ድርጅቶች መልሰው ወደዚህ ሥራ ሲገቡ ከዚህ በፊት ይሠራ በነበረው በ20 በመቶ ላይ የሚጨመር በመሆኑ አቅም የሚፈጥር ነው። ስለዚህ ባለፈው ዓመት ከነበረው ወደ 20 በመቶ አቅም ላይ መውረዳቸው ቀሪውን ክፍተት መንግሥት እንዲሸከመው መነሻ ሆኖ ቆይቷል ማለት ነው::

ስለዚህ ከአጋሮች ጋር ያለን ግንኙነት እንደ የትኛውም ጊዜ መልካም ነው ብለን ብንልም ከሀብት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲታይ ሒደቱ በየጊዜው እየቀነሰ ነው::

ከሌሎች የተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ አካላት ጋር በጉዳዩ ከሚያገባቸው ጋር በጋራ በየሳምንቱ ጉዳዮቹን እየተከታተልን፤ እነሱም ድርሻቸውን እንዲያጎለብቱ እያደረግን የምንሠራው አለ:: በዚህ በኩል የኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የሠብዓዊ ድጋፍም ይሁን ከሌሎች ሠብዓዊ ድጋፍ ከሚያስተባብሩ ተቋማት ጋር በቅርበት እየሠራን ነው::

ባለፉት ወራትም በተለይም ከማዕከላዊ የድንገተኛ ድጋፍ ማዕከል (Central Emergency Response Fund) ከሚባለው ወደ 23 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተመድቦ በድርቅ ለተጎዱ፣ የበሽታ ወረርሽኝ በተከሰተባቸው እና በጎርፍ ለተቸገሩ አካባቢዎች ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል:: ይህ በዓለም አቀፍ ተቋማት በኩል፤ ከፊሉ ደግሞ በሀገር በቀል ተቋማት በኩል ተግባራዊ የሚሆን ነው::

ነገር ግን የምግብ አቅርቦትን በሚመለከት የአጋር ድጋፍ በ20 በመቶ ላይ የተገታ ነው:: ይህም የሆነው የዓለም ምግብ ፕሮግራም (World Food Programme) ሆነ ሌላው ይሁን የሚሰጠው አገልግሎ የ20 በመቶው ፈንድን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል መንግሥት ድጋፉን በራሱ አቅም ለመሸፈን ዓላማ እንዳለው ሲነገር ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ያለው እቅድ ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** ከዚህ አኳያ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ይኖራሉ:: አንደኛው አሁንም ለሚቸገረው ማኅብረሰባችን ሠብዓዊ ድጋፍን በቅርበት ማዳረስ ነው:: በዚህም ድርቁም ይሁን ሌሎች ነገሮች ዜጎቻችንን ወደሚጎዱበት ደረጃ እንዳይደርሱ መሥራት ነው:: ይህንን በምንሠራበት ሒደት በፌዴራል ኮሚሽን ከአጋር ተቋማት፣ ከተባበሩት መንግሥታት የሚመለከታቸው ተቋማት በቅርበት እንሠራለን::



ክልሎች እና ከክልል በታች ያሉ የመንግሥት መዋቅሮችም የራሳቸው የሆነ ተሳትፎ ይኖራቸዋል። ከሁሉም በላይ ሕዝባችን በተለመደው መንገድ ያለውን እና የመደጋገፍ እሴቱን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ሁለተኛው ሠብዓዊ ድጋፍ በራስ አቅም መቻል ነው:: ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህ በሁሉም ደረጃ የሚፈለግ ነው:: በአንድ በኩል የተረጂን ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎችን በስፋት መሥራትን ይፈልጋል:: ሁለተኛው ደግሞ ተጨማሪ ምርት በማምረት በተለይ ከገበያ ጋር መሻማት ሳያስፈልግ ለሠብዓዊ ድጋፍ የሚሆን ምርት ለሚያስፈልገው እንዲዳረስ መሥራት ነው::

ይህንን በማድረግ ሒደት ላይ ሠብዓዊ ድጋፍ አስፈላጊ ሳይሆን ቀርቶ ምርቱ እጃችን ላይ በሚኖርበት ጊዜ ለገበያ ሊቀርብ ይችላል፤ ለውጭ ገበያ ሊቀርብ ይችላል:: እናም ሁኔታዎች በዚህ መልኩ መሔድ ሲጀምሩ "የኢትዮጵያ ርዳታ" (Ethiopian Aid) በሚባል ደረጃም እስከዚያ ድረስ ላለው ድጋፍም ሊሆን የሚችል ነው::

ስለዚህ በአንድ በኩል ሠብዓዊ ድጋፉ አቅርቦቱ ይቀጥላል:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ለሚገባው ብቻ እንዲሆን የማድረግ እና ሁሉም ባለድርሻ እንዲተባበር በማድረግ ነው:: ሁለተኛ ሠብዓዊ ድጋፍ በራስ አቅም መሥራት ነው:: ሊለሙ የሚችሉ በጣም ሰፋፊ በመስኖ ልማት መሬት አለን። እንደሚታወቀው ወደሥራ ሊሰማራ የሚችል የወጣት ጉልበት አለ::

በተለይም ትርፍ አምራች በሆኑ አካባቢዎች ላይ ውሃና ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይ አለ:: የተወሰነ አካባቢ ድርቅ ያስቸግራል ብንልም በጣም በአመዛኙ ግን ሰፋፊ ቦታዎች ላይ ትርፍ ምርት ፤ ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይ ያላቸውን አካባቢዎች መሠረት በማድረግ ወደማምረቱ እንገባለን የሚል ነው::

ከሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት አኳያ አሁን በሚቀጥሉት ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት ላይ ወደስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ተደጋፊ ዜጎች ይኖሩናል:: ለዚህ የሚሆን ዝግጅትም በራሳችን በኩል አድርገናል። ስለዚህ አንድ ላይ ከመንግሥት በኩል ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ማኅበረሰብ ለመሸፈን የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል ማለት ነው:: ይህም ወደ 531 ሺ

**ከሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት አኳያ በሚቀጥሉት ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት ላይ ወደ ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ተደጋፊ ዜጎች ይኖሩናል፡፡ ለዚህ የሚሆን ዝግጅትም በራሳችን በኩል አድርገናል**

አካባቢ ኩንታል እህል የሚፈልግ ነው:: የቀሩትን ደግሞ ከአጋር ድርጅቶች ሥራ ላይ የገቡ ስላሉ እነርሱ የራሳቸውን ድርሻ ወስደው ወደሥራ ይገባሉ ::

በዚህ አይነት መንገድ ለሚቀጥሉት ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት ድረስ ያለውን ድጋፍ ለማከናወን በመንግሥትም በኩል ዝግጅት አድርገናል:: በሌላ በኩል አጋር ድርጅቶች የራሳቸው ድርሻ ይኖራቸዋል። ከዚህ በፊት የነበረውን ነገር በተጠናከረ መንገድ እንቀጥላለን::

በጸጥታ እና በተለያዩ ምክንያት ለማዳረስ ችግር የሆነባቸው አካባቢዎችም በየአካባቢው ያለውን የጸጥታ መዋቅር እየተጠቀምን ድጋፉ የሚቀርብበትን ሁኔታ ላይ እየሠራን እንገኛለን:: እሱም ላይ ውጤታማ የሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: ሁኔታውን እየለየን እየሠራን እንቀጥላለን::

በመጨረሻም ማስተላለፍ የምፈልገው በ70 ዓመት ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የአየር ንብረት ለውጥ ማስተናገዳችን ይታወሳል:: ባለፈው አምስት ተከታታይ ወቅቶች በሙሉ ዝናብ ጠብ ሳይል ቀርቶ ወደ 11 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ችግር ውስጥ ገብቶብን ከርሟል::

በተለይም ደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የነበሩ አካባቢዎች ላይ፤ አሁን ደግሞ በሰሜን አካባቢ በጣም በሰፋ መንገድ ፈተና ተጋርጦ ነበር። በጎርፍም በተባይም በአንበጣም የተደራረበ ችግር ተፈጥሯል:: ይህን መሠረት በማድረግ የሁሉም አካላት ሰፊ ርብብር እና መተጋገዝ ብሎም መደጋገፍን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል::

በአጋር በኩል ያለውም 20 በመቶ ላይ የተንጠለጠለው ድጋፍ ከዚህ የተሻለ ቢሆን የሚመረጥ ነው:: በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ችግር አለ፤ ይህ የዓለም አቀፍ ችግር ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢም ችግር ነው:: ድጋፉ ከዚህ አንጻር የተቃኘ ቢሆንና የተከሰቱ ችግሮችን ማየት የሚቻልባቸው እድሎች ቢኖሩ መልካም ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

በድጋፍ ላይ የሌሉ ወይም ለመደገፍ ያልታደሉ አካላት አሉ:: እነዚህ አካላት መንግሥት፣ ሕዝብ እና ሌላው የሚያደርገውን ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኞች ያልሆኑ ናቸው:: በየክልሉ በሚደረገው ድጋፍ ውስጥ የሌሉ ናቸው:: ነገር ግን የተደረገውን ድጋፍ ለማየት አይፈልጉም፣ የተደረገው ድጋፍ ያዳነውን የሰው ሕይወትም ለማየት ያልታደሉ ናቸው::

እነዚህ አካላት ምናልባት ከዚህ አይነት አስተሳሰብ ተቆጥበው እነዚህን ዓለም አቀፍ እና አሕጉር አቀፍ ችግሮች በጋራ ለመታደግ በሚደረገው ርብርብ ደጋፊ ቢሆኑ መልካም ነው:: ለዜጎቻችን የኑሮ መሠረቶቻቸውን ለመታደግም ይሁን ሕይወታቸው ላይ አደጋ እንዳይደርስ በመሥራት በኩልም ተባባሪ ሊሆኑ ይገባል:: ይህ ከሆነ ሁላችንንም የሚያስደስት እና የተሻለ ውጤት እናገኛለን ብዬ አስባለሁ::

አስቀድሜ እንደጠቀስኩት እስካሁን በመንግሥት ደረጃ ወደ 11 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል፤ ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ተይዟል። ይህ ሁሉ ከመንግሥት ካዝና እየወጣ የሚሠራ ሥራ ነው:: ይሁንና በዚህ ልክ እየተሠራ እያለ በአንዳንድ አካላት መንግሥት ለችግሩ ትኩረት እንዳልሰጠው ተደርጎ ሲነገር ይደመጣል:: እንዲያውም መንግሥት ለዜጎቹ ችግር ጆሮ ዳባ ልበስ እንዳለ ተደርጎ ለማቅረብ ይሞከራል። መንግሥት ችግሩ ግድ እንደማይለው አድርገው ለመሳል የሚፈልጉ አካላትም አሉ::

በየትኛውም መስፈርት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት፤ በሕዝቡ እየተደረገ ያለን መደጋገፍ፤ ከዚያም ባለፈ በተባበሩት መንግሥታት አካላት የሚደረጉ ጥረቶችን፤ ላለማየትም ላለማዳመጥም መሞከር ለማንም አይጠቅምም:: እነዚህ አካላት ካልተገባ መንገዳቸው ተመልሰው ችግሩን በጋራ ተረባርበን እና ተጋግዘን የምንሻገርበትን ሁኔታ መፍጠር የተሻለ ነው ለማለት እወዳለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የሁልጊዜ ተባባሪያችን ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

## ወቅታዊ

# “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን ዘርፍ በማነቃቃት በርካቶች ወደ ቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲገቡ እያስቻሉ ነው”

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ


ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በወቅታዊ ነባራዊ የቱሪዝም ዘርፉ እንቅስቃሴ ላይ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ የመጀመሪያ ክፍል ትናንት ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ ክፍል በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው በዋነኝነት ትኩረት ከተሰጣቸው አምስት የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች መካከል የቱሪዝም ዘርፉ አንዱ ስለመሆኑ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት ዘርፉን ስላጋጠሙት ፈተናዎች እና ፈተናዎች አልፎ አሁን ያለበት ደረጃ ምን እንደሚመስል አይተናል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር፣ በቱሪዝም ዲፕሎማሲው ከገጽታ ግንባታ ጋር የተሠሩ ሥራዎች፤ እየተከናወኑ ስላሉ የቱሪዝም መዳረሻ ልማቶች… ወዘተ ያሉ ተጨባጭ እውነታዎችን ለማየት ሞክረናል። በዛሬው እትማችን የቃለ ምልልሱን የመጨረሻ ክፍል ይዘን ቀርበናል።

**ጥያቄ- ዓለም አቀፍ ቅርሶች ሲመዘገቡ ይዘው የሚመጡት ትሩፋቶች ቅርሶች ላይ የሚደረጉ ጥበቃና እንክብካቤ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቀደም ሲል በተመዘገቡ ቅርሶቻችን ላይ የሚደረጉ ጥበቃዎች ተደጋግሞ ሲነሳ ቆይቷልና በዚህ ረገድ ምን እየተሠራ ነው?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ዩኔስኮ እውቅና ሰጠም አልሰጠም እንደሀገር መሥራት አለብን። እነዚህን ቅርሶች ከአባቶቻችን ከአያቶቻችን የተረከብናቸው ናቸው። በታሪክ አጋጣሚ እኛ ላይ አርፈዋል። እኛም ጠብቀን ተንከባክበን ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ኃላፊነትም፤ ግዴታም አለብን። በዩኔስኮ ስለተመዘገቡ ሳይሆን እንደሀገር እንደ ሕዝብ ኃላፊነት ስላለብን እነዚህን ሥራዎች መሥራት ይጠበቅብናል።

ከቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ አንጻር ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው ከተባለ፤ እንደሚታወቀው እንደሀገር በጣም ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ያ ማለት በጣም ብዙ ቅርሶች ይኖሩናል ማለት ነው። በየትኛውም መዳረሻ ስንሄድ በኢትዮጵያ ክፍል ቅርሶች አሉ። በጣም ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ፤ ለማኅበረሰብም ለዓለምም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው፤ ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉ፣ መመዝገብም መጠበቅም ያለባቸው ብዙ ቅርሶች አሉ።

ከዚህ አንጻር እንደተቋም ብቻ የሚሠራ ሥራ አይሆንም። ማኅበረሰብ የራሱ የሆነ ኃላፊነት አለው፤ የራሱ ቅርስ ነው። ራሱ የተረከበውን ጠብቆ ማስተላለፍ አለበት። ማኅበረሰብ የራሱን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል። ሲቀጥል ደግሞ በየደረጃው ያሉ የተለያዩ አካላት ተቋማትን ጨምሮ የግልም የመንግሥትም ሊሆኑ ይችላሉ ኃላፊነት አለባቸው።

ቅርሶችን ሊጠብቅ የሚችለው ሕዝብ ነው ። ብዙ ቅርሶቻችንን ተመልከቱ ዋና ጠባቂያቸው ሕዝብ ነው። ከሕዝብ ሲቀጥል ደግሞ ሌሎች ተቋማት ይመጣሉ። በፌደራል ደረጃ ያሉ ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ልክ እንደ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፤ በክልል ያሉ ተቋማትም የራቸው የሆነ ኃላፊነት አለባቸው።

የተለያዩ ሲቪክ ማኅበራትም በቅርስ ጥበቃ ሥራ ላይ እንደ ሀገር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ቅርስ ማስመለስ ላይም ቅርስ እንዲጠበቅ የማድረግ ላይም የራሳቸው የሆነ አስተዋፅዖ ያላቸው ማኅበራት አሉ። የዚህ ሁሉ ቅንጅት ነው አንድን ቅርስ ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርገው። በዚህ ዘርፍ እንደሀገር ያለብን ክፍተት የመጀመሪያው ከሙያ አንጻር ነው።

ቅርስ ጥበቃ በጣም የተለየ ሙያ ይጠይቃል። ለዚያ ሙያ የሚሆኑ ሰዎችን ማፍራት ያስፈልጋል። እንዳጋጣሚ ሆኖ ደግሞ በሀገር ውስጥ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ የሚሰጥ ኮርስም የሚሰጥ ትምህርትም የለም። ስለዚህ ብዙ ጊዜ ቅርሶች ሲጠገኑ፣ እንክብካቤ ሲደረግላቸው ኦርጅናል ይዘታቸውን የመልቀቅ ሁኔታዎች ይታያሉ።

እንደ ሀገር እነዚህን ሙያዎች የሚያሠለጥን ኮርስ የሚሰጥ ተቋም ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ክፍተት አለብን። ይሄን በተለያየ መልኩ ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ነው። እሱም መቀረፍ አለበት። የእንጨት ሥራ ላይ ልምድ ያላቸው ፤ከድንጋይ ጋር ተያይዞ ልምድ ያላቸው፤ በተለያየ መልኩ ልምድ ያላቸው በጣም ብዙ ሰዎች ያስፈልጉናል።

ከዛ በዘለለ እንደ ሀገር ያሉንን ትልልቅ የሚባሉ ቅርሶችን ከመጠበቅ አንፃር እንደ መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በጣም ብዙ ርብርቦች ተደርገዋል። ከዓለም አቀፍ/ከኢንተርናሽናል አጋሮቻችን ጋር በመሆን የተለያዩ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በመሥራት ጥረቶች እየተደረጉ ነው።

እንደምታስታውሱት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከፈረንሳይ አቻቸው ጋር ተነጋግረው የላሊበላ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ተጀምሯል። የዋናው ቅርስ ጥገና ሥራ ጥናቶች እየተጠናቀቁ ይገኛል። እንዲሁም ዋናው የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ እስኪጀምር ደግሞ አስቸኳይ የሆኑ የጥገናና የእንክብካቤ ሥራዎች በዘላቂነት /ሴስቴኔብል/ በላሊበላ እየተሠሩ ይገኛል።

ይህ እንግዲህ ለቅርሱ የተለያዩ አስቸኳይ ጥገናዎችን የማድረግ ሥራ ብቻ ሳይሆን የቅርሱን ደረጃውን የማስጠበቅ፣ ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ/ስታንዳርድ የመለወጥ እና አካባቢውን አብሮ የመጠበቅና የማልማት ሥራንም ያካተተ ነው።

ለምሳሌ በላሊበላ ሰው ቀስ ብሎ የሚራመድበት መንገዶች /ዎክ ዌይ/ ተሠርተዋል። ከዚህ በፊት ገብቶ ለመውጣት በጣም አስቸጋሪ ነበር። የዲሽ ቁፋሮና ጠረጋ ሥራዎች ተሠርተዋል። መብራት፤ ድልድይ የመሳሰሉ፤ የተለያዩ የመንገድ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

እነዚህ ሥራዎች ፋይዳቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ለምን ቅርሱ እንደተጠበቀ ከማቆየት አንፃር ብቻ ሳይሆን የበለጠ የቱሪስት ልምዱን ከማሳደግና መዳረሻ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ስላላቸው ነው።

በተመሳሳይ በተለያየ መልኩ እየተጠገኑ ያሉ ቅርሶች አሉ። በተለያየ መልኩ በእቅድ የተያዙ ቅርሶችም አሉ። ነገር ግን ሁሉንም ከማዳረስ አንፃር እንደ ፌዴራል ተቋም ውሱንነቶች አሉብን። ምክንያቱም የቅርስ ጥገና ብዙ ሀብት የሚፈልግ ነው።

በዚሁ አጋጣሚ፤ ቅርስ ጥገና አንደኛው/ዋነኛው ተዋናይ ማኅበረሰቡ ነው። ሁለተኛ የክልል ተቋማትና የክልል መንግሥታት ናቸው። ቅርስ ጥገና ሲባል የሚመጣው ወደ ፌዴራል ከመሆኑ አንፃር እነዚህም ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በዚሁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

**ጥያቄ፡- ሚኒስቴር መሥሪያ በቅርስ ጥበቃ ዙሪያ ከክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያደርጋቸው ጥረቶች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** ከቅርሱ እንጀምርና ስለሌሎቹ ጉዳዮች እንሄዳለን። ከክልሎች ጋር ያለን የቅንጅት ሥራ በተመለከተ የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን በአብዛኛው ከሚባሉ ክልሎች ጋር በጋራ ይሠራል። የቅርስ ጥበቃውም እንክብካቤውም ሥራ ቅርሶች ክልል ላይ እንደመሆናቸው በከፍተኛ ቅንጅት ከእነዚህ ተቋማትና ከክልል መንግሥታት ጋር ይሠራል።

ከላይ ያነሳሁት ጠቀሜታውና አስፈላጊነቱን ለማሳሰብ ነው እንጂ እነዚህ የቅንጅት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። አሁንም እየተጠገኑ ያሉ ቅርሶች በቅንጅት ነው። ጅማን፣ ፋሲለደስ የሚደረገውንም ጥገና መውሰድ ይቻላል።

አሁን እያወራን ባለንበት ሰዓት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚደረጉ ጥገናዎች አሉ። ለምሳሌ ቤኒሻንጉል፣ አፋር፣ ሱማሌና በተለያዩ ክልሎች ብንወስድ የተለያዩ የቅርስ ጥገናዎች እየተካሄዱ ነው። ከክልሎች ጋር በመናበብና በትብብር እየሠራን ነው።

ነገር ግን ብዙ ቅርሶች ያሉን ስለሆነ ትብብሩም ማጠናከርና በተሻለ ሁኔታ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ያለውን ነገር ከማሳደግ አንፃር ነው እንጂ የቅንጅት ሥራዎቹ አሉ። ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

**ጥያቄ፡- ከቱሪስት ገቢ ጋር በተያያዘ በክልል የቱሪዝም ቢሮዎችና በቱሪዝም ሚኒስቴር በኩል የሚወጡ መረጃዎች መጣረስ ይታይባቸዋል፤ ይህ ከምን የመነጨ ነው?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** የገቢ ስሌትን በተመለከተ ገቢ የሚሰላበት ዓለም አቀፍ አሠራር አለ። ይህን ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ከኛ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥመን እንሠራበታለን። ለምሳሌ የቱሪስት ቁጥርን በተመለከተ ዋና የመረጃ ምንጭ የምናደርገው ኢሚግሬሽን ነው። ለምን? የኢሚግሬሽን የቁጥር መረጃ አይሳሳትም። መከፋፈያ መንገድ አለው።

ማን ዘመድ ጥየቃ መጣ፣ ማን ለጉብኝት መጣ፣ ማን ወደ ሌላ ሀገር ሊሸጋገር መጣ የሚሉት እና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች አሉት። ስለዚህ ዋና የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለን የቱሪስት ቁጥር ስንናገር ኢሚግሬሽን ነው። የተለያዩ ተቋማትም ሲያወጡ እንደምታዩት እኛ የምናወጣው ቁጥር በብዛት ከዓለማቀፍ ተቋማት ከሚያገኙት የራቀ አይደለም።

ኢንተርናሽናል ስታንዳርዱ እንደሚፈቅደው ከቱሪስት ገቢ ለመሥራት ይህ ቁጥር ሲባዛ በቀን ወጭ ሲባዛ በቆይታ ጊዜ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ የቆይታ ጊዜ ከዚህ በፊት በተደረገ ጥናት ይታወቃል። ማዕከላዊ/አቬሬጅ የቆይታ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ፤ ስለዚህ ያንን የመጣ የቱሪስት ቁጥር ከቆይታ ጊዜ እንዲሁም በቀን ምን ያህል ያወጣል ተብሎ ከሚታሰበው ወጭው ጋር ይሰላል ማለት ነው። ስለዚህ የራሱ የሆነ ሳይንቲፊክ ስሌት-ሜትድ አለው።

የሀገር ውስጥ ቱሪስትን ከወሰድን በአብዛኛው የመረጃ ምንጮች/የዳታ ሶርሳችን የክልል መረጃዎች / ዳታዎች ናቸው። ስለዚህ ከክልሎች መረጃዎችን እንሰበስባለን/ፑል እናደርጋለን ማለት ነው። አንዳንዴ ቁጥርን አስመልክቶ የሚፈጠሩ ውዝግቦች ምንድ ናቸው የተባለ እንደሆነ እንደሀገር ብዙ የመረጃ ክፍተቶች/የዳታ ክፍተቶች ይኖሩብናል። ለምሳሌ አንድ ቱሪስት ምን ያህል ቆየ የሚለው ምናልባት ድጋሚ ሰርቬይ መሥራት የሚያስፈልገው ይሆናል።

አሁን ባለው አሠራር አንድ ቱሪስት በአማካኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ10 እስከ 11 ቀን ይቆያል። ሲጓጓዝና የተለያዩ ነገሮችን ሲያደርግ ይቆያል። ስለዚህ ያንን በአማካኝ በየቀኑ የሚያወጣውን ነው የምናባዛው። ነገር ግን እነዚህን መረጃዎች/ዳታዎች የበለጠ ማጥራት የበለጠ መተርጎም ያስፈልጋል። በተለየ ደግሞ ከሀገር ውስጥ ቱሪዝም ጋር የሚያያዙ መረጃዎችን/ ዳታዎችን የበለጠ ማጥራት ያስፈልጋል።

ይህን ችግር ለመፍታት አሁን ላይ ያዘጋጀነው የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት አለ። በቀጣይ ወራት ወደ ሥራ የምናስገባው፤ ይህንን የቱሪዝም ሚኒስቴር ከልማትና ፕላን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሌሎችም የፌደራል ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ከግሉም ሴክተር፤ የአስጎብኚ ተቋማት ጋር አብሮ እየሠራ ነው።

ያለው የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት መረጃ/ዳታ በተለያየ መልኩ በኤክስፐርቶች ድጋፍ እየተደረገለት እየሠራ ይገኛል። የዚህ የቱሪዝም ሴክተር ሳተላይት አካውንት ዋና ፋይዳው፤ አንደኛ ምን ያህል ቱሪስት መጣ የሚለውን በሚገባ ያጣራል። ሁለተኛ ቱሪዝም ለጂዲፒ ያለውን አስተዋፅዖ በግልጽ ያስቀምጣል።

መረጃዎችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች /ዳታ ሶርስ/ እናሰባስባለን/ፑል እናደርጋለን። ከአየር መንገድ፤ ከተለያዩ ባንኮች፤ ከኢሚግሬሽን እና ከተለያዩ ተቋማት፣ ከሥራና ክህሎት በጣም ብዙ ከሚባሉ ተቋማት ይሰበሰባል/ ፑል ይደረጋል። እንደ ሀገር ከምንሠራው ከብሔራዊ ቆጠራ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን ከሚሠራቸው የተለያዩ ሰርቬዎች መረጃ ይሰበሰባል/ዳታ ፑል ያደርጋል።

በዚህም ዘርፉ ለጂዲፒ ያለው አስተዋፅዖ ምን ያህል ነው የሚለውን ጥርት አድርጎ ማሳየት ያስችላል። መንግሥት ቱሪዝምን ከዋና ዘርፎች አንዱ ነው ብሎ ወስዷል። ኢንቨስትም እያደረገ ነው። እየወጣበት ያለውን ወጪ የሚመጥን አስተዋፅዖ አለው የሚለውን በሚገባ ያሳያል።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን ዘርፍ በማነቃቃት...

**ከ8ኛው ገጽ የዞረ**

ከዛ በተጨማሪ መንግሥትን ሆነ የግሉን ዘርፍ በዘርፉ ኢንቨስት የሚያደርገውን በሚገባ እና በግልጽ ያሳያል፡፡ በዘርፉ ስንት ሰው ተቀጠረ የሚለውን በግልጽ ያሳያል፡፡ በቀጥታ የተቀጠሩትንም ያሳያል፣ በተዘዋዋሪ የሥራ እድል የተፈጠረላቸውን በሚገባ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ከጂዲፒ አስተዋፅዖ አንጻር ጥርት ያለ መረጃ/ ዳታ ይኖራል። ከሥራ ፈጠራ አንጻር፤ ከዚህ በፊት እንዳለው የሪፖርት መጋጨት እና የመሳሰሉት ችግር አይኖርብንም። ችግሮቹን በመቅረፍ ጥርት ያለ መረጃ/ ዳታ ይኖረናል፡፡

ምክንያቱም ብሔራዊ ስታትስቲክስ በየጊዜው ከሚሠራቸው ሰርቬዎች በተለያየ መልኩ የሚሠሩ ስለሆኑ ጥርት ያለ መረጃ/ ዳታ ስለሚሰጡ እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥርት ያለ የቱሪዝሙ ስታትስቲክስ መረጃ/ ዳታ እናገኛለን፡፡ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት አሁን ጨርሰን ወደ ሥራ እያስገባን ስለሆነ በዘርፉ ያለው መረጃ እየጠራ ይመጣል ፡፡

በዚህ ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነውን አስተዋፅዖ እናያለን ማለት ነው፡፡ እስከአሁን ባለው ግን በተቻለ መጠን የቱሪዝም፤ የኢሚግሬሽን ዳታ ሰብስበን/ፑል አድርገን ዓለማቀፍ ስታንዳርዱ በሚያስቀምጠው መልኩ በቆይታ ጊዜ እናባዘዋለን፤ እንዲሁም በአቬሬጅ ዴይሊ ኤክስፔንዲቸር እናበዛዋለን፡፡

**ጥያቄ፡- የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማስፋፋት አንጻር ምን እየተሠራ ነው ?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማበረታታት አንጻር ያለፈው ዓመት የጀመርናቸው ትልቅ የሚባሉ ዋና ዋና ሥራዎች አሉ፡፡ በዚህ ዓመትም እነዛን ሥራዎች ማስቀጠል ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው፡፡

ያለፈው ዓመት ከጀመርናቸው ዋና ዋና ከሚባሉ ሥራዎች አንዱ የልወቅሽ ኢትዮጵያ ዘመቻ ነው። የልወቅሽ ኢትዮጵያ ዘመቻን በተለያየ መልኩ በዲጂታል ፎርሙ እንዲሁም በኮንቬንሽናል/በዋናው/ ሚዲያ መሥራት ጀምረናል፡፡ ያለፈው የእግር ኳስ ላይ ታስታውሳላችሁ፡፡ ያ ከፍተኛ መነሳሳትና የመጓዝ ፍላጎትን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡

ከዛ በተረፈ በተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉ ጉብኝቶች እና መነሳሳቶች እንዲኖሩ እንደሀገር ከሠራናቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ የቱሪዝም ክበባትን መመሥረት ነው፡፡ የቱሪዝም ክበባትን በተቋማት በመንግሥት እና በግል ተቋማት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በተለያየ ቦታ ክበባት እንዲመሠረቱ ካለፈው ዓመት ጀምሮ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገናል፡፡

በጣም ብዙ የሚባሉ ተቋማት እስከታች ወርደው የጉዞ ክበባትን መሥርተዋል፡፡ ለምሳሌ ባንኮች እስከታች ቅርንጫፎች ወርደው፤ እንደገቢዎች ሚኒስቴር ያሉ ትልልቅ ተቋማት እስከታች ቅርንጫፎች ወርደው፤ የጉዞ ክበባትን መሥርተዋል፡፡ እንዲሁም ሌሎችም በግል ትምህርት ቤቶች ደረጃ የጉዞ ክበባትን መመሥረትና እንዲነቃቁ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡

ይሄ እንግዲህ እንደምታውቁት ድሮ የጉዞ ክበባት አሉ ሰዎች አዋጥተው አንድ ላይ አብረው ይጓዛሉ። ያንን ልምድ ማበረታታትና ድጋሚ ማምጣት ያስፈልጋል በሚል እሱ ተሠርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከባንኮች ጋር የሠራነው ሥራ አስፈላጊ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ከባንኮች ጋር የቁጠባ አካውንቶች፤ የተለያዩ ትርፍ ያላቸው የተለያየ ትርፎችን ማስገኘት የሚችል የቱሪስት የቁጠባ አካውንቶች እንዲከፈቱ ተደርጓል ለዚህም ከሌላው ቁጠባ አካውንት የተሻለ ጥቅም እንዲኖረው እንዲሁም የተለያየ ሽልማት እንዲኖሩት አድርገናል፡፡ እነዚህን በተለያዩ ባንኮች የመክፈት ሥራ ተሠርቷል፡፡

ከዛ በተጨማሪ ከቴክኖሎጂ አንጻር ያለፈው ዓመት ወደሥራ ያስገባነው የቪዚት ኢትዮጵያ አፕሊኬሽን እንደሀገር ስንጓዝ፣ ተጉዘን ስናበቃ የተለያየ ለማስታወቅ ይረዳ ዘንድ የተለያዩ አካላትም ልክ እንደማኅበራዊ ሚዲያ ጉዛቸውን ፖስት የሚያደርጉበት መዳረሻውን የሚያስተዋውቁበት ለመፍጠርም ልምዳቸውንም የሚያካፍሉበት ከማድረግ አንጻር ታስቦ መተግበሪያ ወደሥራ ገብቷል ፡፡

ስለዚህ በዚህ ዓመት የበለጠ እነዚህን በሚገባ የማጠናከር፣ የተለያዩ ዘመቻዎችን የማስተዋወቅ፤ የተመሠረቱት የጉዞ ማኅበራት ወደ ሥራ ገብተው ሰዎች



**ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደተቋም ሀገርን የማስተዋወቅ ኃላፊነት፣ የሀገርን ውበት የማሳየት፤ የሀገርን ገጽታ የመገንባት ኃላፊነት ይኑርበት እንጂ፤ የሀገራችንን ውበት ማሳየት፣ የሀገራችንን ቱባ ባሕል እና ብዝኃነታችንን የማሳየት፤ ረጅም ታሪኳን የማሳየት እና በሁሉም ዘርፍ የሀገራችንን ውበት አሳይቶ ቱሪስቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ ማድረግ፤ በሀገር ውስጥም ያለ በውጭም ያለ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው**

መጓጓዝ እንዲችሉ ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል ነው፡፡ እነዚህንና ተጨማሪ የተለያዩ ጉዳዮችንም በመሥራት የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን የማነቃቃት ሥራ በሚገባ መሥራት አለብን ብለን እየሠራን ነው፡፡

**ጥያቄ ፡- ከግል ዘርፉ ጋር በጋራ ለመሥራት ምን ታስባል?**

**ክብርት አምባሳደር ናሲሴ፡-** ያው እንግዲህ የቱሪዝም ዘርፉን ከማሳደግ አንጻር የግል ዘርፉን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ የተለያዩ ማበረታቻዎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ ተገብቷል። የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ ለምሳሌ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄዶ የሚያለማ ባለሃብት የታክስ እፎይታ ጊዜ ይሰጠዋል። ከግንባታ እቃዎች እስከ መገልገያ እቃዎች ደግሞ ከታክስ ነፃ እንዲያስገባ ሁኔታዎች ተመቻችተው ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከተሸከርካሪዎችም ጋር ተያይዞ በተለያየ መልኩ እስከ አሁን በጣም ብዙ የሚባሉ የጉዞ ወኪሎች/ ቱር ኦፕሬተሮች እንዲሁም የሆቴልና የሎጅ ባለቤቶችም በተለያየ ሁኔታ እንደሀገር ተደግፈዋል፡፡ እንደ ሀገር ያለን ማበረታቻ በጣም ብዙ ነው፤ ከማበረታታት አንጻር የበለጠ መጨመር ያለብን ቦታዎችም አሉ።

ለምሳሌ ከተለያዩ እቃዎች ጋር ተያይዞ በይበልጥም እዚህ ከማይገኙ እቃዎች ጋር ተያይዞ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ አዳዲስ ከሚከፈቱ መዳረሻዎች ጋር ተያይዞ፤ ለምሳሌ( የውሃ ስፖርት) እና የመሳሰሉት ጋር ተያይዞ አሠራሮችን ወደ ሥራ ማስገባት ይጠበቅብናል፡፡

ከኮንፍረንስ ቱሪዝም ጋር ተያይዞ አዳዲስ ማበረታቻዎችን አጥንቶ ወደ ሥራ ማስገባት ያስፈልጋል። ያሉትም ማበረታቻዎች ወይም ድጋፎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ፤ የተለያየ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል። ድጋፎቹ ለትክክለኛ ሰው እየደረሱ ነው ወይ? ለትክክለኛው ባለ ሃብት ትክክለኛው ማበረታቻ እየደረሰ ነው ወይ? የሚለውንም ማጥራት ያስፈልጋል።

ከዚህ አንጻር የገንዘብ ሚኒስቴርን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማት ጋር የምንሠራቸው ሥራዎች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ጥሩ በሚባል መልኩ ለግሉ ዘርፍ ድጋፎችን እየሰጠን እንገኛለን፡፡ አሁንም የሚቀሩ፣ የሚያድጉ፣ ብዙ ፍላጎቶች ቢኖሩም፤ እንደሀገር እያየን መጨመር ያለብንን በተለይም የቱሪዝም ሴክተሩን ከማሳደግ አንጻር አዳዲስ የሚባሉ ነገሮችን ማስለመድና ወደ ሀገር ማስገባት አለብን። ከዚህ አንጻር ማስተካከያዎችን እናደርጋለን፡፡

እንግዲህ የግል ዘርፉን/የፕራይቬት ሴክተሩን ከመደገፍ አንጻር ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚሠሩ ሥራዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ የቱሪስት ፍሰት፣ የቱሪስት ልምድ፣ ለአንድ ሀገር ተወዳዳሪነት በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር ከኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ጋር በመሆን በሠራናቸው ሥራዎች የተለያዩ ክለሳዎች ተደርገዋል፤ ከኦን ላይን ቪዛ አሁን ላይ ቪዛ ኦን አራይቫል 122 ለሚሆኑ ሀገራት ክፍት ሆኗል፡፡ ክብርት ሠላማዊት እዚህ በነበሩ ጊዜ ችግሩን በቅርበት ስለሚያውቁት፣ ችግሩን በፍጥነት ከመፍታት አንጻር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

ከጉምሩክ/ከከስተምስ ጋር ተያይዞም የሚነሱ ቅሬታዎች አሉ፤ በተለይም ከድህነታችን ጋር ተያይዞ በተከለከሉ የቱሪስት መገልገያ መሣሪያዎች ላይ የተለያዩ ቅሬታዎች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህን ቅሬታዎች ጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በቅርበት በመነጋገር ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

አሁን ባለው አሠራር ችግሮች ሲያጋጥሙ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በቅርበት መነጋገር የሚያስችለው አሠራር ተፈጥሯል፡፡ ነገር ግን ይህ አሠራር ወደፊት እኛንም ሳያሳትፍ የሚሳለጥበትና ቱሪስቱ በቀላሉ ይዞ ገብቶ ይዞ የሚወጣበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ ነው፡፡

ለምሳሌ ካጋጠሙ ችግሮች አንዱ ከጎረቤት አገር በድንበር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ጉዳይ ነው። በአብዛኛው በድንበር የሚገቡት ተሽከርካሪዎች አስንብኝተው መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ጉምሩክ ኮሚሽን አንድ የገጠመው ችግር ግን እነዚህ ተሽከርካሪዎች በብዛት የማይወጡ መሆኑ ነው፡፡ ወይ ይሸጣሉ፤ ወይ ሀገር ውስጥ ተቀምጠው ለተለያየ ጉዳይ ይውላሉ፡፡ ስለዚህ ይህንን ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ አቁሞት ነበር፡፡

ነገር ግን አሁን አሠራር ተፈጥሮ ተጠያቂነት ባለው መልኩ የጉዞ ወኪሎች /ወኪሎች/ ቱር ኦፕሬተሮች ኃላፊነት እየወሰዱ ተሽከርካሪዎች በቀላሉ ገብተው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ልክ እንደዚህ አይነት አሠራሮችን እየፈጠርን ሀገርንም ለድህነትና ለአደጋ የሚያጋልጡ፤ ኢኮኖሚያችን በተለያየ መልኩ ማግኘት ያለበትን ጥቅም የሚጎዱ፣ ችግሮች ተቀርፈው የቱሪስቶች ፍሰቱና ልምዱ የተሳለጠ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**ጥያቄ ፡- መጨመር የሚፈልጉት ሀሳብ ካለ?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** በእርግጥ ሁሉንም ጉዳይ ነካክተናል፤ ያልነካካነው ነገር የለም፡፡ ምናልባት ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት፤ አንደኛ ለግሉ ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ዋናው ተዋናይ የግሉ ዘርፍ ነው፡፡ ስለዚህ የግሉ ዘርፍ ጋር ቀርበን በሚያስፈልጋቸው መልኩ ለመደገፍ ጥረት እናደርጋለን። በማበረታቻ ፣ በሕግ ማዕቀፍ ወዘተ... ፡፡

የግሉም ዘርፍ ደግሞ አሁን ባሉ እንቅስቃሴዎች ተነቃቅቶ ሊሠራ ይገባል፡፡ አሁን እንደሚታወቀው ቱሪዝም ቱሪዝም የሚል መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ የግሉ ዘርፍ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ኢንቨስት ማድረግ እና የሀገራችንን ውበት ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ከአደራ ጭምር ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡ ይህ እንግዲህ ወኪሎች/ቱር ኦፕሬተሮች ሌሎችንም ይጨምራል፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ ዘርፉ ለሕገ- ወጥ ተዋናዮች የተጋለጠ ነው፡፡ የተለያዩ ሕገ-ወጥ ኦፕሬተሮችን ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሥራ ውስጥ የተሠማሩ ባለሃብቶች እነዚህን ሕገ-ወጥ ተዋናይን በማጋለጥ እና ወደ መሥመር እንዲገቡ በማድረግ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የማስተላልፈው፤ ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደተቋም ሀገርን የማስተዋወቅ ኃላፊነት፣ የሀገርን ውበት የማሳየት፤ የሀገርን ገጽታ የመገንባት ኃላፊነት ይኑርበት እንጂ፤ የሀገራችንን ውበት ማሳየት፣ የሀገራችንን ቱባ ባሕል እና ብዝኃነታችንን የማሳየት፤ ረጅም ታሪኳን የማሳየት እና በሁሉም ዘርፍ የሀገራችንን ውበት አሳይቶ ቱሪስቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ ማድረግ፤ በሀገር ውስጥም ያለ በውጭም ያለ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡

ስለዚህ በሀገራችን በጎ በጎ ነገሮች ላይ እና የበለጠ የሀገራችንን ገጽታ በመገንባት ላይ ብናተኩር፣ ከስልካችን ጨምሮ የያዝናቸውን ዲጂታል አፕሊኬሽኖች ለመልካም ነገሮች ብንጠቀም፤ በተለይ የሀገራችንን ገጽታ የሚገነቡ፤ በኢኮኖሚ የበለጠ ሀገራችንን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ወደ ሀገራችን ቱሪስቶችን መሳብ የሚችሉ ነገሮች ላይ ትኩረት እንድናደርግ ከአደራ ጭምር ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

**ጥያቄ፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ፡፡**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

# ማህደረ ጤና

# በፎሊክ አሲድ እጥረት የሚከሰት “ የነርቭ ዘንግ ክፍተት” ን ለመከላከል

**እየሩስ ተስፋዬ**

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በተሠራው ጥናት ከአንድ ሺህ ህፃናት ውስጥ 131 ሕፃናት የነርቭ ዘንግ ክፍተት አጋጥሟቸዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም በተወሰኑ ተቋማት ከተወለዱ አስር ሺህ ህፃናት መካከል 126ቱ ክፍተቱ እንዳለባቸው ከጤና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚሁ መረጃ መሠረት፣ በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ደግሞ ከተወለዱ አስር ሺ ሕፃናት፤ 108 ሕፃናት ተገኝተዋል፡፡

እንደ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ ከተወለዱ አስር ሺህ ህፃናት ከአምስት በመቶ የበለጡት የነርቭ ዘንግ ከተገኘባቸው ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መደረሱን፤ ወይም ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ከዚህ ቁጥር በመነሳት ኢትዮጵያም የችግሩ ተጋላጭ ከሆኑት ሀገራት መካከል ተጠቃሽ መሆኗን ለመረዳት ቀላል ነው፡፡

ዶክተር ታደሰ ጉሬ በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህጸን እና የጽንስ ስፔሻሊስት ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው ገለፃ የነርቭ ዘንግ ክፍተት (Neural Tube Defect) (NTD) አንድ ሕፃን ገና በእናቱ ማሕጸን እንደተፀነሰ በሦስተኛው ሳምንት፣ ወይም ከ21ኛ እስከ 26ተኛ ባሉት ቀናት ውስጥ የነርቭ ዘንግ መዘጋት ይኖርበታል። ይህ ሳይሆን ሲቀር ‹‹የነርቭ ዘንግ ክፍተት ተፈጥሯል።›› በዚህም ሳቢያ ከላይኛው የአእምሮ ክፍል እስከ ታችኛው ሕብለ ሰረሰር ድረስ የነርቭ ዘንግና መሸፈኛው ላይ የአፈጣጠር ችግር በታየባቸው ጨቅላ ሕፃናት ላይ የጭንቅላት መጠን ገዝፎ መታየት እና ከጀርባቸው ያበጠ ነገር ይስተዋልባቸዋል፡፡

የነርቭ ዘንግ ክፍተት በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚከሰተው የፎሊክ አሲድ እጥረት እንደሆነ ዶክተር ታደሰ ያብራራሉ። ፎሊክ አሲድ በምንመገባቸው ምግቦች አማካኝነት ይገኛል፡፡ ለአብነትም ካሮት፣ ማንጎ ፓፓያ፣ ጎመን እና ሌሎች ቅጣቅጠሎች ውስጥ ይገኛል፡፡ የአንዲት ሴት ፎሊክ አሲድ በሰውነቷ ውስጥ በቂ ሳይሆን ሲገኝ የሕፃኑ የሰውነት ግንባታ ሂደትን በማስተጓጎል የነርቩ ዘንግ ሳይዘጋ ይቀራል፡፡

ሌላኛው ምክንያት ደግሞ አንዲት እናት የሚጥል በሽታ ካለባት እና ለዛ ህመም መድሃኒት የምትወስድ ከሆነ ፎሊክ አሲዱ እንዳይሠራ በማስተጓጎል ክፍተቱ እንዳይዘጋ ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ የስኳር ህመምተኛ የሆኑ እናቶች እርግዝና ሲከሰት የነርቭ ዘንግ እንዳይዘጋ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩን ዶክተር ታደሰ ይናገራሉ፡፡

አልፎ አልፎ ከአፈጣጠር ጋር በተያያዘ በሰውነታችን ውስጥ ያለው ኢንዛይም ፎሊክ አሲድን የመቀየር ኃይል አለው፡፡ ፎሊክ አሲድ ቢወሰድም እጥረቱን መቀነስ አይቻላቸውም፡፡ ይህም ለክፍተቱ አጋልጦ የሚሠጥ ይሆናል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ችግሩ በፎሊክ አሲድ እጥረት ምክንያት የሚከሰት እንደሆነ አጽንኦት በመስጠት ያስረዳሉ፡፡

ዶክተር ታደሰ እንደሚያብራሩት አንዲት እናት ከማርገዟ በፊት የቅድመ እርግዝና ክትትል (እርግዝና ሳይከሰት በፊት) በማድረግ ከማርገዟ አንድ ወር ቀደም ብላ ፎሊክ አሲድ ብትወስድ ይመረጣል፡፡ እርግዝና ከተከሰተ በኋላ ደግሞ እስከ ሦስተኛ ወር ፎሊክ አሲድ በመውሰድ የነርቭ ዘንግ ክፍተትን መቀነስ ይቻላል። እንዲሁም የተለያዩ በሽታዎች ያሉባቸው እናቶች እርግዝና ከመፈጠሩ በፊት ክትትል እና ህክምናቸውን በማድረግ መከላከል ያስችላቸዋል፡፡ በተለይም የስኳር በሽታ ያለባቸው እናቶች የስኳር መጠናቸውን በመቆጣጠር ከነርቭ ዘንግ ክፍተት ባሻገር ሌሎች በሽታዎችንም ለመከላከል እንደሚረዳቸው ይናገራሉ።

በእኛ ሀገር ያሉ አብዛኛዎቹ እናቶች የእርግዝና



ክትትል ማድረግ የሚጀምሩት ነፍሰጡር መሆናቸውን ካረጋገጡ ከሁለት እና ከዛ በላይ ባሉት ወራት እንደሆነ የታዘቡት የማህጸን እና የጽንስ ስፔሻሊስት ዶክተር ታደሰ፣ ክፍተቱ ከተፈጠረ በኋላ ፎሊክ አሲዱን መውሰድ ክፍተቱን የሚዘጋ ባለመሆኑ ጠቀሜታ የለውም ይላሉ፡፡ ስለዚህም አንድ ባል እና ሚስት ልጅ መውለድ ሲፈልጉ ሴቲቱ ከማርገዟ በፊት ‹‹ምን ማድረግ አለብኝ?›› በማለት ከህክምና ባለሙያ ጋር መወያየት እና መነጋገር ይኖርባታል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊ ምርመራዎችን በማድረግ መቆጣጠር እና ሊታከም የሚገባው ችግር ካለ እነርሱን በመታከም፤ ብሎም ፎሊክ አሲድ በውሰድ ክፍተቱን መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

የህክምና አሰጣጡን በተመለከተ ዶክተር ታደሰ እንደሚመክሩት ከሆነ፣ ምንም እንኳን የነርቭ ዘንግ ክፍተቱ ከተከሰተ በኋላ የሚሰጥ ህክምና ይኑር እንጂ ከሁሉም በላይ የሚመከረው ግን ክፍተቱ ሳይከሰት በፊት አስቀድሞ መከላከል ነው፡፡ ለዚህም ፎሊክ አሲድ በምንመገባቸው ምግቦች ውስጥ ከመገኘቱ ባሻገር የሁሉንም አቅም በሚፈቅድ በርካሽ ዋጋ የቀረበ ሲሆን፤ አስቀድሞ በመውሰድ መከላከል እንደሚቻል ዶክተር ታደሰ ይናገራሉ፡፡

ክፍተቱ ከተከሰተ በኋላም ልዩነታቸውን እና ዓይነታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ህክምናውን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በተለይም ወደ ታችኛው የሰውነት ክፍል ነርቩን የከበበው ወደ ውጭ ካልወጣ ከተወለደ በኋላ በቀላሉ መዘጋት እንደሚቻል የሚናገሩት ዶክተር ታደሰ፣ በእኛ ሀገር ደረጃ ብዙ ኒሮሰርጅኖች ያሉ ሲሆን እነርሱም ይህንን መዝጋት ይቻላቸዋል ይላሉ፡፡ ባደጉት ሀገራት ደግሞ ጨቅላ ሕፃናቱ በእናታቸው ሆድ ውስጥ እያሉ በአምስት እና ስድስተኛ ወራቸው ላይ የጀርባ ዘንግ ክፍተት መኖሩ ከተረጋገጠ ሆድ ውስጥ እያለ የመዘጋት ዕድል አለው። በእኛ ሀገር ግን ሆድ ውስጥ እያለ የሚሰጠው ህክምና እንዳልተጀመረ ያስረዳሉ፡፡

ዶክተር ታደሰ እንደሚሰጡት ማብራሪያ፤ ከነክፍተቱ ለሚወለዱ ልጆች ሕክምናው ሀገር ውስጥም፣ ከሀገር ውጭም ያለ ቢሆንም ከህክምናው በኋላ ኢንፌክሽን ሊከሰት ይችላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከተዘጋ በኋላ ነርቭ የከበበው ወደ ውጭ ከወጣ እና ተመልሶ እንዲዘጋ ከተደረገ ለተለያዩ ኢንፌክሽኖች የመጋለጥ ዕድላቸው ሰፊ እንደሆነ የሚገልጹት ዶክተር ታደሰ፤ በዚህም ምክንያት በጭንቅላት ውስጥ ውሃ መጠራቀም፣ እግራቸውን አለመቆጣጠር (አለመታዘዝ)፣ ሽንት እና ሰገራ ለመቆጣጠር መቸገርና

**አልፎ አልፎ ከአፈጣጠር ጋር በተያያዘ በሰውነታችን ውስጥ ያለው ኢንዛይም ፎሊክ አሲድን የመቀየር ኃይል አለው**

የመሳሰሉት ያጋጥሟቸዋል። ለአእምሮ ዕድገት ውስንነት የመጋለጥ ዕድላቸውም ሰፊ ነው፡፡

ከኬንያ፣ ማሊ፣ ሞዛምቢክ እና ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ክፍተቱ ያለባቸው ጨቅላ ሕፃናት ቁጥር በእኛ ሀገር ከፍ ብሎ ይታያል ያሉት ዶክተር ታደሰ፣ ባደጉት ሀገራት ጨው፣ ዱቄት እና የመሳሰሉት ምርቶች ላይ ፎሊክ አሲድ እንዲጨመሩ አስገዳጅ ሕግ በመውጣቱ ቁጥሩ እንዲቀንስ አግዟቸዋል። በእኛ ሀገር ደረጃ ፎሊክ አሲድ ለመጠቀም (Folic Acid Fortification) አስገዳጅ መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ እንዲሆን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ እንዲሁም ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የሚሠራበት ቻምፐስ ድርጅት እና ሌሎች ድርጅቶች ፎሊክ አሲድን በጨው፣ ዱቄት እና የመሳሰሉት ላይ እንዲጨመር ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። መመሪያው በሀገራችን ተግባራዊ ሲሆን፣ የታማሚው ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንስ እንደሚችል ተስፋ ማድረጋቸውንም ያስረዳሉ።

“አንዳንድ ሰዎች ስለነርቭ ዘንግ ክፍተት በፊት እንዳልነበር ወይም አዲስ ነገር እንደሆነ ሲያወሩ ይደመጣል፡፡ የእውነት አልነበረም ወይ?” ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ዶክተር ታደሰ “የነርቭ ዘንግ ክፍተት አሁን የተከሰተ ነገር አይደለም” የሚል ምላሽን ይሰጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ የደረሰበትን ደረጃ የሚያመላክቱ ጥናቶች ግን አልነበሩም፡፡ ሌላው ከዚህ በፊት አብዛኞቹ እናቶች የነርቭ ዘንግ ክፍተት ያለባቸው ልጆች ሲወልዱ እንደ ፈጣሪ ቁጣ ስለሚያዩት ልጆቻቸውን ይደብቋቸው እንደነበር በማውሳት፤ የፈጣሪ ቁጣ እና እርግማን ሳይሆን ከፎሊክ አሲድ እጥረት የሚመጣ እንደሆነ ሕብረተሰቡን ማስገንዘብ እንደሚገባም ይገልፃሉ፡፡

ዶክተር ታደሰ ጨምረው እንዳስረዱት፤ ጤነኛ ልጅ ማግኘት እናትም ልጅም ጤናማ እንዲሆኑ ያግዛል። ስለዚህም ጤነኛ እናት እና ልጅ እንዲኖሩ ከተፈለገ ባደጉት ሀገራት የተለመደውን የቅድመ እርግዝና ምርመራ በእኛም ሀገር ማስፋፋት ይጠበቃል። እርግዝና ከተከሰተ በኋላም ቢሆንም የእርግዝና ክትትል በማድረግ እናት እና ልጅ ያሉበትን ደረጃ መከታተል ይገባል፡፡ ቀጥሎም ህክምና ተቋማት ሄዶ በመውለድ የእናቶችን ሞት ከመቀነስ ባሻገር የልጆችን ጤንነት ለመጠበቅ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

ቅድስት ወልደሰንበት በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ሥራ አስፈጻሚ ክፍል ውስጥ የመከላከል ተኮር ዴስክ ኃላፊ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በግልጽ የሚታወቅ መንስኤ ባይኖረውም ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ግን 75 በመቶ የሚከሰተው የነርቭ ዘንግ ክፍተት በፎሊክ አሲድ እጥረት እንደሆነ ነው የሚናገሩት፡፡ ለተጓዳኝ በሽታዎች የሚወሰዱ መድሃኒቶችም ድርሻቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ ለሚጥል ሕመም የሚወሰድ መድሃኒትን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

እንደ ጤና ሚኒስቴር፣ ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት መከላከል ላይ መሠራት እንዳለበት የሚታመን ሲሆን፤ እንደ ሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ ክፍልም መከላከል ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን እየተሠሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ የነርቭ ዘንግ ክፍተትን ለመቀነስ አስቀድሞ መከላከል ላይ ቢሠራ ችግሩን በሚገባ መቀነስ እንደሚቻልም ጨምረው ያስረዳሉ፡፡

አንዲት እናት ከመጸነሷ በፊት አንድ ወር ቀደም ብላ እንዲሁም እስከ ሦስት ወር ድረስ የፎሊክ አሲድ እንክብል በመውሰድ የሰውነት ክብደትን (መጨመርም ሆነ መቀነስ) ማስተካከል እና የተመጣጠነ ምግብ መውሰድ አለባት ያሉት ኃላፊዋ፣ በተለይም ምግብን ማስተካል፣ ከሁሉም የምግብ አይነቶች አመሳጥሮ እና አመጣጥኖ መመገብ ይገባል፡፡ በፎሊክ አሲድ የበለጸጉ፣ እንደ ጎመን ያሉ ደማቅ አረንጓዴ ምግቦችን፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፤ ከጥራጥሬ ደግሞ እንደ ምስር፣ ባቄላ እና አተር ያሉትን መመገብ ችግሩን ለመከላከል እንደሚረዳ ይመክራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር ምግብን የማበልጸግ መመሪያ (Food Fortification) የተዘጋጀ ሲሆን፤ በመመሪያው መሠረት በምንመገበው ዘይት እና ዱቄት ላይ ጥቃቅን ማዕድናትን ጨምሮ ሌሎች ምግቦችን ማበልጸግ እንደሚገባ አስገዳጅ መመሪያ ተዘጋጅቶ መፅደቁን ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም፣ ከቫይታሚን ኤ እና ቫይታሚን ዲ በሚመረቱ ዘይቶች ላይ፤ ፎሊክ አሲድን ደግሞ በዱቄት ላይ እንዲጨመር የሚያስገድድ ሕግ መውጣቱ ችግሩን ሊቀንስ እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

በመመሪያ ደረጃ አሁን የተዘጋጀ ሲሆን፣ በቀጣይ ደግሞ በሁሉም የጤና ተቋማት “እንዴት ልንሰጥ እንችላለን” የሚለውን እየሠራንበት ነው ያሉት ቅድስት፤ አሁን ላይ በቤተሰብ ደረጃ ታቅዶ የተገኘ እርግዝና ለእናትም፣ ለልጅም፣ ለሀገርም ውጤታማነት ድርሻው ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

የዴስክ ኃላፊዋ ቅድስት እንደሚያብራሩት ከሆነም፤ የነርቭ ዘንግ ክፍተት ላለባቸው ልጆች የሚሰጥ ህክምና አሁን ካለው ፍላጎት አንፃር በቂ ነው ብሎ ደፍሮ ለመናገር ያዳግታል፡፡ በሀገር ኢኮኖሚ፣ በጤና እና በሥነ ልቦና ላይ የሚያደርሰውን ችግር በመገንዘብ መከላከሉ ላይ እና የሰዎችን ግንዛቤ ከፍ የማድረግ ሥራ ከሁሉም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ፣ እንደ ጤና ሚኒስቴር ችግሩ አሳሳቢ እየሆነ የመጣ መሆኑን በመረዳት ሕብረተሰቡ ስለነርቭ ዘንግ ክፍተት ምንነት እና እንዴት መከላከል እንደሚቻል የግንዛቤ ሥራ በሰፊው ለመሥራት ታስቧል፡፡ እንዲሁም ከዚህ በፊት ጥናት ተደርጎባቸው ቁጥሩ ከፍ ወዳለባቸው ክልሎች በመዘዋወር የግንዛቤ ማስጨበጥና መሰል ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

# ከጥሪው ባሻገር ...

**ታምራት ተስፋዬ**

ለኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ የሕልውናቸው መሠረት ናት። እሷ ወድቃ እነርሱ አይቆሙም። እሷ እያዘነች እነሱ አይደሰቱምም። እሷን ረስተው እነርሱ አይታወሱም። እሷ ከሌለች የእነርሱ በሕይወት መቆየት ትርጉም አልባ ነው። የሚኖሩት በእሷ ተከብሮ መቆየት ውስጥ ነው። እሷ ሰላሟን አጥታ ሕሊናቸው አትረጋጋም፡፡ ኢትዮጵያ ጎድሎባት እነርሱ አይሞላላቸውም፡፡

እሷ ዝቅ ብላ እነርሱ አይገዝፉም፡፡ ያለ ኢትዮጵያ የሚበሉት አይጣፍጣቸውም፡፡ የሚጠጡት አያረካቸውም። ልባቸውን እንጂ ጀርባቸው አይሰጧትም፡፡ እድገቷን እንጂ ዝቅታዋን፣ ደስታዋን እንጂ ኀዘኗን፣ ክብራን እንጂ ውርደቷን ፈፅሞ አይመኙም፡፡

ሀገር ውስጥ እንዳለው ሁሉ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊም ከምንም በላይ የሀገራቸውን ፍቅር በልባቸው ይዘው የሚኳትንና በአካል ቢርቁም በመንፈስ ሁሌም ሀገራቸው ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ሀገራቸውን የሚወድ፣ ሀገራቸው ተሻሽላና አድጋ መመልከትን የሚፈልግ፣ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትኖር ከልብ የሚመኙና ለዚያም የሚታገሉ ናቸው።

ይሁንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተለያይቶ እንዲያስብና ተግባብቶ እንዳይኖር ፅኑ ፍላጎት ያላቸው መንደርተኞች አሉ፡፡ የፍላጎታቸውም የሚመኙትን ሥልጣን ለመቆናጠጥ የሕዝብ ማሰቢያ ላይ የበላይነትና የበታችነት ወላፈን በመዝራት ስሜት በማነሳሳት ንዴት ማስታጠቅና እንዳሻቸው ሕዝቡን እየዘረፉ ሀብት ማከማቸት ነው።

በጎሳና በጎጥ ተደራጅተው በሀገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ፀብ በመዝራት ጥላቻን በመስበክ ማበጣበጥና የሕዝቡን ሠላም የሚያደፈርሱ ዛሬም መንደራዊ ሹማምንቶች፣ የሀገሬውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ዲያስፖራውንም ከእናት ሀገሩ ለማፋታት ሌት ተቀን የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ በተደጋጋሚ ታዝበናል፡፡

ይሁንና ዲያስፖራው የዞፋን ጥማታቸውን ለማርካት ፀብን እየዘሩ ጥላቻን እያጎረሱ በሚኖሩ መንደርተኞች እንቶ ፈንቶ ተረብሾ ጨለማ ውስጥ መዳከር ምርጫው እንዳልሆነ እያስመሰከረ ይገኛል። ከምክንያታዊነት ይልቅ ለስሜታዊነት የተጋለጡ ጥቂቶች እንዳሉ ሆነው አብዛኛው ዲያስፖራ አንድ ከማድረግ ይልቅ የሚነጣጥል፤ መሰብሰብን ትቶ የሚበትን፣ ከማዋሓድ ይልቅ የሚለያይ አስተሳሰብን ማራመድ ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደሌለው ጠንቅቆ በመረዳት ሀገሩን ከፈተና ወደ ልዕልና ከፍ ለማድረግ ከሁሉም በላይ በሀገር ባለቤትነት ስሜት እጅ ለእጅ በመያያዝ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡

በተለይ ከለውጡ ወዲህ ዲያስፖራው የለውጥና የሀገር ባለቤትነት ስሜቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ በመላው ዓለም የሚገኙ ዲያስፖራዎች ለእናት ሀገራችን ለኢትዮጵያ አናንስም፣ ባለን ሁሉ እንቆምላታለን ብለው ሲነሱም ታይተዋል፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ ላይ የተከፈቱ ሴራዎችን ለመቀልበስ ዓለም እውነቱን እንዲረዳ ድምፃቸውን በማሰማት ረገድ ታላቅ ገድልን መፈፀማቸው መቼም የማይዘነጋ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች በመወከል የሀገራቸውን መብትና ጥቅም ከመከላከልና ከማስከበር ባለፈ በሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችን ለማቃለል የሚችሉና በጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ናቸው፡፡ ሀገር ግጭት ውስጥ በቆየችባቸው ጊዜያት ለመከላከያ ሠራዊት፣ ለተፈናቀሉ ወገኖች ለመደገፍና በተለይ ‹‹በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል›› ለተባለው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ያደረገው ሁለንተናዊ ድጋፍ ለዚህ ምስክር የሚሆን ነው፡፡

መንግሥትም ለዚህ የዲያስፖራው ሁለንተናዊ አስተዋፅዖ ክብርና አድናቆቱን ከመግለፅ ባለፈ ከጋራ ሀገር እድገት ከዲያስፖራው ጋር ይበልጥ ለመቀራረብ የተለያዩ ጥሪዎችን ሲያቀርብ መቆየቱም የሚታወስ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) በ2014 ዓ.ም "የአንድ ሚሊዮን ዲያስፖራ የሀገር ቤት ጥሪ" እና "ከኢድ እስከ ኢድ ወደ ሀገር ቤት ጥሪ" ማድረጋቸውን ተከትሎም በርካቶች ወደ ሀገሪቱ መምጣታቸው የሚዘነጋ አይደለም፡፡

የዚሁ ምዕራፍ ቀጣይ በሆነ መልኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ታኅሣሥ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ለሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ወደ ሀገር ቤት እንደሚመጡ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል። ይህ የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ጥሪ ዲያስፖራው ሀገሩን በማወቅና ከማንነቱ ጋር በመተሳሰር በሀገሩ ጉዳይ ላይ እንዲሳተፍ የማድረግ ዓላማን ያነገበ የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ጥሪ ዓላማ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸው ተፈጥሮ ታሪክና ባሕል በማወቅ ከሕዝባቸው ጋር ያለውን ትስስር የማጠናከርና በቀጣይ በሀገራቸው ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው ።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ መሠረት "Back to your Origin" በሚል መሪ ሀሳብ የዲያስፖራ አባላቱ ከታኅሣሥ 20 ቀን 2016 እስከ መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም በሦስት ዙር ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ሥራውን የሚያስተባብር ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ የተለያዩ ሥራዎችን በመከናወን ላይ መሆናቸው ታውቃል፡፡

የመጀመሪያ ዙር ከታኅሣሥ 20 እስከ ጥር 20/2016 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ ሲሆን 'Connect to your culture' በሚል መሪ ሃሳብ ይከናወናል። በዚህ ሁነት ዲያስፖራዎቹ ባሕላቸውን እንዲያውቁና እንዲያስታውሱ የሚያስችላቸው መርሐ ግብሮች ተዘጋጅቷል፡፡

ሁለተኛው ዙር ደግሞ 'Connect to your history' በሚል መሪ ሀሳብ በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከሚካሄደው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ጀምሮ እስከ ክረምት መግቢያ የሚካሄድ ነው። ይህ ዝግጅት የዲያስፖራ አባላቱ በባሕል፣ በቋንቋ እና በሃይማኖት ያሉ ታሪኮችን እንዲያውቁ ማስቻልን ግቡ አድርጓል።

ሦስተኛው ዙር ደግሞ 'Leave your legacy' በሚል ከ2016 ዓ.ም የክረምት መግቢያ ጀምሮ እስከ መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም ይከናወናል። በዚህኛው ዙር ሕጻናትን ማስተማር፣ ችግኝ መትከልና ሌሎች ሰፋፊ የበጎ ፈቃድ ተግባራት በማከናወን በሀገራቸው አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ማድረግን ዋንኛ ዓላማ አድርጓል።

በአሁን ወቅትም ጥሪውን ተቀብለው በመላው ዓለም የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ወደ ሀገር ቤት ገብተዋል፡፡ በመግባትም ላይ ናቸው፡፡ ከኤርፖርት አንስቶ ለዲያስፖራው ጥሩ አቀባበልና መስተንግዶ እየተደረገና እየተሰጠ ስለመሆኑም ተመልክተናል፡፡

ወቅቱ የበዓል ሰሞን ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት የሚስተዋልበት እንደመሆኑም በተለይ ዲያስፖራው የሚሳተፍባቸው የተለያዩ ፓኬጆችና መስተጋብሮች ተመቻችተዋል። እነዚህ ሁነቶቹም ዲያስፖራው ሀገሩ፣ እምነት፣ ባሕሉን ይበልጥ እንዲያውቅ፣ እንዲወድና እንዲያጣጥም ከማድረግ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በተለይ የቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡

እንደሚታወቀው፣ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት የቱሪዝም ዘርፉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለማድረግ የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ኅብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ተጠቃሚነትን ለማጎልበት ብርቱ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

> **ዲያስፖራው ኢትዮጵያ ውስጥ መሠረቱ የማይነቃነቅ አሻራ እንዲያሳርፉ በሀገሪቱ ምን አይነት አቅምና አማራጭ አለ የሚለው ታሳቢ ባደረገ መልኩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስተዋወቅ ረገድ ሰፊ ሥራዎችን መሥራትም ግድ ይላል፡፡ የኢንቨስትመንት ፎረም ማካሄድ ይገባል**

የሀገሪቱን የቱሪስት መዳረሻነት ለማሳደግ እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት መካከል የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ይገኝበታል። በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ቀደም ሲል ትኩረት ያልተሰጣቸው ቦታዎችን በመምረጥም የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ነው፡፡ በዚህም ትኩረት ተነፍጎት የቆየው የሀገሪቷን የተፈጥሮ ቱሪዝም ሀብት የማልማት ሥራ በጎርጎራ፣ በኮይሻና በወንጪ አካባቢዎች በመከናወን ላይ ይገኛል።

የእነዚህ እና ሌሎች ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ታዲያ የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ አቅም ይበልጥ በማጎልበት ከዘርፉ የሚገኘውንም ጥቅም ከፍ ለማድረግ ሁለንተናዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ ወደ ሀገሩ ለመጣው ዲያስፖራ ማኅበረሰብ ተጨማሪ የጉብኝት አማራጭ እንደሚሆኑም አይጠራጥርም፡፡

ይሁንና የአገሪቱ የቱሪዝም ተስፋ እንዲሰምር የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን ከመፍጠር ባሻገር የዘርፉን እንቅስቃሴ ሠላማዊ መንገድ ላይ ማራመድ የግድ እንደሚል መዘንጋት አያስፈልግም። የዲያስፖራውን ጥሪውን ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት በመትመሙ ምክንያት ዓይናቸውን የሚቀላ አይጠፉም በዚህ ረገድም ሰፊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያም ይህን ወርቃማ እድል በአግባቡ ልትጠቀምበት ይገባል፡፡ የዲያስፖራውን አቅም በአግባቡ ለመጠቀም ትኩረት የሚሹና ቀደም ሲል ግልፅ ድክመት ሆነው የሚስተዋሉ ጉዳዮችን በመለየት ለመፍትሔው አስቀድሞ መሥራት የግድ ነው፡፡

ከሁሉ በላይ ዲያስፖራው ገንዘቡን፣ ዕውቀቱንና ልምዱን አቀናጅቶ ሀገሩን የሚደግፍበት መደላድል እንዲፈጠር፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከወትሮው በተለይ ተገቢውን ክብካቤና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም አገልግሎት አሰጣጣቸውን ይበልጥ ማቀላጠፍ ይጠበቅባቸዋል።

በተለይም ዲያስፖራው በሚወዳት ሀገሩ መዋዕለ ንዋዩን ፈሰስ ለማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ እንቅፋቶች ሳይገጥሙት፣ በተቀላጠፈ መልኩ ለሚጠይቀው ጥያቄና ለሚፈልገውም ምቹ አማራጭና ከባቢን ፈጣን ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

ዲያስፖራው ኢትዮጵያ ውስጥ መሠረቱ የማይነቃነቅ አሻራ እንዲያሳርፉ በሀገሪቱ ምን አይነት አቅምና አማራጭ አለ የሚለው ታሳቢ ባደረገ መልኩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስተዋወቅ ረገድ ሰፊ ሥራዎችን መሥራትም ግድ ይላል፡፡ የኢንቨስትመንት ፎረም ማካሄድ ይገባል፡፡

ከዚህ ባሻገር ልዩ ትኩረት ሊሠጠው የሚገባ የቤት ሥራም አለ፡፡ ይህም የጥቁር ገበያ ነው። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ወደ ኢትዮጵያ በመደበኛ መልክ እየገባ ያለው ገንዘብ በጣም በዝቅተኛ መጠን ነው። ከአንድ ሦስተኛው የማይበልጥ ነው፡፡ የዚህ አንደኛ እና ዋነኛ ምክንያት ጥቁር ገበያ ወይንም ብላክ ማርኬት ነው፡፡

ኢትዮጵያም ጥቁሩን ሰንሰለት መበጠስ አለመቻሏ የዲያስፖራ ልጆችን አቅም መጠቀም ከልክሏታል። ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ገቢ አሳጥቷታል። ለአብነት ከግብፅና ከናይጄሪያ ገቢ አንፃር ብንመለከተው አንድ አራተኛ እንኳን አይሞላም። ሀገሪቱ ጥቁሩን ሰንሰለት መበጠስ ብትችል እስከ 12 ቢሊየን ዶላር ማግኘት እንደሚቻላትም ጥናቶች ይመሰክራሉ፡፡፡

በእርግጥ ይህ ችግር በተለያዩ መድረኮች ይነሳል። ይሁንና መፍትሔ በመስጠት ረገድ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ማከናውን የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሔ ማስቀመጥም የግድ ይላል፡፡ በተለይም ከአጭር ጊዜ አንፃር ዲያስፖራውም ሆነ ባንኮች ከባድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይሰማኛል፡፡

እንደሚታወቀው በርካታ ሀገራት የተቀየሩት ለእድገት የበቁት ዲያስፖራዎቻቸው በከፈሉት ዋጋ ነው፡፡ በመሆኑም ዲያስፖራው በተለይ በአሁን ወቅት ዋጋ በመክፈል ገበያው እስኪረጋጋ ልዩነቱን በመተው በባለቤትነት፣ በኃላፊነት፣ ዋጋ በመክፈልና ‹‹ለሀገሬ ነው የማደርገው›› በሚል ስሜት በመደበኛው መንገድ ብቻ ገንዘቡን መላክ ይኖርበታል፡፡

የፋይናንስ ተቋማትም ዲያስፖራው ገንዘብ በሚልክበት ወቅት በአነስተኛ የአገልግሎት ክፍያ አማራጭን ማስተዋወቅና የመላኪያው ወጪ የሚጋሩበት ሁኔታ ማሰብ እንዲሁም በመደበኛ መልኩ የሚልኩ ዲያስፖራዎችን ማበረታታት ፍቱን አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው። ሽልማት መስጠትና የእውቅና መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀት የግድ ይላል። ይህ በማድረግ ተጨማሪ የውጭ ምንዛበ ማግኘት ይችላል፡፡ ከረጅም ጊዜ መፍትሔነት አንፃር ጥቁር እና ነጭ የሚባል ገበያ ስለማጥፋት መሥራት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከጥሪው ባሻገር እነዚህ ዐበይት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

# የትዳር አጋርን ነፍስ የነጠቀው የንዋይ ጥማት

አስመረት ብስራት



ተወልደው ያደጉት በአርሲ ዞን አርሲ ነገሌ ከተማ ነው። ለዓመታት እዛው ከተማ ነዋሪ የሆኑት የ45 ዓመቱ አቶ ከተማ አበበ ተወልደው ባደጉባት ከተማ በልጅነታቸው ተድረው ለዓመታት ኖረዋል። እኚህ ግለሰብ በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ሰው ናቸው ። ከልጅነታቸው ጀምሮ ሱቅ በመላላክ ስላደጉ ለንግድ ሥራ ቅርብ ነበሩ፡፡ በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ የሚያውቁትም ሥራ ንግድ ብቻ ነው። እሱም ይሳካላቸው ነበር።

ከልጅነት እስከ እውቀት በያዙት ሥራ በራሳቸው መንገድ ስኬት ላይ ደርሻለሁ ብለው ያስባሉ። በሚሠሩት ሥራ ጥሪት አፍርተው ቤተሰብ መስርተውም ይኖሩ ነበር። አቶ ከተማ ከዚህ ትዳር በፊት በትዳር ሕይወት የነበሩ ቢሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች የትዳር ግንኙነታቸው ሳይሳካ ቀርቶ በፍች ተደምደሞም ነበር።

ሕይወት ሁለተኛ እድል ስትሰጣቸውም ዓይናቸውን ሳያሹ የተቀበሉት እኚህ ሰው የመጀመሪያ ትዳራቸውን ካጡ በኋላ ለብቻቸው ለተወሰነ ጊዜያት ኖረው ነበር። ቤት ንብረት ይዘው እንደ አባወራ ይኖሩ የነበሩት እኚህ ሰው ዳግም እንደ ወንደላጤ ምግብ ፍለጋ እዚህና እዚያ መርገጥ አማረራቸው። ልብሳቸው ታጥቦ ምግባቸው ተሠርቶ ይጠብቃቸው የነበረውን መልካሙን የትዳር ዘመን እያስታወሱ በሚብሰለሰሉበት ወቅት ነበር ከሁለተኛ ትዳር አገራቸው ጋር የተገናኙት።

ትግስት ደረጀ የተባለችው የአርሲ ነገሌ ከተማ ነዋሪ ጋር በአጋጣሚ ይተዋወቃሉ። ወትሮም ብቸኝነት አስመርሯቸው የነበረው አቶ ከተማ የተወሰነ የፍቅር ምልክት ሲያዩ ጉዳዩን ወደ ቁም ነገር ወስደው በትዳር ይጣመራሉ። ትደራቸው ሞቅ ያለ በሀብት የተባረከ በመሆን ከብቸኝነታቸው ያላቅቃቸዋል። አቶ ከተማ አበበ ከወይዘሮ ትግስት ደረጀ ጋር አብረው እየኖሩ እያለ አቶ ከተማ በሸቀጣሸቀጥ ንግድ የተዋጣላቸው ሰው ይሆናሉ። ስኬቱ ጎልብቶ ሥራው ያለ ረዳት የማይሠራበት ደረጃ ላይ መድረስ ይጀምራል።

እሳቸው ለገበያም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ሱቁን ዘግተው ከመውጣት በማለት ረዳት ሠራተኛ መቅጠር አለብኝ ብለው ሰው ማፈላለግ ጀመሩ። ሥራ የሚረዳቸው ሰው እየፈለጉ እንደሆነ የሰማችው ባለቤታቸው ወይዘሮ ትግስት ሌላ ሰው ከሚቀጠር ወንድሜ ሥራውን ቢያግዝ ብላ ትጠይቃለች ። ለዚህም እንደ ምክንያት ያቀረበችው ገንዘበ አካባቢ የማይታወቅ ሰው ከማስቀመጥ ቤተሰብ መቅጠር ከዘረፋ ሊያድን ይችላል የሚል ነበር።

አቶ ከተማ በአንድ በኩል በሁለት ጥንዶችና ባለ ትዳሮች መካከል ቤተሰብ ጣልቃ ማስገባት ጥሩ እንዳልሆነ ቢረዱም ለባለቤታቸው ትግስት ካላቸው ፍቅር የተነሳ ይስማማሉ። ከፍቅሩም በሻገር የተወሰኑ ገንዘቦች ቢነካኩም ቤተሰብ ስለሆነ ከራስ አይወጣም ብሎ በማሰብ ከባዳ ወገን ይሻላል በማለት ወንድሟ መጥቶ የሱቁን ሥራ እንዲያግዛቸው ይስማማሉ።

### በታማኝነት የተመረጠው የባለቤታቸው ወንድም

የወይዘሮ ትእግስት ደረጀ ወንድም ሙሉቀን ደረጀ ቤተሰብ ጋር ያለ ሥራ ቤት ተቀምጦ ውሎ ማደሩ ከእናትና አባቱም በላይ ትእግስትን ሲያስጨንቃት ኖሯል። እንድ ወንድ ዞር ዞር ብሎ ሥራ ከመፈለግ ይልቅ ተኝቶ መዋልን ምርጫው ያደረገው ወጣቱ ሙሉቀን ለምን እንደማይሠራ ቢጠየቅም ምንም ምላሽ ስለማይሰጥ ቤተሰቦቹም እንዳሻው ብለው ትተውታል።

ልክ የትእግስት ባለቤት አቶ ከተማ ሠራተኛ የመፈለጋቸውን ጉዳይ ከሰማችበት ሰአት ጀምሮ ወንድሟ በልቧ እየተመላለሰ አላስተኛት ያለው ወይዘሮ ወንድሜ ለስራ ይምጣና እኛ ጋር ይሁን በማለት ባለቤቷን አሳመነች። በዚህም ወላጆቿም ሆኑ መላው ቤተሰብ በጣም ተደሰቱ። ወትሮም ሥራ ፈልጎ የማግኘት ነገር ሞት የሆነበት ወንድሟ እንዲህ የተመቻቸ እድል ሲያገኝ ዓይኑን ሳያሽ ወደ ከተማ ቤት ይመጣና ሥራ ይጀምራል።

ለዓመታት ከቤት ሳይወጣ ታሽጎ የተቀመጠው ወጣት ብር በእጁ ሲገባ ከተማውን ዞር ዞር ብሎ ሲመለከት ጓደኛ መያዝ ያምረዋል። የእህቱ ባለቤት ሱቅ ተቀጥሮ መሥራት የጀመረው ሙሉቀን ደረጀ ነገሌ አርሲ ከተማ ነዋሪ ከሆነችው ሰላም ፋንታሁን ከተባለች ልጅ ጋር ይተዋወቃል። የእህቱ ባል ጥረው ግረው ያፈሩት ሀብትን እንደልቡ ማድረግ የቻለው ወጣት በግብዣና በስጦታ እያባበለ ፍቅር ይጀምራል።

በየእለቱ መግባት ከሚገባው ገቢ እየቀነሰ መምጣቱ ያሳሰባቸው አቶ ከተማ ይህ ነገር ከምን እንደመጣ ለማወቅ ይከታተሉ ጀመር። በክትትላቸውም መሠረት የባለቤታቸው ወንድም ፍቅር ውስጥ መግባቱንና ለልጅቱ የተለያየ ነገሮችን ለማድረግ ሲል ሂሳብ እያጎደለ መሆኑን ይረዳሉ።

አቶ ከተማ አበበ የባለቤታቸው ወንድም ሙሉቀን ፍቅር መጀመር ተገቢ መሆኑን ቢረዳም ከልጅቷ ጋር ከተዋወቀ ጊዜ አንስቶ ሥራ እየሠራ እንዳልሆነ ለባለቤቱ ትግስትና ወንድሟን ሙሉቀን ይነግራቸዋል። ሥራውን በአግባቡ እየሠራ ገንዘቡን በትክክል የማያስረክብ ከሆነም ሊባረር የሚችል መሆኑንም አስረገጠው ይናገራሉ።

በዚህም ምክንያት ከተማ አበበና የባለቤቱ ወንድም ሙሉቀን ጋር ቅራኔ ይፈጠርና ሙሉ ቀን ከቤት ይወጣል። የወንድሟ ከቤት መውጣት የከነከናት ሚስት ለማን መወገን እንደሚገባት ግራ ተጋብታ እጇን አጣጥፋ ትቀመጣለች።

የአቶ ከተማ ባለቤት ወንድም ከቤት ከወጣ ጀምሮ ቂም በመያዝ አቶ ከተማን አበበ ለመግደል ያስባል። በሀብቱ ተመክቶ ከቤቱ አባሮኛል፤ ቤተሰቤንና እህቴን አሳጥቶኛል በማለት መውጪያ መግቢያውን ያጠናል። ማጥናት ብቻ ሳይሆን የግድያ አቅድም ያወጣል። የእቅዱ ተባባሪ እንድትሆን እህቱን ትግስትን ያማክርታል ። ትእግስት በፍፁም አንደማትስማማ ብትነግረውም፤ እሷ የማታዝበት ሀብት ከሚኖራት ግለሰቡን ከገደሉት በኋላ ንብረቱን አብረው እንደሚውርሱና የቤተሰባቸውን ሕይወት ሊቀይሩ የሚችሉ መሆኑን ያሳምናታል። ልቧ ለሁለት ቢከፈልም ከወንድሟ የሚበልጥ የለም በማለት ባሏን ገድላ ሀብቱን ለመውረስ ትስማማለች።

### የሞት ድግስ

አቶ ከተማ የባለቤታቸው የትእግስት ወንድም ከቤት በመውጣቱ የሚወዷት ባለቤታቸው እንዳትከፋ ነጋ ጠባ እሷን ለማስደሰት የተለያዩ ጥረቶችን ያደርጋሉ። ተወዳጇ ሚስታቸውም የሆዷን በሆዷ ይዛ ምንም እንዳልመሰላት በማስመሰል ፈገግ ፈገግ ትላለች።

በእለቱም ማታ ላይ የሚወዱትን ምግብ ሠርታ ቤቷን ፏ አድርጋ አፅድታ ቡና አፍልታ እራሷም ታጥባ ፅድታ ነበር የተቀበለቻቸው። ከአራት በኋላ ቡና እየተፈላ ቆሎ እየቆረጠሙ ጠላ ፉት ማለት ለሚወዱት አባ ወራ እንደውዴታቸው ጠላውንም የገብስ ቆሎውንም አዘጋጅታ ነበር የጠበቀቻቸው።

በስተጓሮ ከሚገኘው ክፍል ውስጥ ወንድሟና የወንድሟን ፍቅረኛ ሸሽጋ አስገብታ የቆየች ቢሆንም ምንም ነገር እንደላሰበች በማስመሰል ባሏን ስትንከባከብ ታመሻለች። ምሽቱ ስለገፋና ጠላው በእናት በእናት ስለተቀዳ ያዳከማቸው አቶ ከተማ እንቅልፍ ሲያዳፋቸው እኔ ልግባ ነይ ብለዋት ወደ ውስጥ ገቡ።

እሷም እቃውን አነሳስታ እንደምትመጣ ተናግራ እቃ ማነሰሳት ጀመረች። ምሽቱ ሊጋመስ ጥቂት ሲቀረው ወደ መኝታ ክፍሉ የገባቸው ሚስት ባለቤቷ ጧ ብለው መተኛታቸውን ትመለከታለች። ለመቀስቀስ ሙከራ ብታደርግም ገልበጥ ብለው እንቅልፋቸውን የቀጠሉት ባለቤቷ ሊነቁ እንደማይችሉ ስትረዳ በቀስታ ከክፍሉ ተመልሳ ወጣች።

በካቲት 10 ቀን 2015 ከምሽቱ 6:00 ሰአት ሲሆን ወንድሟና ፍቅረኛው ከተደበቁበት እንዲወጡ ጠርታ ያሰቡትን ለማድረግ ተዘጋጁ። በእለቱ ትግስት ደረጀ፣ ሙሉቀን ደረጀ እና የሙሉቀን ፍቅረኛ ሰላም ፋንታሁን፣ አቶ ከተማ አበበን በተኙበት በመጥረቢያ ቆራርጠው ገደሏቸው። ሀገር ሰላም ብለው በተኙበት በአመኑት እጅ እስከ ዘለአልም አንቀላፉ። በህብረት የገደሏቸውን አቶ ከተማን ቆራርጠው በማዳበሪያ ከከተቱ በኋላ ቀድሞ እነ ሙሉቀን ተደብቀው የነበረበት ቤት ውስጥ ይቀብሯቸዋል።

ማስረጃ ይሆናል ያሉትን ነገር በሙሉ አጥፍተው ከጨረሱና በደንብ ከተረጋጉ በኋላ ለቀጣይ እቅድ ቁጭ ብለው መመካከር ጀመሩ። የሠሩትን ሠርተው ዝም ካሉ ፖሊስ ጉዳዩ ላይ ሊደርስብት እንደሚችል በመነጋገር የአቶ ከተማ ባለቤት ወይዘሮ ትእግስት ፖሊስ ጣቢያ ሄደው እንዲያመለክቱ ይስማማሉ።

በስምምነታቸውም መሠረት ይህን ፀያፍ ድርጊት ከፈፀሙ በኋላ ከተማ አበበ ቤት እንዳልመጡና ገዳዩ ሲያስጨንቃቸው ማደሩን በጠዋት በመሄድ ለፖሊስ ያመለክታሉ። ፖሊስ የአቶ ከተማ አበበ መጥፋት ጥቆማ ከደረሰው በኋላ የክትትል ሥራውን ጀመረ።

### የፖሊስ ምርመራ

አቶ ከተማ አበበ ቤት እንዳልመጡ መረጃው ከደረሰው በኋላ ክትትል ሲጀምር ሙሉቀን ወደ አዲስ አበባ መሄዱን ይሰማል። የሙሉ ቀን ከከተማይቱ መውጣት ሲሰማ ፖሊስ ሁኔታውን በመጠራጠር እህቱንና ፍቅረኛውን በቁጥጥር ሥር ያውላቸዋል። ወትሮም የሰው ደም ገዳይን ማቅነዝነዙ አይቀርምና ገና በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ሲውሉ ነበር ያልተጠየቁትን በሙሉ መቀበጣጠር የጀመሩት።

ነገረ ሥራቸው የላማረው ፖሊስ ወደ ማረፊያ ቤት በማስገባት በማግስቱ በደንብ በተቀናጀ ሁኔታ ቃላቸውን መቀበል ጀመረ። መጀመሪያ ሁለቱን በጋራ ለማናገር በተደረገው ሙከራ እርስ በእርስ በመተያየት አቀርቅረው ዝም ከማለት በስተቀር ምላሽ መስጠት አልቻሉም።

ያን ጊዜ ለየብቻቸው ማነጋገር አማራጭ ያደረገው ፖሊስ መጀመሪያ የሟችን ባለቤት ወይዘሮ ትግስት ላይ ምርመራ ሲያደርግባት ወንድሟ ድርጊቱን እንዳቀነባበረው ትናገራለች። ያለፍላጎቷ በተለያዩ ማባበያዎች ያሳመናት መሆኑንም ታስረዳለች።

የሙሉቀን ፍቅረኛም ሙሉቀንን በማበረራቸው ቂም ይዛ መቆየቷንና ለፍቅረኛዋ ስትል የድርጊቱ ተባባሪ መሆኗን አስረዳች። ፖሊስም ባለቤቱንና የሙሉቀን ፍቅረኛ ሰላም ፋንታሁንን በቁጥጥር ስር አውሎ ሙሉቀንን መፈለግ ጀመረ።

የሙሉቀን ፎቶ ለመላው ሀገሪቱ ፖሊስ በማሰራጨት በድብቅ እንዲፈለግ ተወሰነ። በፖሊሶች ያልተቋረጠ ፍለጋ ሲደረግበት የነበረው ተጠርጣሪ ማንም አያውቀኝም አያገኘኝም በሎ ባሰበበት በአዲስ አበባ ከተማ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በነፃነት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥር ስር ውሏል።

ፖሊስም የተከሳሾችን የእምነት ክህደት ቃልንና የሰነድ ማስረጃ ማለትም የፎረንሲክ ምርመራውን በማጠናቀር ለፌዴራል አቃቤ ሕግ ልኳል።

### የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው በካቲት 10 ቀን 2015 ከምሽቱ 6:00 ሰአት ሲሆን ትዕግስት ደረጀ ወንድሟና ፍቅረኛው ከተደበቁበት እንዲወጡ ጠርታ ባለቤቷን ለማስገደል ተዘጋጀች። በእለቱ ትግስት ደረጀ፣ ሙሉቀን ደረጀ እና የሙሉቀን ፍቅረኛ ሰላም ፋንታሁን፣ አቶ ከተማ አበበን በተኙበት በመጥረቢያ ቆራርጠው ገደሉት። በፈጸሙት የግድያ ወንጀል በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

ወንጀላቸውም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሀብት ያላግባብ ለመውረስ በፈፀሙት ድርጊት በመክሰስ ውሳኔ ለመስጠት ቀን ተቆረጠ።

**ውሳኔ**

**ፖሊስና አቃቤ ሕግ በጋራ በመሆን ምርመራ መዝገቡን በማጣራት በተመሠረተው ክስ መሠረት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሀብት ያላግባብ ለመውረስ በፈፀሙት ድርጊት እያንዳንዳቸው ላይ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወስኖባቸዋል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ከህሊና ጋር ትንቅንቅ

**ዋስልኝ አየለ**

ባለፈው ሐሙስ ነው፡፡ በአዲስ አበባ፣ 02 ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የፒያሳና አራት ኪሎ ታክሲ መያዣው ጋ (የረር ሕንጻ አጠገብ) ቆሜ ሰው እየጠበቅኩ ነው፡፡ ከሕንጻው ሥር ብዙ ጫማ የሚያጸዱ (ሊስትሮ) ልጆች አሉ። አንደኛው ሰውዬ ጫማ ለማስጠረግ ከጎን ተቀምጦ ወረፋ እየጠበቀ ነው፡፡ በዚህ መሐል አንዲት ሁለት ልጆች የያዘች እናት መጣች፡፡ አንደኛውን በጀርባዋ ያዘለችው ሲሆን ሁለተኛው በእግሩ ከፊት ከፊቷ የሚሄድ ነው። በልመና ላይ ነች።

ወረፋ ከሚጠብቀው ሰውየ ጋ ስትደርስ ሰውየው ወደ ኪሱ ገባ፡፡ ከኪሱ ካወጣው ብር ውስጥ ዝቅተኛው 50 ብር ነው፡፡ ያወጣውን ብር በአንደኛው እጁ ይዞ ወደ ሌላኛው ኪሱ ገባ፡፡ በዚህን ጊዜ ሕጻኑ ልጅ እጁን ወደ ሰውየው ዘረጋ። ይሄኔ እናትየዋ የልጁን እጅ መታ እያደረገች ‹‹እረፍ›› አይነት ቁጣ ተናገረችው፡፡ ሰውየው የፈቀደውን ይስጥ እንጂ ግዴታ በሚመስል መንገድ መሆን የለበትም በሚል ከህሊናዋ ጋር እየታገለች መሆኑ ነው፡፡ ሰውዬው ከሌላኛው ኪሱ ሲገባ ዝርዝር ብር አጣ፡፡ ወደ ኪሱ መግባቱ ደግሞ ሴትዮዋ እና ልጆቹ እንዲጓጉ አድርጓል። እሱም ከህሊናው ጋር እየታገለ ነው፡፡ 50 ብሩን ነጥሎ በማውጣት ሰጣት፡፡ አመስግና ሄደች። እኔም በውስጤ ደስ የሚል ነገር ተሰማኝ። ምንም እንኳን ያላሰበውን ቢሆንም የሰጠው ቢያንስ ከእርሷ እሱ ይሻላልና ለእርሱም የህሊና ደስታ ነው፡፡

እንዲህ አይነት ከህሊና ጋር ትንቅንቅ የሚገጠምባቸው ሁኔታዎች የሚያጋጥሙኝ ልጅ ይዘው በሚለምኑ እናቶች ላይ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ በየካፌውና ምግብ ቤቱ ውስጥ ሰውነታቸው የጠወለገ ሕጻናት ይዘው የሚመጡ እናቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከምግብ ቤቶች ባለቤቶች ጋር አትገቡም የሚል ሌላ ትንቅንቅም አለ፡፡ እነዚህን እናቶችና ሕጻናት ማየት ልብን ይሠብራል። የሞቀ ቤትና ንብረት የነበራቸው ሰዎች ናቸው። ሕጻናት ይዛ የምትለምን አንዲት እናት ሳይ የዚያች እናት ነገር ብቻ አይደለም የሚያሳስበኝ፤ እሷን የመሰሉ በከተማዋ ጎዳናዎች ዳር ሁሉ አሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሕጻናት ይዘው የሚለምኑ እናቶች ሳይ ‹‹የሚሰጣቸው ይኖር ይሆን?›› በሚል ስጋት ጭምር ነው እጃቸውን የዘረጉበትን ሁሉ የማየው፡፡ በእርግጥ ችግሩ ለእነዚህ እናቶች 5 ብር እና 10 ብር በመስጠት የሚቀረፍ አይደለም!

ከችግሩ በላይ የሚያሳዝነው ከህሊና ጋር ያለው ትንቅንቅ ነው፡፡ ያቺ ሴትዮ የምትለምነው ተቸግራ ነው። ልጁ ወደ ሰውየው እጁን ሲዘረጋ የከለከለችው ግን በሰጪው ሰውዬ መልካም ፈቃድ ብቻ መሆን አለበት እያለ አዕምሮዋ ስለሚታገላት ነው፡፡ ያ ሰውዬ የያዘውን ብር ሁሉ ቢሰጣት ደስታዋ ነው። ያ ግን መሆን ያለበት በሰውዬው መልካም ፈቃድ ብቻ ነው፡፡ ወዲህ ደግሞ ልጁ እጁን መዘርጋቱ ሰውየው እንዲታዘበኝ ያደርገኛል ብላ ከህሊናዋ ጋር እየታገለች ነው፡፡ በዚህ ሕይወት ውስጥ ሆና እንኳን ‹‹ልጁን በጨዋነት አታሳድገውም እንዴ?›› ይሉኛል የሚል ይሉኝታ ይዟታል፡፡ አሳሳቢው ነገር ይህ ችግር እየከፋ ሲሄድ፣ ተጨማሪ ተፈናቃይ ሲበዛ እና ሰጪ ሲጠፋ አሁን ያለው ይሉኝታ እና ከህሊና ጋር የሚደረግ ትንቅንቅ ያልቃል፡፡ አሁን እየኖሩ ያሉት ከዚህ በፊት በነበራቸው የምቾት ጊዜ ባዳበሩት ይሉኝታና ህሊና ነው፡፡

ሰጪው ሰውዬም ህሊናው እምቢ ብሎት ነው 50 ብር የሰጠው፡፡ መጀመሪያ ላይ ዝርዝሮች ሲፈልግ ነበር። ያቺ ልጆች የያዘች እናት ከፊቱ ቆማ ግን ዝርዝር አጣሁ ብሎ መተው አልቻለም፤ ሊያደርገውም አይችልም፡፡ ምክንያቱም እጁን ከኪሱ አስገብቶ ሲያወጣ ከታየ በኋላ መተው ለማንም ሰው ይከብዳል፡፡

ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ ግን እነዚህ ይሉኝታዎች እንዳይሚጠጡ ያስፈራል፡፡ ለልመና የሚሰማሩ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ብቻ ይታይ የነበረው አሁን በየምግብ ቤቱና በየካፌው በር ላይ ሆኗል። በየትኛውም ቦታ ላይ ሕጻናት ይዘው የሚለምኑ እናቶችን ማየት የተለመደ ነው። ይህ ቁጥር እየጨመረ ከሄደ የሚሰጠው ዜጋ ቁጥር ይቀንሳል፡፡ ከዚህ በፊት የሚለምን ሰው ሲያይ አንጀቱ ይላወስ የነበረ ሰው የዕለት ከዕለት ክስተት ሲሆንበት እየተላመደው ይሄዳል፡፡ ከዚህ በፊት አንድ የተቸገረ ሰው ሲታይ ‹‹ለወገን ደራሹ ወገን ነው›› በሚለው ተረባርቦ ማዳን ተችሎ ነበር፡፡ አሁን ግን የተቸገረውና የሚለምነው ቁጥር ከበዛ የሰጪ ሰዎች አዕምሮ የተቸገረ ሰው ማየትን ይላመደዋል፡፡

ለጊዜው በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች፣ ችግረኞችን ማየት መላመዳቸው በልመና ላይ የተሰማሩት የሚበሉት እንዲያጡ ያደርጋል። የሚበሉት አጡ ማለት ደግሞ ነገርየው በልመና ብቻ እንዲገደብ አያደርገውም። ቁጥሩ እየጨመረና እየከፋ ከሄደ ዝርፊያ እና መቀማት ሁሉ ሊጀምር ይችላል። አዲስ አበባ አሁን ከሚታየው በላይ ተፈናቃይ ዜጎች ይኖሯታል። ያኔ ችግሩ ለሁሉም ይተርፋል ማለት ነው፡፡ አሁን በጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉትንም ይነካል ማለት ነው፡፡ በ“አደገኛ አጥር እና በ“አደገኛ ውሻ ሊከላከሉት የሚችሉት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ”ሲቀጥል የውጭው ሁኔታ የተረበሸ ከሆነ በቤት ውስጥ ሰላም ሊኖር አይችልም፡፡ ከውጭ ዳቦ ገዝቶ መግባት የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

እነዚህ ነገሮች ዛሬ ላይ ሆነን ስናያቸው ምናልባትም ‹‹ሟርት›› ሊመስል ይችላል፡፡ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች የሚታዩ በልመና ላይ የተሰማሩ ዜጎች ቁጥር ግን እንዲህ በቀላሉ የሚታይ መሆን የለበትም። የመንገደኛ ልብስ ላይ ተጣብቀው የሚከታተሉ ሕጻናት በየጎዳናው ላይ አሉ። እንቅስቃሴው ሁሉ በመኪና የሆነ ሰው ይህን ችግር አይረዳው ይሆናል፤ ለጊዜውም እሱን አያገኘው ይሆናል፡፡ ችግሩ እየከፋ ከሄደ ግን እንኳን በመኪና በአየር የሚሄድም አያመልጥም። ምክንያቱም የከተማዋ የውጭ ሁኔታ ሲበላሽ የውስጡንም ያበላሸዋል፡፡ ዛሬ ላይ የተደላደለ ኑሮ ላይ ያሉ ሰዎች ነገ ወጣ ብለው የሚዝናኑበት ሁኔታ ላይኖር ይችላል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ምን ሆነው ነው ለልመና የተሰማሩት? የሚለውን ሁሉም ሰው ሊጠይቅ ይገባል፡፡ እነዚህ ሰዎች የሞቀ ቤት የነበራቸው ናቸው። ሀገርን መቀለብ የሚችል ምርት ያመርቱ የነበሩ ናቸው፡፡ ለተቸገረ ያጎርሱ የነበሩ ናቸው። ልመናን ከማንም በላይ ይፀየፉ የነበሩ ናቸው። እንኳን ለምኖ ገዝቶ መብላትን እንደ ነውር የሚያዩ ነበሩ፡፡ ግን በየአካባቢያቸው ያለው የሰላም እጦት ለዚህ ችግር ዳረጋቸው፡፡

ስለዚህ ችግሩ አሁን ካለበት ከመባባሱ በፊት መንግሥትም ሕዝብም ጉዳዩን ‹‹በቃ›› ሊለው ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም በየመን በሁቲ አማጽያን ላይ የአየር ጥቃት ከፈቱ

የአሜሪካ እና የዩናይትድ ኪንግደም ጥምር ኃይል በየመን የሁቲ አማጽያንን ዒላማ በማድረግ የአየር ጥቃት ከፈቱ። ሁለቱ ሀገራት በጥምረት ጥቃት ከጀመሩ በኋላ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፣ ጥቃቱ በኢራን የሚደገፉት የሁቲ አማጽያን በቀይ ባሕር ላይ በመርከቦች ላይ ላደረሱት ጥቃት ምላሽ እንደሆነ ተናግረዋል።

የሁቲ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም “ከፍተኛ ዋጋ” እንደሚከፍሉ አስጠንቅቋል። የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ እንዳሉት፣ የሮያል አየር ኃይል ጥቃቱን የከፈተ ሲሆን፣ ይህ ጥቃት “ውስን፣ አስፈላጊና ራስን ለመከላከል የተፈጸመ ተመጣጣኝ እርምጃ ነው” ብለዋል።

ኔዘርላንድስ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ እና ባሕሬን ለዚህ ጥቃት ድጋፍ መስጠታቸው ተገልጿል።ጥቃቶች ተፈጽመዋል የተባሉት በየመን መዲና ሰንአ፣ በሁቲ በተያዘ የቀይ ባሕር አካባቢ ሁዳያህ፣ ዳህማር እና በሰሜን ምዕራብ ከፍተኛ የሁቲ አማጽያን ይዞታ ባለበት ሳዳ ነው።የሁቲ አማጽያን አብዛኛውን የመን ይቆጣጠራሉ።

ለሐማስ ድጋፍ ለመስጠት ወደ እስራኤል እየተጓዙ የነበሩ መርከቦች ላይ ጥቃት ሲሰነዝሩ ቆይተዋል።የሁቲ መሪ ሞሐመድ አል-ቡካቲ፣ አሜሪካ እና ዩኬ “በቅርቡ በታሪካቸው ትልቅ ስህተት መሥራታቸውን ይገነዘባሉ” ብሏል።“የመን ላይ ጦርነት መክፈታቸው ስህተት ነው። ከቀደመው አልተማሩም” ብሏል።

በቀይ ባሕር ላይ የሁቲ አማጽያን መርከቦች ላይ ባለፉት ሳምንታት በፈጸሟቸው ጥቃቶች ሳቢያ ግዙፍ የባሕር መጓጓዣ ድርጅቶች ሥራ ለማቋረጥ ተገደው እንደነበር ይታወሳል።የኤሌክትሪክ መኪና አምራቹ ተስላ በግብዓት መስተጓጎል ሳቢያ የጀርመን፣ በርሊን



ምርቱን ማቆሙን ገልጿል።

በአማጽያኑ ላይ የደረሰው የአየር ጥቃት በቀጣይ ሁቲዎች ጥቃት እንዳይሰነዝሩ መልዕክት ሊያስተላልፍ እንደሚችል ምዕራባውያን መሪዎች ያምናሉ።በአሜሪካ፣ ዋይት ሀውስ ፊት ለፊት ‘ከየመን እጃችሁን አንሱ’ የሚል መፈክር ያለው የተቃውሞ ሰልፍ ተካሂዷል።‘የመን ትኑርበት’ የሚሉና ሌሎችም መፈክሮች ተሰምተዋል።

የአውስትራሊያ፣ ባሕሬን፣ ካናዳ፣ ዴንማርክ፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድስ፣ ኒው ዚላንድ እና ኮርያ፣ አሜሪካ እና ዩኬ መንግሥታት በጋራ መግለጫ አውጥተዋል።ሁቲዎችን በተመለከተ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ “ስምምነት” ላይ መድረሱን መግለጫው ይጠቁማል።“የግልና የጋራ መከላከል መብትን በተከተለ ሁኔታ” የአየር ጥቃቱ መፈጸሙን አገራቱ ባወጡት መግለጫ አካተዋላል።

“እነዚህ ዒላማ ያላቸው ጥቃቶች የሁቲን አቅምና መዋቅር ለማዳካም ነው ያለሙት። የሁቲ እንቅስቃሴ በዓለም ቀዳሚው የውሃ አካል ላይ ዓለም አቀፍ ንግድን አውኳል” ብለዋል።ግባቸው “ቀውሱን ማብረድና አካባቢውን ማረጋጋት” እንደሆነም አክለዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ባለፈው ወር ባወጣው መግለጫ የሁቲ አማጽያን በቀይ ባሕር ላይ በሚጓዙ መርከቦች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት እንዲያቆሙ ጠይቋል።ሳውዲ አረቢያ በበኩሏ አሜሪካ እና አጋሮቿ ከጥቃትና ነገሩን ከማባባስ “እንዲቆጠቡ” አሳስባለች።የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ “ከፍተኛ ስጋት አለን” ማለታቸውም ተዘግቧል።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ዋና ሐጸፊ ሎይድ አስተን፣ የአየር ጥቃቱ የተፈጸመው በሁቲ ተሽከርካሪዎች፣ መርከቦች፣ የአየር መቆጣጠሪያዎችና ሌሎችም መገልገያዎች መሆኑን ተናግረዋል።እስካሁን ወደ 12 ገደማ ዒላማዎች መመታታቸው ተገልጿል።ባይደን ተጨማሪ ርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል።

አሜሪካ እና አጋሮቿ “ጥቃትን ዝም ብለን አንቀበልም። በዓለም ዋነኛ የንግድ ቀጣና እርምጃ ሲወሰድም ዝም አንልም” ብለዋል። በቀይ ባሕር ላይ እየደረሱ ያሉ ጥቃቶች የማያቆሙ ከሆነ በሁቲ አማጽያን ላይ ርምጃ እንደሚወሰድ ምዕራባውያን አገራት ባለፉት ሳምንታት ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ ቆይተዋል።

የየመን ሁቲ አማጺያን በቀይ ባሕር ላይ የሚያልፉ ዕቃ ጫኝ መርከቦችን በሚሳኤል እና በድሮን ዒላማ ማድረጋቸው የነዳጅ እና የሌሎች ምርቶችን ዋጋ ከፍ ያደርጋል መባሉን ይታወሳል።ሰፊ የየመን ግዛትን ተቆጣጥረው የሚገኙት ሁቲ አማጺያን ከእስራኤል እና ከሐማስ ጦርነት መቀስቀስ ወዲህ በቀይ ባሕር በኩል በሚያልፉ ግዙፍ የጭነት መርከቦች ላይ ጥቃት ሲሰነዝሩ ቆይተዋል።

አማጺያኑ ከእስራኤል ጋር ጦርነት ውስጥ ለገባው ሐማስ ያላቸውን ድጋፍ በይፋ ከገለጹ በኋላ፣ በቀይ ባሕር በኩል አድርገው ወደ እስራኤል የሚያቀኑ መርከቦችን ዒላማ እንደሚያደርጉ በይፋ አሳውቀዋል። የሁቲ አማጺያን ባለፉት ሳምንታት ወደ ተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ነዳጅ እና የተለያዩ ምርቶችን ጭነው የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ መርከቦችን በሚሳኤል እና በድሮን ሲያጠቁ እና እገታ ሲፈጽሙ ነበር።

ታዲያ ይህ ስጋት ውስጥ የከተታቸው የዓለማችን ዋነኛ የመርከብ ጭነት ማጓጓዣ ድርጅቶች ቀይ ባሕርን ከመጠቀም ይልቅ ረዥም ጊዜ እና ብዙ ነዳጅ አባክነው በደቡብ አፍሪካ በኩል አድርገው ወደ መዳረሻቸው እያቀኑ መሆኑ ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከመንግሥት ጥረት ጎን ለጎን ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ለሰብዓዊ ድጋፍ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል!

የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች የመገናኛ ብዙኃን የዕለት ተዕለት ዜና መሆን ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። የችግሩ አሳሳቢነትም ዓለም አቀፍ አጀንዳ ከሆነ ውሎ አድሯል። መፍትሄ የማፈላለጉም ሥራ የብዙዎችን ትኩረት እየሳበ ይገኛል።

ችግሩ በተለይም በድሆችና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ሕዝቦች ላይ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ " በመሆን፤ አጠቃላይ በሆነው የመልማት ፍላጎታቸው ላይ ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል። ምክንያት ላልሆኑባቸው ችግሮች ዋነኛ ገፈት ቀማሽ በመሆንም ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ተገደዋል።

በተለይም የአየር ንብረት ለውጡን ተከትሎ ከሚከሰተው ድርቅ ጋር በተያያዘ ተጠቂ የሆኑ የአፍሪካ ሀገራት፤ ችግሩ ቀድሞውኑም በምግብ እህል ራሳቸውን የቻሉ ካለመሆናቸው ጋር ተዳምሮ ፤ሕዝቦቻቸውን ለከፋ አደጋ ተጋላጭ እያደረጋቸው ይገኛል።

የችግሩን አሳሳቢነት ቀድመው የተረዱ የአህጉሪቱ ሀገራት መንግሥታትም ቢሆኑ፤ ችግሩን ቀድመው ለመከላከል ለሚያደርጉት ዝግጅት በቂ የሆነ ዓለም አቀፍ ድጋፍ ባለማግኘታቸው አደጋዎች ሲከሰቱ ባሰቡት ልክ ሕዝቦቻቸውን መታደግ የሚያስችል አቅም መገንባት ተስኗቸው፤ እጃቸውን ለርዳታ ለማንሳት መገደዳቸው የማይቀር ሆኗል።

ችግሩን እያስከተለ ካለው ዓለም አቀፍ ምስቅልቅል አንጻር ለማየት ፈቃደኛ ያልሆነው አንዳንድ አካላት በችግሩ ሰለባ በሆኑ ሀገራት ሕዝቦች ስቃይ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በየትኛውም ሰብአዊ መመዘኛ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል።

ችግሩ በተደጋጋሚ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች ላይ እየተከሰተና ዋጋም እያስከፈላቸው ነው። የቀጣናው ሕዝቦች በተደጋጋሚ የድርቅ እና የጎርፍ አደጋዎች እየተጠቁ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። በዚህም እየከፈሉት ያለው ዋጋ ነገዎቻቸውን እያደበዘዘባቸው ነው።

አሁን ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የአየር ንብረት ለውጥ ተከትሎ በተከሰተ የድርቅ አደጋ ከፍተኛ ለሆነ የምግብ እጥረት ተጋልጠዋል።ችግሩ ወደ ከፋ ረሀብ እንዳይቀየርም ስጋት ስለመፍጠሩ ከሁሉም በላይ ከችግሩ ዋነኛ ባለቤቶች እየተነገረ ነው።

ችግሩ በኛም ሀገር አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጋችን የአስቸኳይ ርዳታ ድጋፍ ጠባቂ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፤ በቀጣይ ሦስት ወራትም የርዳታ ፈላጊዎቹ ቁጥር ወደ ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሊያድግ እንደሚችልም ይታመናል።

ከርዳታ ፈላጊዎቹ 80 በመቶ የሚሆኑት፤ በአማራ ክልል ስምንት ዞኖች፣ በትግራይ ክልል አራት ዞኖችና በአፋር ክልል ሦስት ዞኖች የሚገኙ ናቸው፤ ችግሩ ወደ ረሃብ እንዳይቀየር በመንግሥት በኩል ተከታታይ የሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች ተጠናክረው እንደቀጠሉ ነው።

መንግሥት ቀደም ባለው ጊዜ በምግብ እህል ራስን ለመቻል የጀመራቸው ጥረቶች እና ጥረቶቹ እያስገኙት ያለው ውጤት፤ችግሩ የከፋ አደጋ ከማስከተሉ በፊት መከላከል የሚያስችል ብሔራዊ አቅም መገንባት አስችለዋል። ከዚህ የተነሳም እስካሁን ባለው ሂደት ችግሩ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ ሳይሆን ቀርቷል ።

ችግሩን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ እስካሁን አብዛኛውን ድጋፍ እያቀረበ የሚገኘው መንግሥት ነው። ይህ መንግሥት ከፈጠረው የአደጋ መከላከል ዝግጁነት አንጻር ከፍ ያለ እውቅና ሊያሰጠው የሚገባና እንደ አንድ ስኬታማ ተሞክሮ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ከዚህም ባለፈ መንግሥት በተለያዩ ወቅቶች በመርህ ደረጃም "አንድም ኢትዮጵያዊ በምግብ እጥረት ምክንያት መሞት የለበትም፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ያለንን ሀገራዊ አቅም በሙሉ በመጠቀም ዜጎችን ከአደጋ ለመታደግ ዝግጁ መሆኑን" ደጋግሞ ማሳወቁ ለዜጎች ሕይወት ያለውን ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየ ነው።

እስካሁንም በመላ ሀገሪቷ ባሉት ከሶስት ሺህ በላይ የምግብ ማከማቻ ጣቢያዎች፤ ከ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር አንስቶ እስከ ታኅሣሥ መጀመሪያ ድረስ 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ቁሳቁሶችንና የምግብ ድጋፎችን በሶስት ዙሮች አቅርቧል። በዚህም የብዙ ዜጎችን ሕይወት መታደግ ችሏል።

ይህም ሆኖ ግን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ችግሩንና ከችግሩ በስተጀርባ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ተሳቢ በማድረግ፤ ችግር ውስጥ ያሉ ዜጎቻችንን የመደገፍ የሕግ ሆነ የሞራል ኃላፊነት አለበት።ለዚህም ከተለመዱ ፖለቲካዊ ቅድመ ሁኔታዎች ወጥቶ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

የመንግሥት ጥረት ውጤታማ እንዲሆንም የችግሩን ግዝፈት እና አሳሳቢነት ከማውራት ወጥቶ፤አስፈላጊውን ድጋፍ ፈጥኖ በማቅረብ ኃላፊነቱን ሊወጣ፤ ከተጠያቂነት ራሱን ሊታደግ በሚያስችል ተጨባጭ ተግባር ውስጥ ሊገኝ ይገባል።

በተለይም ለአየር ለውጥ በዋነኛነት ተጠያቂ የሆኑ ሀገራት ፤እነሱ በፈጠሩት ችግር ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል እየተገደዱ ላሉ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች አስፈላጊ የሆኑ ርዳታዎችን ከማቅረብ ጀምሮ የሀገራቱ መንግሥታት በምግብ እህል ራሳቸውን ለመቻል ለሚያደርጉት ጥረት ስኬት በቁርጠኝነት ከጎናቸው መሰለፍ ይጠበቅባቸዋል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአገልግሎት አሰጣጥን ግልጽ ማድረግ የብቁ ተቋም መገለጫ ሊሆን ይገባል

**ሰሚራ በርሀ**

አንድ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ሲመሰረት አገልግሎቱ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈለግ ስለመሆኑ ጥናት ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡ ምናልባትም ራሳቸው አገልግሎት ሰጪዎች ችግሩን በመረዳት ለማህበረሰቡ አዲስ እይታን ፈጥረው ችግር ፈቺ የአገልግሎት አይነትን ያስተዋውቃሉ፡፡

አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተቋማት የሚያመሳስላቸው ነገር በየእለቱ ባላቸው የሥራ ሒደት በአብዛኛው የነሱን አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል የተለያዩ ማህበረሰቦችን ማስተናገዳቸው ነው፡፡ የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ዴስኮች ነጋዴዎችም ጭምር በነዚህ ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

አገልግሎቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ በሒደት ተገልጋዮችን ማፍራት ሲጀምር አገልግሎቱን ፈልጎ የሚመጣውም ሰው ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት እነሱን ብሎ ለሚመጣ ተገልጋይ አገልግሎቱን በቀላሉ የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡

ዲጂታል ሲስተሞችን ይዘረጋሉ፣ የአንድ መስኮት አገልግሎቶችን ያስተዋውቃሉ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር ጥምረትን በመፍጠር የአገልግሎት ፈላጊውን ድካም በማቅለል ጊዜን ይቆጥባሉ፤ ተደራሽነታቸውን በማስፋትም ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

ሰዎች ካለባቸው የሥራ ጫና አማካኝነት ጊዜያቸውን የሚቆጥብላቸው በመሆኑ አሰራሩ በአሁኑ ሰዓት እየተለመደ የመጣ እና ተቀባይነትን እያገኙ ነው፡፡ በአገልግሎት ሰጪዎችና በተገልጋዮች መካከል የተሻለ ግንኙነት እየፈጠረ ነው፡፡ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችም እለት እለት የሚቀንሱበት ሁኔታም እየተስተዋለ ነው፡፡

ይህም ሆኖ ግን አሁንም አንዳንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሁንም እራሳቸውን በአግባቡ አይተው፤ የሚሰጡትን አገልግሎት የተሻለና ቀልጣፋ ማድረግ ሲሳናቸው ይታያል ። ስለነዚህ ተቋማት ከማንሳቴ በፊት ለአንዳንድ ችግሮች እራሱ አገልግሎት ፈላጊው ምክንያት የሚሆንበትን ላንሳ።

አንዳንድ ጊዜ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ለሚፈጠሩ ክፍተቶች የሚቀመጡ መብትና ግዴታዎችን በአግባቡ ካለማወቅና እና ካለማክበር የሚመነጩ ሆነው ይስተዋላሉ፤ ከነዚህ ውስጥ የተቀመጡ ቀነ ገደቦችን ሳያከብሩ መሄድ እና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች አለመሟላት በተጨማሪም ወደ ተቋማቱ በሚሄዱበት ወቅት በተለየ መልኩ መስተናገድ መፈለግ (ህጋዊ በሆነ መንገድ) ጉዳያቸውን ለማስፈጸም መፈለግ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ደግሞ በተደጋጋሚ የሚነሱ ክፍተቶች የሚጀምሩት ፤ የመረጃ ዴስክ ላይ ከተቀመጡ ባለጉዳይ ለማስተናገድ ከተቀመጡ ባለሙያዎች የሚመነጭ ነው፤ ትክክለኛውን መረጃ ያለመስጠት ችግር፡፡ ይህ ቀላል መስሎ የሚታይ ክፍተት ይሁን እንጂ የተቋሙን ገጽታ የሚያበላሽና ወደ ቦታው ያቀኑ ተገልጋዮችን ሰዓት በመግደል ለተለያዩ እንግልቶች የሚዳርግ ነው፡፡

ሌላው ከፍ ያለ ቅሬታ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሚያስነሳው ሰዓትን ጠብቆ በሥራ ቦታ አለመገኘት ፣ ተገልጋዮችን አለማክበር ፣ በእኩል ዓይን አለማስተናገድ ፣ ግላዊ ጥቅም መፈለግ ፣ በቶሎ ማለቅ የሚችሉ ሥራዎችን ማዘግየት ናቸው፡፡

በአንዳንድ ተቋማት የተለመደ እስከሚመስል ድረስ ሰዓት ባለማክበራቸው « አሁን አይገቡም እኮ » ተብለው የተለዩ ፣ ያልተገባ የግል ጥቅም በመፈለጋቸው « ያለ ገንዘብ መች ይሰራሉ » ተብለው የተፈረጁ አሉ፡፡

ሌላኛው ልብ የማንለው ክፍተት ደግሞ አገልግሎት ሰጪዎች ደንበኞችን ለማፍራትና ለመሳብ የሚጠቀሙት መንገድ እና ተገልጋዮች ወደ ተቋሙ ሲሄዱ አስቀድመው የሚያውቁትን እና ወደ ተቋሙ ለመሄድ እንዲወስኑ ያደረጋቸውን መረጃ የሚያፈርስ አልያም የማይገናኝ አገልግሎት ይሆናል፡፡

አልያም ተገልጋዮች የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት ሌላ የማይፈልጉትን አገልግሎት በእጅ አዙር እንዲጠቀሙ የሚያስገድድ ሆኖ ያገኙታል፡፡

ተቋሙ የሚከተለውን የአሰራር ሒደት ግልጽ አለማድረግ ተቋማቱ ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸውና የሚያገለግሉትን ሕዝብ በአግባቡ ስለማገልገላቸው ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡

በአብዛኛው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በተለይም የመንግሥት ተቋማት ደግሞ በሕዝብ ሀብት የተመሰረቱ መሆናቸው እየታወቀ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር የማይነጻጸር የአገልግሎት ክፍያ በመጠየቅ ሌላው ቅሬታ የሚያስነሳ ችግራቸው ነው ፡፡

ግልጽ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ተጠቃሚዎችን ለመሳብ የሚጠቀሟቸውን መንገዶች መመርመር፣ አገልግሎት መስጠት በጀመሩባቸው ቀናት ላይ ያሳዩትን ሥነ-ሥርዓትና ግልጸኝነት የሳቧቸውን ተገልጋዮች ደንበኛ አድርገው ማስቀረት እንዲችሉ አካሄዳቸውን ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡

አንዳንድ ተቋማቸውን ማሳደግ እና ማስፋት የሚፈልጉ ተቋማት ስለሚሰጡት አገልግሎት ከተገልጋዮቻቸው በተወሰነ የጊዜ ልዩነት አልያም ማሻሻያ ማድረግ በፈለጉ ጊዜ አስተያየትን ይጠይቃሉ። በሚኖራቸው የሥራ ሒደትና ለውጥ የመረጃ ክፍተትና መጉላላት እንዳይኖር ይጠነቃቀሉ ፡፡

በዚህም ምክንያት አንዳንድ ተቋማት የረጅም ጊዜ ደንበኞቻቸውን ቤተሰብ የሚል ስያሜ ሲሰጧቸው ተገልጋዮች ደግሞ ይህንን ቤተሰባዊነት በሙሉ ፍቃደኝነት ይቀላቀላሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ተቋማቱ አስቀድመው ያፈሯቸውን ደንበኞች ከማቆየት ባሻገር አዳዲስ ደንበኞችን ለማፍራት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

ለዜጎች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ፣ መልካም አስተዳደርን የሚያጎለብት እና ለሀገር ዘላቂ ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያደርግ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ማሳደግ የሀገሪቱን ገጽታ ከመገንባት አልፎ ለዜጎች እፎይታን በመስጠት ዜጎች የሀገር ፍቅር ስሜቶቻቸው እንዲያድግ ያደርጋል፡፡

ሁሉም ተቋማት ለሕዝብ ጥሩ እና ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን መስጠት፤ ተደራሽ መሆን፤ ተመጣጣኝነትን እና ጥራታቸውን የጠበቁ አገልግሎቶችን መስጠት አለባቸው፡፡ ሁሉም የመንግሥት ግብይቶች እና ስራዎች ውስጥ ግልጽነት፤ ተጠያቂነት እና ታማኝነት ማሳደግ፤ የመንግሥት ሠራተኞችን በስልጠና እና በልማት ፕሮግራሞች ክህሎትና ብቃትን ያለማቋረጥ ማሳደግ፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ውጤታማነትን ለማሻሻል ቴክኖሎጂን እና ፈጠራን መጠቀም ያስፈልጋል።

ከሌሎች ሴክተሮች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በሀገሪቱ የሚስተዋሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ችግሮችን ለመፍታት፤ የዜጎችን በተለይም የተገለሉ እና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብትና ደህንነት ማረጋገጥ እንዲሁም በሁሉም የመንግሥት እርምጃዎች እና ውሳኔዎች የሕግ የበላይነትን እና የሰብአዊ መብቶችን በማክበር ግልጋሎቶችን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በገበያ ልማትና በደንበኛ አያያዝ ላይ እውቀት እና ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች "የማርኬቲንግ መርህ እና የሰው ልጅ ባህሪም የሚመሳሰል ነው፤ እርሱም አንድ ሰው የወደደውን ነገር ለሌላ ለአንድ ሰው ሲያጋራ ቅር የተሰኘበትን ግን ለአስራ አንድ ሰው ያሰራጫል" የሚል ነው ፤ ከዚህ አንጻር የደንበኞች እርካታን ተቀዳሚ ግብ በማድረግ ሥራዎችን መከወን ለነገ የሚተው ሳይሆን ዛሬ የሚከወን መሆን አለበት እያልኩ ጽሑፌን እቋጫለሁ፡፡

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ያልታየችው ጥበበኛ ትጣራለች

መልካምሥራ አፈወርቅ



**ልጅነት ደጉ ...**

የብርቱ ገበሬ ልጅ ነች፡፡ ቤተሰቦቿ ኮረሪማና ቡና ያመርታሉ፡፡ ለቤቱ ብቸኛ ልጅ ናት፡፡ ሁሉም እንደ ዓይኑ ብሌን ያያታል፡፡ ትንሸዋ እቴነሽ ፈጣንና ተጫዋች ነች፡፡ የታዘዘችውን ለመፈጸም አትዘገይም፡፡ በትምህርት ውሎዋ እሷ ከጓደኞቿ ትለያለች፡፡ ስትጫወት፣ ስታወራ ቀልጠፍ ማለቷ ከሁሉ ዓይን ጥሏታል፡፡

ይህን የሚያውቁት አባቷ ዘወትር ይጨነቃሉ፡፡ ቅልጥፍናዋ ከልጅነቷ ተዳምሮ ትኩረት እንዳትስብ ስጋታቸው ነው፡፡ ልጃቸውን የሚያዩ ብዙዎች በሌላ እንዳያስቧት፣ በድንገት ጠልፈው እንዳይወስዷት ይፈራሉ፡፡ ምን አልባት እንዲህ ከሆነ ስማቸው ይጠፋል፤ ክብራቸው ይዋረዳል፡፡

ከቀናት በአንዱ ግን አባት በድንገት ወሰኑ ፡፡ አሁን ልጃቸው እያደገች ኮረዳ እየሆነች ነው፡፡ ቆይታ ደግሞ ዕድሜ ታከላለች፡፡ ውበቷ ይታያል፣ ወጣትነቷ ይማርካል፡፡ ስለዚህ ማግባት፣ መዳር አለባት፡፡ ትዳር ከያዘች ለእሷም ለእሳቸውም ክብር ነው፡፡

**ሙሽሪት ልመጂ ...**

እቴነሽ ወንድሙ ስድስተኛ ክፍል እንደገባች ለትዳር ተጠየቀች። ይሄኔ አባት የልባቸው ሞላ፡፡ አብሯቸው ከኖረው ስጋት ድነው ‹‹እፎይ!›› አሉ፡፡ የዛኔ አስራ አራተኛ ዓመት ዕድሜዋን መጀመሯ ነበር፡፡ ትንሸዋ ልጅ ትዳር ስትይዝ ሁሉም ነገር ቀረ። የልጅነት ሩጫዋ፣ ሳቅ ጨዋታዋ ተገታ፡፡ ጅምር ትምህርቷ ተቋረጠ፡፡

ጎጆ ስትወጣ ለባሏ ጥሩ ሚስት ሆነች፡፡ ‹‹ሙሽሪት ልመጂ›› ያሏት ዘመዶቿ ከእሷ ቁም ነገርን ሽተው ብዙ ጠበቁ። 1977 ዓ.ም የጫጉላ ጊዜዋ ሆነ፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላ የመጀመሪያ ልጇን ታቀፈች፡፡

አሁን እቴነሽ ጥሩ ወይዘሮ ሆናለች፡፡ ስለ ትዳርና ጎጇዋ እንጂ ስለ ትምህርቷ፣ ሮጦ ስለመጫወት አታስብም። የመጀመሪያ ልጇ ትንሽ ከፍ እንዳለች ሁለተኛዋን አረገዘች። እሷን አይታ ሳትጠግብ ሶስተኛው ተደገመ፡፡ በአጭር ጊዜ አከታትላ የወለደችው እናት ኑሮን ከልጆች አስማምታ ማደሩ ይከብዳት ያዘ፡፡

የእቴነሽ ባለቤት ጉራጌ ሀገር ተወልዶ ያደገ ነው። ልጆች ሲበዙ፣ ቤተሰቡ ሲሰፋ ሕይወትን በተሻለ ሊኖር አሰበ፡፡ ሃሳቡን እውን ለማድረግ የመጀመሪያ ምርጫው ወደ ሀገሩ ጠቅልሎ መግባት ነበር፡፡

እቴነሽና ባለቤቷ ጅማን ለቀው ወደ ጉራጌ ምድር ‹‹አጨበር›› አቀኑ፡፡ ስፍራው ለምና አረንጓዴ ነው፡፡ እቴነሽ ቦታውን አልጠላችውም፡፡ በአካባቢው የባለቤቷ እህትና የመጀመሪያ ልጁ መኖራቸውን ታውቃለች፡፡ በስፍራው ከአንድ ዓመት በላይ እንደቆዩ እቴነሽ አራተኛዋን ልጅ ነፍሰጡር መሆኗን አወቀች፡፡ አልከፋትም፡፡ እርግዝናው እየገፋ አራት ወራትን አስቆጠረ፡፡

**የቀን ክፉ . . .**

አንድ ቀን በእነ እቴነሽ ቤት ከባድ ኀዘን ወደቀ፡፡ የትዳር አጋሯ፣ የልጆቿ አባት ‹‹አለኝ›› የምትለው መከታዋ በድንገት ሕይወቱን በሞት ተነጠቀ፡፡ እቴነሽ ትይዘው፣ ትጨብጠው ጠፋት፡፡ አሁን ከትውልድ ሀገሯ ርቃለች። እዚህ በቅርብ የምትጠራው ወዳጅ፣ ዘመድ የለም፡፡ ለሀገሩ ባዳ፣ ለሰው እንግዳ የሆነችው ነፍሰጡር ኀዘኗ ከፋ፡፡ ልጆቿን በትካዜ እያየች ስለነገው ተጨነቀች፡፡

ባለቤቷ ከተቀበረ ጥቂት ቀናት በኋላ የጎረቤት እግር ቀነሰ፡፡ ‹‹እንዴት ዋላችሁ፤ እንዴት ከረማችሁ?›› የሚል ጠፋ። ይሄኔ በወጉ አፋቸውን ያልፈቱ ልጆችን የየያዘችው እቴነሽ በባዶ ቤት ባዶነት ተሰማት፡፡ አባወራው የተወላት ሀብት ንብረት ከእጇ የለም፡፡ ወጣ ብላ ‹‹አበድሩኝ፣ አጉርሱኝ›› ለማለት የምትግባባበትን ቋንቋ አታውቅም፡፡ ችግር ሰተት ብሎ ቤቷ መግባቱን እያየች በጥልቅ ኀዘን ተዋጠች፡፡

እቴነሽ ሆዷ እየገፋ፣ ወሯ እየደረሰ ነው፡፡ ባለቤቷ በሌለበት በባዶ ቤት መውለዷን ስታስብ አስቀድሞ ሆድ ባሳት፡፡ የሚሆነው ከመሆን አላለፈም፡፡ በችግርና ኀዘን መሀል በሰላም ወልዳ ልጇን ታቀፈች፡፡ የአራስ ቤት ቆይታዋ መልካም አልሆነም፡፡ ‹‹እንኳን ማርያም ማረችሽ›› የሚላት የሚጎበኛት ጠፋ፡፡ በለቅሶ ብዛት ዓይኖቿ ደከሙ፡፡ አንጀቷ በጀርባዋ የተጣበቀ መሰሎ ተሰማት፡፡

በአራስ ቤት ባዶነት፣ ብቸኝነት ይከብዳል፡፡ የዘመድ አዝማድ ጥየቃ፣ የወዳጅ ባልንጀራ እጅ ይናፍቃል፡፡ እቴነሽ ለቀናት ደጁን እያየች ሰው ጠበቀች፡፡ ‹‹ወድቀሽ ተነሺ›› የሚላት አልተገኘም፡፡ አሁን ከእሷና ከልጆቿ በቀር ቤቷ ባዶ ነው። እንደ ወጉ ገብቶ ያያት፣ የጠየቃት የለም፡፡ እቴነሽ ውስጧ በኀዘን ረመጥ ጋየ፡፡ ለቀናት በትኩስ ዕንባ ታጠበች፡፡ መሽቶ በነጋ ቁጥር ደጋግሞ ሆድ ባሳት፡፡

**መከራን በዘዴ**

ውሎ ሲያድር እሷና ልጆቿ ረሃብ ጎበኛቸው፡፡ አሁን እቴነሽ ታጠባለች፡፡ ለህጻኗ ወተት፤ ለልጆቿና ለእሷ ምግብ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ምንም ተነስታ ወደ ጓሮ አቀናች፡፡ ገብስ ተቆልቶ የቀረው ገለባ በጆንያ ተሞልቷል፡፡ ገለባው ከብቶች ሲወልዱ ለመኖ እንዲያግዝ የተቀመጠ ነው፡፡ እቴነሽ ይህን አሳምራ ታውቃለች፡፡ ገለባውን በሰፌድ ማበጠር፣ ማንጓለል

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ያልታየችው ጥበበኛ...

ከ16ኛው ገጽ የዞረ

ያዘች፡፡ ጥቂት የገብስ ፍሬዎችን አላጣችም፡፡

ያገኘችውን ገብስ አጠራቅማ እንደ ቅንጬ ቀቀለችው፡፡ ደጋግማ ገለባውን አነፈሰች፡፡ አሁንም ጥቂት ገብስ አላጣችም። እሱኑ ከልጆቿ ጋር ተቃምሳ ቀናትን አለፈች፡፡ ውሎ አድሮ ግን ገብሱ ነጥፎ ገለባው ብቻ ቀረ፡፡

እቴነሽ ዕብቁን «ይቅርብኝ» ብላ አልተወችውም፡፡ ላይ ላዩን አንጓላ የሚቀረውን ድቃቂ ከሰው ጓሮ ለቅማ ባመጣችው ጎመን እየቀቀለች ለልጆቿ አጎረሰች፡፡ አንድ ቀን ግን ጡቷ ደረቀ። ትንሽዋ ልጅ ልትራብ ሆነ፡፡ ዕፍኝ የማትሞላ ገብስ ፈጭታ እንደ ወጉ አጥሚት ሠራች፡፡ ልጇ ከጡቷ በረከት እንድታገኝ የፈጠረችው ብልሀት ነበር፡፡

**ሆድ ስባሰው...**

እቴነሽ በአካባቢው «ይሁን» ብላ መቀመጥ አልፈለገችም። ሰውነቷ የበረታ ሲመስላት ብድግ ብላ መጥፋት ፈለገች፡፡ ትልቋ ልጅ ከአክስቷ ዘንድ ናት፡፡ የእሷን ተከታይ ደግሞ አዲስ አበባ ያሉት አክስት ወስደዋታል፡፡ አንድ ማለዳ እቴነሽ የልቧን ልትፈጽም ቆረጠች፡፡ በባዶ ሆዷ፣ ድንገት ጎጆዋን ዘግታ ከቤት ወጣች፡፡ አሁን ርቃ ልትሄድ፣ ልትጠፋ ወስናለች፡፡

ሁለቱን ልጆች ይዛ መንገድ እንደጀመረች አንድ ሰው አግኝቶ አስቆማት፡፡ የባለቤቷ የመጀመሪያ ልጅ ነበር፡፡ ገና እንዳያት ልቡ ጠረጠረ፡፡ ወዴት እንደምትሄድ ደጋግሞ ጠየቃት። እቴነሽ ውስጧ ተከፍቷል፡፡ መላ አላጣችም፡፡ አዲስ አበባ ያሉት የባሏ እህት ልብስ ሊገዙላት እንደ ቀጠሯት ነገረችው፡፡

የባለቤቷ ልጅ የህጻናቱን አብሮ መሄድ አልወደደም። ደርሳ እስክትመለስ አንደኛዋን ከእጇ ተቀበላት፡፡ እቴነሽ እንዷን ህጻን እንደ ያዘች አዲስ አበባ ዘለቀች፡፡ ስፍራው ስትደርስ ሁኔታዎች ግራ አጋቧት፡፡ የአዲስ አበባ ፀሀይ ጨለማ ሆነባት። ከገጠር ወጥታ መሀል ከተማ መግባቷ ለእሷ ፈተና ነበር፡፡ እንደ እንግድነቷ ለጥቂት ቀናት ከባሏ እህት ቤት አረፈች፡፡ ውሎ አድሮ ግን መቀጠል የማያስችሏት ምክንያቶች ተፈጠሩ፡፡ እቴነሽ አሁንም በድንገት ወሰነች፡፡ በጉልበቷ ሰርታ ለማደር «ጢያ» ከተባለ ሀገር አመራች፡፡ ጢያ ከአዲስ አበባ በኪሎ ሜትሮች ይርቃል፡፡ «ለሀገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ» የሆነችው እቴነሽ አሁንም ሕይወትን እንደ አዲስ ልትጀምረው ግድ አላት፡፡

አራት ልጆቿን በአንድ ቤት ማሳደግ ያልሆነላት ሴት ጉልበቷን ከፍላ፣ ላቧን ጠብ አድርጋ በምታድርበት ቤት ተቀጠረች፡፡ ሁሌም ልጆቿ በዓይኗ ውል ይላሉ፡፡ በሞት ያጣችው ባለቤቷ፣ ያለፈችበት ውጣ ውረድ በትዝታ ይፈትኗታል፡፡ አስር ዓመታት በቆየችበት የሠራተኝነት ሕይወት ብዙ መከራን አይታለች፡፡

ቀጥረው የወሰዷት የአዲስ አበባ ነዋሪ የሀገሩ ተወላጅ ናቸው። ሰውየው ጢያ ላይ የበዛ ሀብት አፍርተዋል። ንብረታቸው በታማኝ ሰው እንዲጠበቅ፣ ይሻሉ፡፡ ለዚህ የታጩችው እቴነሽ ከከተማው በሚርቅ አንድ የገጠር ወንዝ ዳርቻ ከነልጆቿ ተጓዘች። በርካታ ከብቶችና የጋማ እንስሳት የእሷ ሃላፊነት ሆኑ፡፡

ከአንድ ውሻ በቀር ማንም ጎኗ የሌለው ሴት ጉልበቷን እየገበረች ጥበቃዋን ቀጠለች፡፡ ጭው ባለው መንደር ታዛቢ በሌለበት ዓለም እቴነሽ ጉልበቷን አትሰስትም፡፡ ወፍ ሳይንጫጫ እበት ከበረት ትዝቃለች፣ አውድማ ትለቀልቃለች፣ እንሰት ቆርጣ ትፍቃለች፡፡ ለእሷ አሁንም በማታውቀው ሀገር ዝቅ ብሎ ማደር ብርቋ አልሆነም፡፡

ጉልበቷ እንጂ ቀለቧ ያልታሰበላት አገልጋይ ኑሮዋን ለማሸነፍ አትሆነው የለም፡፡ ስንደዶ እየቀጨች፣ ርቃ ሄዳ ጸጉር ትሠራለች። ባገኘችው ገቢ ልጆቿን እያጎረሰች አዲስ ቀን ትናፍቃለች፡፡ በዚህ ሁሉ መሀል ሰዎች ሊጎዷት፣ ሽፍቶች ሊዘርፏት ሞክረዋል። ጥንካሬዋ ብርታት ሆኗት ብዙ የፈተና ቀናትን በድል መሻገር ችላለች፡፡

**የሰባቶች እናት...**

ይህን ችግር ለማምለጥ የገባችበት፣ ሶስት ልጆችን ያፈራችበት ሁለተኛው ትዳር አልደላትም፡፡ እቴነሽ አጋር ይሆነኛል ብላ ያገባችው ሰው ሌላ ትዳር ነበረው፡፡ አሁን በአራቱ ላይ ሶስት ልጆችን አክላ የሰባቶች እናት ሆናለች። በቂ መተዳደሪያ ለሌላት ሴት እንዲህ መሆኑ ይከብዳል፡፡ ለእንጀራ ስትል የመጣችበት ኑሮ ያስገኘላት ቢኖር ሶስት ልጆቿን ብቻ ነበር፡፡ አንድ ቀን እቴነሽ ብዙ ካየችበት የጢያ ሕይወት ልትላቀቅ ወስና ጓዟን ሸከፈች፡፡ እግሮቿ ወደ አዲስ አበባ መለሷት፡፡

አዲስ አበባና እቴነሽ ዳግም ሲገናኙ ከጭንቅ ጋር ሆነ፡፡ አሁንም ለዚህች ሴት ይህች ከተማ ባህር ውስጥ እንደ መስመጥ ሆነባት፡፡ ዛሬም ትጠጋበት ዘመድ፣ ትጠራው ወዳጅ፣ ጓደኛ የላትም፡፡ አሁንም ያላት ምርጫ በጉልበቷ ማደር ብቻ ነው። ተመልሳ የቤት ሠራተኛ ሆነች፡፡ ጥቂት ጊዜ የቆየችበት ሥራ ብቻውን የሚያዋጣ አልሆነም፡፡ ልጆቿን አብልታ ለማሳደር ቤት ተከራይታ መኖር ግድ አላት፡፡

እቴነሽ አዲስ አበባ የገባች ሰሞን ያልሆነችው የለም። የዛኔ የአንድ ኪሎ በቆሎ ዋጋ አራት ብር ነበር፡፡ እሷ ይህን የመግዛት አቅም የላትም፡፡ ውሎ አድሮ ችግር ብዙ አስተማራት። የወፍጮ ቤት ጥራጊ በጥቂት ወጪ መግዛት ልምዷ ሆነ፡፡ ጥራጊውን፣ ከወረቀቱ፣ ከአሸዋውና ከአሰሩ ለይታ፣ ነፍታና አበጥራ እንጀራ ማድረግ ቀላል አይደለም፡፡ ይህ ሁሉ ታልፎ ብጣሪው እንጀራ ከሆነ ግን ለዓይንና ጉሮሮ ይከብዳል፡፡ እሷና ልጆቿ ከዚህ ሌላ በልቶ ለማደር ምርጫ የላቸውም፡፡

**ስለእንጀራ ...**

ሶስት ልጆቿ ሁሌም የእሷን እጅ ይናፍቃሉ፡፡ አሻሮ እየቆላች፣ ከጉልበት ሥራ እየዋለች ከምታገኘው ጥቂት ገቢ ለዕለት ጉሮሯቸው ይዛ ትገባለች፡፡ ሲነጋ እነሱን ከቤት ትታ ከጉልበት ሥራዋ ትገኛለች፡፡ እቴነሽ የተጠየቀችውን ለመሥራት ሁሌም ታዛዥ ናት፡፡ ጉልበቷን አትሰስትም፡፡ ከአቅሟ በላይ ሲጭኑባት "ለምን?" ብላ አትጠይቅም፡፡

አንድ ቀን ለሥራ ከሄደችበት ቤት ሃምሳ ኪሎ በቆሎና ሃያ አምስት ኪሎ ገብስ እንድትቆላ ተሰጣት፡፡ እቴነሽ ወገግ ካለው እሳት ብረት ምጣዱን ጥዳ መቁላት ጀመረች። ብዛት ያለው እህል በእሷ አቅም ተቆልቶ እንዳለቀ ራሷን ስታ ወደቀች። ማግስቱን ግን ከውሎዋ አልቀረችም፡፡ ይህን ሁሉ ቆልታ የሚከፈላትን ሃምሳ ብር ለማግኘት ልቧን ደግፋ ከቦታው ተገኘች፡፡

እቴነሽ አውደ ዓመት በደረሰ ጊዜ ጉልበቷን የሚሹ ብዙ ናቸው፡፡ በቀን ሰባት ቤት ገብታ የዓመት በዓሉን እንጀራ በእንጨት ትጋግራለች፡፡ ለእሷ የዕለት ጉርሷ ነው፡፡ ከየቤቱ የሚሰጣት እንጀራ ለልጆቿ ይሆናል፡፡ የምታገኘው ጥቂት ክፍያ ተጠራቅሞ ለቤት ኪራይ ይውላል፡፡

እቴነሽ ሰባት ልጇቿን ለማሳደግ ከስታ ጠቁራለች፤ተርባ ተጠምታለች፡፡ ወድቃ ተነስታለች፡፡ ማንም የጎደጎደ ዓይኗን አይቶ፣ ማድያት የወረሰው ፊቷን ቃኝቶ ኑሮዋን መገመት አይሳነውም፡፡ ልጆቿ ከፍ ባሉ ጊዜ ጥቂት ነገሮች ይዛ ጉልት መሸጥ ጀመረች፡፡ እነሱም ከትምህርት መልስ የሚሸጠውን በአቅማቸው በየጉልቱ እያዞሩ ያግዟት ያዙ፡፡

እንዲያም ሆኖ ከቤት የሚላስ ፣ የሚቀመስ ሊጠፋ ይችላል። በእነቴነሽ ቤት ጦም ውሎ ጦም ማደር ብርቅ አይደለም። አንዳንዴ ለልጆቿ ባዶውን ጎመን ጨው ጨምራ፣ ቃሪያ ጣል አድርጋ ትሰጣቸዋለች፡፡ አያዝኑም፣ አይከፉም፡፡ በፍቅር ተቃምሰው በጨዋታ አዋዝተው ምሽቱን ያልፉታል፡፡

ከልጆቿ አንዷ የእናቷን ሸክም ለማቅለል ከአምስተኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ በቀን ሥራ ተሠማርታለች፡፡ ድንጋይ በባሬላ ተሸካሚዋ ልጅ እናቷ ትናንት የተበደረችውን ዛሬ እየከፈለች፣ ለኑሯቸው ታገለች፡፡ አሁንም የጎደለው አልሞላም። ቤተሰቡ በአቅም ማጣት በቤት ኪራይ ይንገላታል፡፡

ከቀናት በአንዱ አንዲት መልካም ሴት ወደ አርሷ ቀርበው የሚበጃትን አመላከቷት፡፡ እቴነሽ የቀበሌ መታወቂያ አወጣች። ይህን ተከትሎ ልጆቿን እያስተማረ የሚያሳድግ የውጭ ድርጅት አገኘች፡፡ ሁለቱ አዳሪ ትምህርት ቤት ገቡ፡፡ ሌሎች በየዘመዱ ቤት ኑሯቸውን ቀጠሉ፡፡ እቴነሽ ሸክሟ ቀለለ፡፡ ፈጣሪዋን አብዝታ አመሰገነች፡፡

ከድርጅቱ ጋር የተጀመረው ግንኙነት ፍሬው መልካም ሆነ። በልጆቿ መነሻ ሕይወቷ የተጎበኘው እናት የእጅ ሙያዎችን የመማር አጋጣሚ ተፈጠረላት፡፡ ይህ ጊዜ ለሥራ ወዳጇ፣ ለብርቱዋ እቴነሽ መልካም የሚባል ነበር፡፡ እሷን ከመሰሉ ሴቶች ጋር ተደራጅታ በጀመረችው ሥልጠና ከሌሎች በላቀ ውጤታማ ሆነች፡፡

እሷና አጋሮቿ በሚሰሯቸው የእጅ ሙያዎች የዕለት ገቢያቸውን አላጡም፡፡ በሥልጠና የቀሰሙት ዕውቀት ለእንጀራቸው ማግኛ ሆኖ ትኩረት አገኙ፡፡ በየጊዜው የእጆቻቸው ጥበቦች ይሸጡ፣ ይጎበኙ ያዙ፡፡ ሶስት ዓመታት በመልካም ሁኔታ አለፉ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ግን ድርጅቱ በድንገት መዘጋቱ ተሰማ፡፡ እንዲህ መሆኑ ለእንጀራ ፈላጊዋ እቴነሽ አስደንጋጭ ነበር፡፡

**ዛሬን...**

እቴነሽ ተመልሳ ወደ ጉልበት ሥራ መግባት ከበዳት፡፡ ይህን እያሰበች ባለበት ጊዜ አምሳለ የምትባል አንዲት ሴት ሥራውን የምትቀጥልበትን መንገድ ጠቆመቻት፡፡ እቴነሽ ምክሯን ተቀብላ ሞከረችው፡፡ የምትሠራቸው የአንገት፣ የእጅና የጆሮ ጌጦች ሞገስ አገኙላት፡፡ ያዩ፣ የጠየቁ ሁሉ ይገዟት ጀመር፡፡

ውሎ አድሮ ግን በእጇ ሙያዎቿ ብቻ ቀሩ፡፡ እንደቀድሞው የምትሸጥበት ዕድልና ቦታ አጣች፡፡ እቴነሽ ውብ ጌጦቿ ለዓይን ይማርካሉ፡፡ ዋጋዋ አነስተኛ ነው፡፡ እነሱን ሸጣ የምታገኘው ገቢ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ እንዲያም ሆኖ ጥበበኛ እጆቿ ከሥራ አልታቀቡም፡፡ አሁን ከገበያ አገናኝቶ፣ ከእንጀራዋ የሚያውላትን ወገን ትሻለች፡፡

**መልካም ዓይኖችን ፍለጋ ...**

ዛሬ ልጆቿ በአቅማቸው ተምረዋል፡፡ አብዛኞቹ ግን ሥራ ላይ አይደሉም፡፡ ተአምረኞቹ፣ ጥበበኞቹ የእቴነሽ እጆች ሥራ ላይ ናቸው፡፡ ሆኖም የቤት ኪራዩ ይከብዳታል፡፡ ጤፍ አስፈጭቶ እንጀራ መቁረስ ይቸግራታል፡፡ ጠንካራዋ ሴት እዩኝ፣ ጎብኙኝ እያለች ነው፡፡ በእሷ እጆች ያልተመነዘረ ጥሬ ገንዘብ፣ ያልታየ ድንቅ ውበት አለና፡፡

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ጠንካራ ማንነት እንዴት ይገነባል?

**አስናቀ ፀጋዬ**

ጠንክራችሁ ሥሩ ስትባሉ ‹‹ደሞ ይሄ ለእኛ ሊነገረን ነው›› ልትሉ ትችላላችሁ። ሌሎቻችሁ ደግሞ ጠንክሮ ስለ መሥራት መንገር ለመኖር ምግብ መብላት አለባችሁ፤ ለመኖር ውሃ መጠጣት አለባችሁ እንደ ማለት ነው ብላችሁ ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ ልክ ናችሁ። ግን አንዳንዴ በሕይወታችን እንዘናጋለን። ሕይወት ተደጋጋሚና አሰልቺ ትሆንና ጠንክረን ከመሥራት እንሰንፋለን፡፡ በቃ! ሕይወት አሰልቺ ይሆንብናል፡፡ ስለዚህ የሚያባንነን፣ የሚያነቃንና ጠንክረን መሥራት እንዳለብን የሚያስታውሰን ነገር ያስፈልገናል፡፡

ጠንክረህ የምትሠራው ገንዘብ ለምታገኝበት ነገር ብቻ አይደለም፡፡ ለትምህርትህም ጠንክረህ መሥራት አለብህ፡፡ ትዳርህን የተሳካና ጥሩ ለማድረግ ጠንክረህ መሥራት አለብህ፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ደስተኛ ለመሆን መጠንከር አለብህ፡፡ እንዴት መጠንከር እንዳለብህ ማወቅ ከፈለክ ደግሞ ይኸውልህ ... በቃ! በሁሉም በኩል የተሳለ ሰይፍ መሆን አለብህ። ጠንካራ ማንነት ወይም ጠንክሮ መሥራት ከሰማይ ወርዶ እጅህ ላይ ዱብ የሚል ነገር አይደለም። እየገነባኸው፣ እየመሠረትከውና እያሳደከው የምትሄደው ነገር ነው። እንዴት ጠንካራ ማንነት ልገንባ፣ እንዴት ወጥሬ ልሥራ፣ እንዴት ጠንካራ ልሁን ካልክ ግን ይኸው ይህን ጽሑፍ አንብብ፡፡

ተሰጥዖ የለኝም አትበል፡፡ ስቴፈን ኪንግ የተባለ ደራሲ ‹‹ተሰጥዖ እንደገበታ ጨው ርካሽ ነው። ታላቁን ሰው ስኬታማ የሚያደርገው ጠንክሮ መሥራቱ ነው›› ይላል፡፡ ከተሰጥዖ በላይ ጉልበተኛ የስኬት ምስጢር አለ፤ ጠንክሮ መሥራት የሚባል። አንዳንዴ በዙሪያህ ያለውን ነገር ተመልከት እስኪ። ካንተ በእውቀት ያነሱ፣ ማንም የማይደግፉቸው፣ ገንዘብ ታበድራቸው የነበሩ፤ ብቻ ያልጠበካቸው ሰዎች አሁን ተቀይረውና ከፍ ብለው አንተን ከላይ ወደታች እያዩህ ነው፡፡ አንድ ደራሲ ‹‹ከታሪክ የምንማረው ሰዎች ከታሪካቸው አለመማራቸውን ነው›› ይላል። አሁንም በልፋቱ የበለጠህን ሰው ‹‹አይ እሱ እኮ ዘመድ አግኝቶ ነው፡፡ ሙስና ሠርቶ ነው›› ትላለህ። አሁን ጥያቄው ከኋላህ መጥቶ የተቀየረውን ሰው አይተህ ሰበብ ታበዛለህ፤ ወይስ ራስህን ትቀይራለህ? ነው፡፡ ጥያቄው ይሄ ብቻ ነው፡፡

አዳራሹ ከአፍ እስከ ገደፉ በሰዎች ተሞልቷል። ሁሉም ትኬት ገዝቶ ገብቷል፡፡ መሐል ላይ አንድ ፒያኖ ተጫዋች ቁጭ ብሏል፡፡ በጣም ታዋቂ ነው። የተከበረ ነው፡፡ ሰዎች በሙሉ እርሱን ለማየት ታድመዋል። በተመስጦ ተቀምጠዋል፡፡ ለሰዓታት ፕሮግራሙን አቀረበ፡፡ ፒያኖውን ተጫወተ፡፡ ሰዎች በተመስጦ ሆነው አደመጡት፡፡ ፕሮግራሙ አለቀ፡፡ በአዳራሹ የነበረው ሰው በሙሉ ተነስቶ አጨበጨበ። አደነቀው፡፡ መጨረሻ ላይ ይህ የፒያኖ ተጫዋች ዞር ሲል ከኋላው አንድ ወጣት ልጅ አጠገቡ ቆሞ አየው። ፒያኖ ተጫዋቹ እድሜው ወደ አርባዎቹ መጨረሻ ተጠግቷል፡፡ ወጣቱ ምን አለው? ‹‹እኔ እንዳንተ ፒያኖ መጫወት ብችል እድሜዬን፣ ጉልበቴን፣ ሁሉ ነገሬን አሳልፌ እሰጥ ነበር›› አለ። ፒያኖ ተጫዋቹ መለሰ ‹‹እኔም ብሆን ያደረኩት እርሱን ነው›› አለው፡፡

በዚህ ዓለም ላይ በጣም የምትፈልጉት ስኬት ካለ በጣም ከባድ ላብ ሊያልባችሁ ይገባል። ደም መትፋት አለባችሁ፡፡ መልፋት አለባችሁ። መጣር አለባችሁ፡፡ ጠንክራችሁ መሥራት አለባችሁ። ጠንክሮ ያልሠራ ሰው ከፍታው ላይ መውጣት አይችልም፡፡ አየህ ወዳጄ! ያንተ ሕልም ሙሉ አቅምህን የሚጠይቅ ከሆነ ሙሉ አቅምህን ትሰጣለህ፡፡ ማልመጥና መቀለድ የለም፡፡ ጠንክረህ ትሠራልህ፡፡ ሁሉም ቢሆን ተራ ሕልም የለውም። ሁላችንም የምንፈልገው ነገር አለ። ጥልቅ መሻት አለ፡፡ የሆነ ማሳካት የምንፈልገው ነገር አለ፡፡ እሱን ለማድረግ ግን ጠንክሮ መሥራት ወሳኝ ነው፡፡

ሰዎች እንዲሁ ሊፈልጉህ አይችሉም፡፡ አንተን ለመፈለግ ወይም አንቺን ለመውደድ ምክንያት ይፈልጋሉ፡፡ ታዲያ ምን ይሻላል? መጀመሪያ ራሳችንን መውደድ፡፡ ራስህን ስትወድ በብዙ ነገር ላይ ትጠነክራለህ፡፡ ልበ ሙሉ ትሆናለህ፡፡ ብዙ ነገሮችን ያለሰው እርዳታ ታሳካለህ፡፡ ያኔ በስንፍናህ ጊዜ ዞር ብለው ያላዩህ ሰዎች ምን እናግዝ፣ ከጎንህ ነን ይሉሃል፡፡ አየህ! ይህ የሰው ፀባይ ነው፡፡ ምንም ከሌለህ፣ ልፍስፍስ ከሆንክ ብትንፈራፈር እንኳን አያነሱህም፡፡ ዞር ብለው አያዩህም፡፡ ስለዚህ ከሰው መጠበቁን አቁመህ ወደ ራስህ አተኩር፡፡ ጠንካራ ጎንህ ላይ ጠንክረህ ሥራ፡፡ ሕልምህን አሳካ፡፡ ማንነትህን በሥራ ወይም በትምህርትህ አሳይ፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም ምርጫ የለህም፡፡

ልፋቱ ያለው መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ አየህ! ምንም ነገር እስክትለምደው ድረስ ከባድ ነበር። መራመድ እንኳን ከባድ ነበር፡፡ መፃፍ ከባድ ነበር። እጅህ እስኪጠነክር ትቸከችክ ነበር፡፡ ጠንክሮ መሥራትም ልምምድ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ውስጥህ እስኪለምደው ታገስ፡፡ ለራስህ ጊዜ ስጠው፡፡ ሮኬት ጉልበት የሚያወጣው መጀመሪያ ሲወነጨፍ ነው፡፡ አየህ! የመሬትን ስበት አሸንፎ አየሩን እስኪቀላቀል ነው የሚለፋው፡፡ አንተም ሕይወትህ መቀየርና መለወጥ እስኪጀምር ድረስ ጠንክረህ መሥራት አለብህ፡፡ ከዛማ ሥራውን ስታውቅበት ውሃ እንደመጠጣት ቀላል ይሆናል። ጠንክረው የሚሠሩ ሰዎች ‹‹ልፋቴ እኮ በጣም ቀላል ነው›› ቢሉህ እንዳትደነቅ፡፡ ስለለመዱት ነው። አንተም ጠንክሮ መሥራቱን ልመደው፡፡ ምንም አትሆንም፡፡

በቃ በርታበት፡፡ ጠንክረህ አጥና፡፡ ረጅም ሰዓት ቁጭ በልና አስብ፡፡ እንዴት ሕይወቴን ልቀይር በል፡፡ ጠንክረህ እንደምትሠራ ጠንክረህ አስብ፡፡ ያለበለዚያማ ዝምብም እኮ ትለፋለች። ልፋቷ ግን መና ነው፡፡ እንደ ንብ ልፋት፡፡ ማር ለሚሰጥ ነገር ማለት ነው፡፡ ሕይወትህን ለሚቀይር ነገር መልፋት አለብህ፡፡ ትርጉም ላለው ነገር ጠንክረህ ሥራ፡፡ እሱ ነው ከፍ የሚያደርግህ፡፡ እሱ ነው የሚቀይርህ። ከሰው በላይ የሚያደርግህ። ከናቁህ ሰዎች በላይ ከፍ የሚያደርግህ ጠንክረህ መሥራትህ ነው፡፡ ‹‹የውሃ ጠብታ እያደር ድንጋይ ይበሳል›› ይባላል። እንዴት ነው፣ ቆይ እጅ የማይሰብር ውሃ ድንጋይ የሚሰብረው? ግን አትርሳ ያ ጠብታ ተመሳሳይ ቦታ ላይ ዝምብሎ ከወረደ የሚያርፍበት ቦታ ብቻውን መዳከሙ አይቀርም። ድንጋዩ መፈርከሱ አይቀርም፡፡

ጠንክረህ ስትሠራ የመጀመሪያው ወር ደሞዝህ ሕይወትህን ላይቀይረው ይችላል። ኧረ! የአንድ ዓመት ደሞዜም ቢሆን ተጠራቅሞ ቢሰጠኝ እንዴት አድርጎ ነው ሕልሜን የሚያሳካልኝ እያልክም ይሆናል። ጠንክረህ ስትሠራ ግን የሆነ ሰዓት የአምስት ዓመት ደሞዝህ በአንዴ የወር ደሞዝህ የሚሆንበት ቀን ይመጣል፡፡ ከሚከፈለህ በላይ ስትሠራ ከምትሠራው በላይ ይከፈልሃል። አሁን የምታገኘውን ገቢ አይተህ ልፋትህን አትቀንስ፡፡ ነገ የምትደርስበት ነው ወሳኙ፡፡ ስለዚህ ለምን አቅምህን ትሰስታለህ፡፡ በሙሉ አቅምህ ሥራ፡፡ በሙሉ አቅምህ ተማር፡፡ ከዛ በሕይወትህ ላይ ተዓምሩን ታየዋለህ፡፡ ተዓምሩን ራስህ ትመሰክረዋለህ። ልፋትህን መውደድ አለብህ። ማፍቀር አለብህ፡፡ መቀየር አለብህ፡፡ ጠንክረህ ካልሠራህ ግን አትቀየርም፡፡ ካለፋህና ካልጣርክ ምንም ነገር በሕይወትህ ላይ አትጨምርም፡፡

አንድ ሰው ምን አለ መሰለህ፣ ‹‹በሕይወቴ በጣም እየለፋሁ፤ እየጣርኩ ምንም ለውጥ ማምጣት ሲያቅተኝ፣ ነገሮች በፈለኩት መንገድ አልቀየር ሲሉኝ ድንጋይ ፈላጮች ጋር እሄድና ቁጭ ብዬ አያቸዋለሁ፡፡ ድንጋይ ፈላጩ መዶሻ አንስቶ ድንጋዩን ይመታል፤ እኔ ደግሞ ቁጭ ብዬ እያየሁ እቆጥራለሁ፡፡ አንድ . . . ሁለት . . . ሦስት . . . እያልኩ፡፡ መቶ እደርሳለሁ፡፡ የሆነ ቁጥር ላይ መቶ ሃያ ስድስት ላይ ስደርስ ድንጋዩ ይሰበራል›› አለ፡፡ ታዲያ 126ኛው ኃይል ስላለው ይመስለሃል ድንጋዩ የተሰበረው? አይደለም! ፈላጩ ቀድሞ የመታቸው 125 ምቶች ድንጋዩን አድክመውት ነበር፡፡ 126ኛውን ፈላጩ ቀለል አድርጎ ቢልከውም ድንጋዩ መሰበሩ አይቀሬ ነበር።

> **ጠንክሮ መሥራትም ልምምድ ይጠይቃል። ስለዚህ ውስጥህ እስኪለምደው ታገስ። ለራስህ ጊዜ ስጠው፡፡ ሮኬት ጉልበት የሚያወጣው መጀመሪያ ሲወነጨፍ ነው። አየህ! የመሬትን ስበት አሸንፎ አየሩን እስኪቀላቀል ነው የሚለፋው**

አንተም በሕይወቴ እየለፋሁ ነው፣ ጠንክሬ እየሠራሁ ነው፤ ግን ደግሞ አልተለወጥኩም ካልክ 126ኛውን ቀን ጠብቀው፡፡ ሕይወትህ የሚቀየረው የሆነ ሰዓት ላይ ነው፡፡ ታገስ፡፡ ለውጡን ትፈልገዋለህ አይደል? ታገስ፤ ለምን ታቆመዋለህ፡፡ የመጨረሻውን ብርሃን ማየት ከፈለክ ጨለማውን መታገስ አለብህ፡፡ በቃ! ማስታመም አለብህ፡፡ ችግር የለም፤ እበረታለሁ፤ እጠነክራለሁ ማለት አለብህ፡፡ እኔ የምልህ ወዳጄ! እልህ ይዞህ ያውቃል? የሚንቁህና የበታችነት ስሜት እንዲሰማህ የሚያደርጉህ ሰዎች ሕይወትህን የቀን ጨለማ አድርገውት ያውቃሉ አይደል? እሳቱን ስትፈልግ ንብረት ለማውደም ትጠቀምበታለህ፡፡ ስትፈልግ ደግሞ ምግብ ታበስልበታለህ፡፡

ታዲያ ለናቁህ ሰዎች ማንነትህን ለማሳየት ጠንክረህ በስኬትህ የያዘህን እልህ ለምን አትወጣም። የምድራችን ጣፋጭ በቀል በናቁህ ፊት የሚያስከብር ስኬት መጎናፀፍ ነው፡፡ ታዲያ ለምን ጠንክረህ አትሠራም፡፡ ሕይወትህን የሚቀይረው፤ የሆነ ቀን ደስ ብሎህ ያስቀመጥከው ብር አይደለም። ወይ የሆነ ቀን በጥሩ ሙድ የሠራኸው ስፖርትም አይደለም። ወይ ያነበብከው መጽሐፍ አይደለም፡፡ ወዳጄ! ሕይወትህን የሚቀይረው በየቀኑ እየደጋገምክ የምታደርገው ልማድ ነው፡፡ ስኬት ማለት እኮ እየተዘጋጀህ እያለህ እድል ሲመጣልህ ነው፡፡ ስለዚህ በእውቀት፣ በልምድ፣ በገንዘብ ተዘጋጅ፡፡ እድሉ ሲመጣ እንዳንተ የሚጠቀምበት አይኖርም፡፡ ስኬቱ ይምጣና እዘጋጃለሁ ካልክ እየቀለድክ ነው ማለት ነው፡፡ ለጦርነት የምትዘጋጀው እኮ በሠላሙ ጊዜ ነው፡፡

አየህ! አሁን ከጠነከርክና ከበረታህ ከባድ ጊዜያት ባንተ ላይ አቅም አይኖራቸውም፡፡ ምርጥ ጊዜያት ደግሞ ወደ ከፍታው ይወስዱሃል፡፡ አሁን ከጠነከርክና ከበረታህ ከባድ ጊዜያት ባንተ ላይ አቅም አይኖራቸውም፡፡ ምርጥ ጊዜያት ደግሞ ወደ ከፍታው ያንደረድሩሃል፡፡ ጫፍ ያወጡሃል። ጠንክረህ የምትሠራ ከሆነ የትም ብትሄድ ይሳካልሃል። የትም ብትገባ ያልፍልሃል፡፡ በቃ! ጠንካራ ሠራተኛ ከሆንክ ምንም ውስጥ ብትገባ ከፍ ትላለህ። ዝቅ ብትል ትነሳለህ፡፡ ብታጎነብስ ቀና ትላለህ፡፡ ትጋት ያስፈልግሃል፡፡ ጠንክረህ መሥራት ያስፈልግሃል። ስለዚህ ጠንክረህ ሥራ፡፡ ልፋትህንም አታቁም፡፡ አስተውል! የተለወጡ ሰዎች ከጫፍ የወጡት፣ አንተ የምትፈልገውን ስኬት የተጎናፀፉት ሰዎች እድለኞች አይደሉም፡፡ ለፊዎች ናቸው፣ የሚጥሩ፣ የሚግሩ በጣም የሚታትሩ ሰዎች ናቸው፡፡

‹‹ትልቁ የስኬት ምስጢር የማይቆም ጥረት ነው። ወዳጄ እየለፋህ ከሆነ ዛሬ ከባድ ነው፡፡ ነገ በጣም ከባድ ነው፡፡ ከነገ ወዲያ ግን ምርጥ ነው፡፡ ዛሬን ተጨነቅና ቀሪ ዘመንህን በተስፋ ኑር እለዋለሁ ራሴን›› ይለናል ታላቁ ቦክሰኛ መሐመድ ዓሊ፡፡ አንተም አሁኑኑ ልደሰት አትበል፡፡ ለገንዘብ መሥራቱን አቁመህ ገንዘብ ላንተ መሥራት እስኪጀምር ድረስ ጠንክረህ ሥራ። የዚህ ዓለም ስኬት ትንፋሹን ለረጅም ጊዜ ተቆጣጥሮ ደስታውን ለሚያዘገይ ብቻ ነው፡፡ ዘላለም እንደሚኖር ሰው ወጥረህ ሥራ፡፡ ዛሬ እንደሚሞት ሰው ደግሞ ተደሰት፡፡ ወዳጄ አንተ ብትጠነክርም ባትጠነክርም ጊዜው እንደሆነ መሄዱ አይቀረም፡፡ ጠንክረህ ሥራ!! ለራስህ ስትል ነው፤ ለማንም አይደለም፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ግንባታቸው የተጓተተ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ በትኩረት እየሠራ ያለው ዩኒቨርሲቲ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቀዳሚውና ፈር ቀዳጅ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በረጅም ዘመን አገልግሎቱ በርካታ ምሁራንን አፍርቷል፤ ለሀገርና ሕዝብ የጠቀሙ የምርምር ሥራዎችን አካሂዷል፡፡ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን ኃላፊነቶቹን በቀጣይም ለመወጣት እያካሄዳቸው ከሚገኙ ተግባሮች መካከል ለመማር ማስተማር፣ ምርምርና ለመሳሰሉት ተግባራት ወሳኝ የሆኑ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተለያዩ ካምፓሶቹ እያካሄደ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርስቲው በቅርቡ ደግሞ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እየተካሄዱ የሚገኙትንም ሆነ በቀጣይ የሚያካሂዳቸውን የግንባታ ፕሮጀክቶችንም ሆነ ሌሎች ሥራዎቹን ይሄንን ራስ ገዝነቱን የሚመጥኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለእዚህም የዲጂታላይዜሽን አቅም ማሳደግ፣ የመምህራን፣ የሠራተኞችንና የተማሪዎችን አቅም ማጎልበት ይጠበቅበታል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ሥራዎች የሚጠቅሙትን የመሠረተ ልማት አቅሞች ለመፍጠር እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

በፋይናንስ አቅሙና በአገልግሎቱም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስቀመጠውን ራዕይ እውን ለማድረግ እየሠራ ነው፡፡ ተቋሙ ስድስት ኪሎ ያለውን ዋና ግቢን ጨምሮ በርካታ ካምፓሶች ያሉት ሲሆን በአብዛኞቹ ካምፓሳቹም በርካታ የግንባታ ፕሮጀክቶችን እያካሄደ ይካሄዳል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የተቋማዊ ለውጥ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ወንድወሰን ሙሉጌታ በዩኒቨርሲቲው እየተከናወኑ ያሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎች አስመልክተው እንዳብራሩት፤ በዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው የሪፎርም ቡድን ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ በዩኒቨርስቲው 16 የሚደርሱ ከመሠረተ ልማት ጋር ተያያዥ የሆኑ ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን አብዛኞቹ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ ፕሮጀክቶቹ ትላልቅ ሕንፃዎችን ጨምሮ እስከ ምድረ ጊቢ ማስዋብ፣ የአጥር እና የአካባቢ ውበት መጠበቅን የመሳሰሉ ስፋፊ ሥራ የሚካሄድባቸው ናቸው፡፡

በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እየተገነቡ ከሚገኙት ፕሮጀክቶች መካከል የድንገተኛ ክፍል፣ የተመላላሽ ታካሚዎች፣ የተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻ ግንባታዎች የሚገኙበት መሆኑን ዶክተር ወንድወሰን ይናገራሉ፡፡ በአቡነ ጴጥሮስ ካምፓስም እንዲሁ ለጋዜጠኝነትና ተግባቦት ትምህርት ክፍል እና ለሌሎች የሥራ ክፍሎች አገልግሎት የሚውሉ እንዲሁም ከፍተኛ ገቢ የማመንጨት አቅም ያላቸው የሕንጻ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡

በዋናው ጊቢም እንዲሁ የፎረም ሕንጻ ወይም አካዳሚክ ኮምፕሌክስ የሚባል በየካቲት 12 ሰማዕታት አደባባይ በኩል እየተገነባ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚሁ ግቢ “ዎክ አፕ ዶርሚተሪ” የሚባል በርካታ ተማሪዎችን የመያዝ አቅም ያላቸው የዶርሚተሪ ፕሮጀክት እንዲሁም የአጥርና አካባቢ ማስዋብ ሥራ ፕሮጀክቶች መኖራቸውንም ነው ያብራሩት፡፡

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በአራት ኪሎ ካምፓስ እንዲሁ የጂኦፊዚክስ ወይንም ተዛማጅ ሥራዎች የሚሠራበት ሕንጻ፣ በአምስት ኪሎ ካምፓስም በተመሳሳይ የቢሮና የቤተ-ሙከራ የሕንፃ ፕሮጀክት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ጋር በተዛማጅነት ሥራ ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ በያሬድ ትምህርት ቤት የኮንሰርት ወይም “የፐርፎርሚንግ ሆል”፣ በእንጦጦ ፓርክ የአርት ጋለሪም እንዲሁ የዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቶች አሉ፡፡

አብዛኛዎቹ የፕሮጀክቱ ሥራዎች ከረጅም ዓመት በፊት ተጀምረው በተለያየ ምክንያት እክል ገጥሟቸው የቆሙ መሆናቸውን ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ግንባታቸው የተጓተተባቸው መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በዋነኝነት በእነዚህ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን አንስተውም፤ ‹‹የገንዘብ አቅምን በማጠንከር፣ ከተቋራጮች እና ከአማካሪዎች ጋር በቅርበት በመሥራትና የፕሮጀክት ክትትል በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በፍጥነት ተጠናቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ እየተሠራ ነው›› ብለዋል፡፡

**ዩኒቨርስቲው ከመማር ማስተማሩ ሥራ በተጨማሪ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በኩል የሕክምና አገልግሎት በኩል መስጠት ግዴታው መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም የድንገተኛ እንዲሁም የተመላላሽ ሕክምና መስጫ ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ በከተማ ያለውን የሕክምና አገልግሎት ችግር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚፈታ ያስረዳሉ**

ፕሮጀክቶቹ በበርካታ ተቋራጮች የሚከናወኑ መሆናቸውን ዶክተር ወንድወሰን ጠቁመው፣ አንዳንድ ተቋራጮች ሁለት ፕሮጀክቶች የያዙበት አጋጣሚ መኖሩን ይገልፃሉ፡፡ አብዛኞቹ ተቋራጮች ከአማካሪዎች ጋር በተለያየ ጊዜ ኮንትራቶች መፈረማቸውን ዶክተር ወንድወሰን አመልክተው፤ በፕሮጀክቶች የፋይናንስ አፈጻጸሞች እና በግንባታዎቹ ላይ የአፈጻጸም ልዩነቶች እንዳሉባቸው ነው ያስገነዘቡት፡፡

እንደምክትል ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ እስከ አምስት ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ርክክብ የሚደረግባቸው ፕሮጀክቶች አሉ፡፡ በዋናው ግብ የሚገኘው ዎክአፕ ዶርሚተሪና የያሬድ ትምህርት ቤት ጊቢው የኮንሰርት አዳራሽ በማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሌሎቹም ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደት ከ75 እስከ 85 በመቶ በላይ የደረሱ ሲሆን ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም ያስፈልጋል፡፡

ለማጠናቀቂያ ሥራዎች የሚያስፈልገው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ውድ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም የሚጠይቁ፣ ይሁንና ለማጠናቀቅ ጥቂት ሥራዎች የቀሯቸው በአራት ኪሎ፣ በአምስት ኪሎ፣ በጥቁር አንበሳ እንዲሁም በአቡነ ጴጥሮስ ያሉ ፕሮጀክቶች እንዳሉ ነው ያመለከቱት፡፡ አብዛኛዎቹ ለማጠናቀቂያ ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ከውጭ የሚመጡ መሆናቸውን አንስተው፤ ‹‹በተለይም የአልሙኒየም፣ የኮርኒስ መሸፈኛዎች፣ አሳንሰሮች፣ ለሰፈረ ሰላም ካምፓስ የሚሠራው ጥቅም ላይ የዋለ ፍሳሽ ውሃን ለማከም እንዲያስችል እየተገነባ ላለው ፕሮጀክት የሚያስፈልጉት የማጠናቀቂያ እቃዎች ከውጭ የሚገቡ ናቸው›› ብለዋል፡፡

በዚህ ወቅት ከሚታየው የወጭ ምንዛሪ እጥረት አኳያም ለፕሮጀክቶቹ ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታምኖበት በብሔራዊ ባንክና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

በበጀት ዓመቱ ለዩኒቨርስቲው በካፒታል በጀትነት የተመደበው ገንዘብ አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ ዩኒቨርስቲው ራስገዝ ከመሆኑ እና መሠራት የሚገባቸው የመሠረተ ልማት ሥራዎች ሰፋፊ ከመሆናቸው አንፃር የአቅም ማነስ እንዳያጋጥም ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ የፋይናንስ ችግሮቹን ለመቅረፍ እየተሞከረ ነው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ሌሎች አጋዥ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ ኤምባሲዎችን ለማስተባበርም ብዙ ሙከራዎች እየተደረጉ መሆናቸውን ነው ያስረዱት፡፡

በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶቹ ላይ ዋነኛ ተግዳሮት እየሆኑ ከመጡት ምክንያቶች አንዱ ፕሮጀክቶቹ ለረጅም ዓመታት መጓተት እንደሆነ አንስተው፤ ‹‹በኮንትራቱ የመግዣ ዋጋ እና አሁን ገበያ ላይ ባለው ዋጋ መካከል ልዩነት በመፍጠሩ በተቋራጮች በኩል ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ይቀርባሉ›› ሲሉ ይናገራሉ፡፡

በአማካሪዎች በኩል አልፎ አልፎ ፈተናዎች እንደሚገጥሙም ዶክተር ወንድወሰን ይናገራሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ሥራዎች መዘግየትና ይህን ተከትሎ የሚታዩ የዋጋ ጭማሪዎች፣ የተገኘውን ገንዘብ ሥራ ላይ ለማዋል ያለው ፈተና በሚቀጥለው እቅድ ላይ ሳይቀር አሉታዊ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ፡፡ በተቋራጮች በኩል ያለው መዘግየት እና ሥራዎችን በአግባቡ አሟልቶ ያለመላክ ችግሮች እንቅፋት መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህንም በውይይት ለመፍታት እየተሞከረ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ምክትል ፕሬዚዳንቱ እንደተናገሩት፤ እነዚህን የፋይናንስ አቅሞች በሚገባ ማንቀሳቀስ ከተቻለም ፕሮጀክቶቹ በቅርብ ጊዜ ተጠናቅቀው ወደ ሥራ መግባት እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ሕንጻዎችን ወደ ሥራ ከማስገባት አኳያም አንድ ሕንጻ ሙሉ ለሙሉ እስኪጠናቀቅ መጠበቁ ባለፈ የሕንጻውን የተወሰነ ክፍል ወደ አገልግሎት ለማስገባት እየሠራ ነው፡፡ አንድ ትልቅ የሕንጻ ፕሮጀክት አራት ወይንም አምስት አገልግሎት የሚሰጡ ግንባታዎች ሁሉም እስኪጠናቀቁ ከመጠበቅ ይልቅ የተወሰነው የሕንፃው ክፍል አገልግሎት መስጠት እንዲችል ለማድረግ በከፊል ሕንጻዎችን የመረከብ ሥራ እየተሄደበት ይገኛል፡፡

ለአብነትም በዋናው ግቢ የሚገኘውን የአካዳሚክ ኮምፕሌክስ ዘመናዊ ሕንጻን ጠቅሰው፤ ‹‹ሕንጻው የመምህራን ቢሮዎች፣ እስከ ሁለት ሺ ሰው የሚይዝ አዳራሽ፣ 18 መማሪያ ክፍሎች፣ 18 የኮምፒውተር ቤተ-ሙከራዎች እና ለቢዝነስና ለሬስቶራንት አገልግሎቶች የሚውሉ አምስት ሕንፃዎች እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡

የተወሰኑት ፕሮጀክቶች ገቢ እንዲያመነጩ የተገነቡ መሆናቸውን ዶክተር ወንድወሰን ጠቅሰው፣ ዩኒቨርስቲው ራስገዝ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ የዩኒቨርስቲውን የፋይናንስ አቅም ለማጎልበት ሕንጻዎቹ እድል እንደሚፈጥሩ ያመለክታሉ፡፡ ለእዚህም የሕንጻዎቹን ርክክብ በከፊል ለመፈጸም የሚያስችሉ ሥራዎችን እየተከናወኑ መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡

ለእዚህም ግንባታው ያለቀውንና ለመምህራን ቢሮ የሚሆነውን ለብቻው ራሱን ችሎ ያለውን የፕሮጀክቱን አካል፣ ቀጥሎም የትምህርት እና የኮምፒውተር ቤተ-ሙከራዎችን፤ ከዚያም የኮሜርሻል ክንፍ የሆነውንና ለንግድ ሊውል የሚችለውን የሕንጻ ክፍል ተራ በማውጣት በከፊል ኮሚሽኒንግ ሕንጻዎችን በመረከብ ወደ ሥራ ለማስገባት አቅጣጫ መያዙን ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ወደ ሥራ በሚገቡበት ጊዜ የመምህራን ሕንጻው ወደ አገልግሎት ይገባል፤ በቢሮዎች፣ በላቦራቶሪ እንዲሁም በመማሪያ ክፍል በኩል ያለው ችግርም ይቀርፋል በማለት ተናግረዋል፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ብዙዎቹ ፕሮጀክቶች በግንባታ ሂደት ላይ እያሉ ከተለያዩ ወገኖች በመነጩ አዳዲስ ሀሳቦች እና የዲዛይን ማስተካከያዎች ለውጦች ተደርጎባቸዋል፡፡ ለውጦቹም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ዩኒቨርሲቲው ተጠይቆ እንዲሁም በአማካሪው ተመርምሮና ፀድቆ ወደ ተቋራጩ ሄደው የተፈጸሙ ናቸው፡፡ በዚህ አይነት መልኩ በአንዳንድ የሕንፃ ፕሮጀክቶች ላይ ለውጥ ተደርጓል፡፡

‹‹አሁን ባለበት ደረጃ በተቻለ መጠን ለውጦችን ላለመጨመር ጥረት እየተደረገ ነው፤ አንዳንድ ለሕንፃው አገልግሎት የግድ ያስፈልጋሉ የሚባሉ እና ያለእነዚህ ለውጦች ሕንጻው ወደ ሥራ የማይገባ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው፣ በተቋራጩ እና በአማካሪ መሐንዲሱ በኩል ውይይት በማድረግ ሥራውን ለማስኬድ እየተሞከረ ነው›› ይላሉ፡፡ ይሁንና በተቻለ መጠን ባሉበት ሁኔታ ሕንጻዎቹን ለማጠናቀቅ ጥረት እንደሚደረግ ያስረዳሉ፡፡

ጥቁር አንበሳ ላይ ያለው ፕሮጀክት ግን ከሌሎች በተለየ መልኩ እንደሚገነባ ዶክተር ወንደሰን ይናገራሉ፡፡ ዩኒቨርስቲው ከመማር ማስተማሩ ሥራ በተጨማሪ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በኩል የሕክምና አገልግሎት በኩል መስጠት ግዴታው መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም የድንገተኛ እንዲሁም የተመላላሽ ሕክምና መስጫ ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ በከተማ ያለውን የሕክምና አገልግሎት ችግር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚፈታ ያስረዳሉ፡፡

በአቡነ ጴጥሮስ የዩኒቨርስቲው ካምፓስ ያሉትን የሕንፃ ፕሮጀክቶች በተመለከተም ሲያብራሩም ‹‹ለመማር ማስተማሩ ሥራ ከሚውሉ ግንባታዎች በዘለለ ዘመናዊ ስቱዲዮዎች፣ ለቀረፃ የሚሆኑና ለሬዲዮ ጣቢያነት የሚያገለግሉ አዳራሾች የተካተቱበት ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ከትምህርት ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ናቸው›› ይላሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ኮሜርሻል ሆነው የሚከራዩ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን ሊሰጡ የሚችሉ ሕንጻዎች መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ራስገዝ በመሆኑ ዩኒቨርስቲውን የሚመጥን ሰፋፊ እቅዶችን በማዘጋጀት ይሠራል፡፡ ከሌሎች ሀገሮች በተገኘው ልምድ መሠረት የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲ ከቢሮ፣ ከመማሪያ ክፍሎችና ከላቦራቶሪዎች በተጨማሪ፣ ስፔሻላይዝድ የሚባሉ ላቦራቶሪዎች ያስፈልጉታል፡፡ ይሄንንም በቀጣይነት እቅድ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ለመሥራት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ የፈጠራ ሀቦች፣ የስታርት አፕ ላቦራቶሪዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ዓለም አቀፍ ዩኒቨርስቲ የመሆን ራዕይ ያለው በመሆኑ የውጭ ተማሪዎችን ማሳረፍ የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ ሆስቴልም ሊኖረው ይገባል፡፡ ገቢ ማመንጫ የሚሆኑ የመሠረተ ልማት ሥራዎችም መሥራት አለባቸው፡፡

አሁን እየተከናወኑ ያሉትን መሠረተ ልማቶች ማጠናቀቅ ብቻ በቂ ነው ማለት እንዳልሆነም ዶክተር ወንድወሰን ተናግረው፤ በሂደት የሚሟሉ በርካታ መሠረተ ልማቶች እንዳሉም ነው ያስታወቁት፡፡ ‹‹ዩኒቨርሲቲው ስር ያለው ሆስፒታልም ደረጃውን የጠበቀ እና ሰፊ መሆንም ይኖርበታል፤ ሆስፒታሉንም ከመንግሥት ጥገኝነት በተወሰነ ደረጃ ማላቀቅ የሚቻለው የራሱን ገቢ ማመንጨት ሲችል ነው፡፡ የምርምር ተቋሞቹም በርካታ ፋሲሊቲዎች ያስፈልጓቸዋል›› ይላሉ፡፡ በኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ በኩል ሲታይም ከመደበኛው አገልግሎት እና ከተወሰኑ የዲጂታል ድጋፎች በዘለለ ዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች ያሏቸውን ዓይነት የዲጂታላይዜሽን አቅም የሌለው በመሆኑ ቀጣዩ የዩኒቨርሲቲው የቤት ሥራ መሆኑንም ነው ያስገነዘቡት፡፡

ኢኮኖሚ

## ስኬት

# በቴክኖሎጂ ፈጠራ ከተቀጣሪነት ወደ ኢንቨስተርነት

**ማሕሌት አብዱል**

ከዛሬ 37 ዓመት በፊት ነው በኤሌክትሪክሲቲ ሙያ ከተግባረ-ዕድ ትምህርት ቤት በከፍተኛ ውጤት የተመረቁት፡፡ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤት የሚያሸጋግር ውጤት ቢኖራቸውም፣ ቤተሰቦቿቸውን በኢኮኖሚ ማገዝ እንዳለባቸው አምነው ሥራ ፍለጋ ማሰኑ። ይሁንና የተወለዱባትና ያደጉባት አዲስ አበባ ልክ እንደዛሬው በኢንዱስትሪ አልተከበበችምና እሳቸው በተመረቁበት ሙያ ልትቀጥራቸው አልቻለችም፡፡

እኚህ ሰው የዛሬው የስኬት እንግዳችን የኢ ሜክ ኢንጅነሪንግ እና አግሮ ኢንዱስትሪ ትሬዲንግ መሥራችና ጀነራል ማናጀር ኤፍሬም ኃይሉ ናቸው። ቀያቸውና ያሳደጋቸውን ማኅበረሰብ ለቀው ለመውጣት የተገደዱት እንግዳችን፤ በወቅቱ ግንባታ ላይ ወደ ነበረውና 575 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ሚገኘው ጣና በለስ ፕሮጀክት ነበር ሥራ ፍለጋ የተጓዙት፡፡

ለቴክኖሎጂ ልዩ ፍቅር የነበራቸው የያኔው ወጣቱ ኤፍሬም ሥራ ለመልመድ ብዙ አልተቸገሩም፤ በኤሌክትሪክና ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ እጃቸውን ከማፍታት አልፈው አዳዲስና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች የመፍጠር አቅም አጎለበቱ። ለ13 ዓመታት በሙያው ድንቅ ብቃታቸውን አሳዩ። በተለይም ከቅርብ አለቃቸው ጋር በመሆን ለፕሮጀክቱም ሆነ ከዚያ ውጪ በሆኑ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶችን በማምረትና በመጠገን ለሀገራዊ ልማቱ የበኩላቸውን ጥረት አደረጉ፡፡

አንዲት የሥራ አጋጣሚ ግን የሕይወት አቅጣጫቸውን እንደቀየረችላቸው አቶ ኤፍሬም ያስታውሳሉ፡፡ «ከአለቃዬ ጋር በመሆን አዲስ አበባ የድንጋይ መፍጫ ማሽን ለመትከል በመጣንበት ወቅት የሚያግዘን ባለሙያ ብንፈልግም ሙያውን የሚያውቅ አንድም ሠራተኛ ማግኘት አልቻልንም፤ በመሆኑም ለዚህ ችግር እኔው ራሴ የመፍትሔ አካል መሆን እንዳለብኝ አመንኩኝ፤ ያለውን ክፍተት በመጠቀም የራሴን ድርጅት ለመክፈት ወሰንኩኝ» ይላሉ፡፡ ይህንን ውሳኔያቸውን የሰሙ አለቆቻቸውና ጓደኞቻቸው ሃሳባቸውን ደገፉላቸው፡፡

ከሦስት የቤተሰብ አባላት ጋር በመሆን በአምስት ሺ ብር ሥራውን መጀመራቸውን የሚናገሩት አቶ ኤፍሬም፣ ለስድስት ወራት ያህል ያለምንም ገቢ መሥራታቸውን ያስታውሳሉ፡፡ ይሁንና ትልቅ የመንፈስ ጥንካሬና ራዕይ በመሰነቅ በመነሳታቸው ለፈተናዎች ሳይበገሩ አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ማሽኖችን ለመሥራት ተጉ፡፡ «ያን ጊዜ በዘርፉ ያለውን ክፍተት በማየት በድፍረት በመግባቴ እንደሃገር የነበሩ ችግሮችን ለማስተካከል የበኩሌን ተወጥቻለሁ፤ በዚህም ደስተኛ ነኝ» ይላሉ፡፡ ለዚህም አብነት አድርገው «ኢንዱስትሪው በሚፈልገው ደረጃ ባለሙያ ባለመኖሩ ብዙ ሥራዎች በእጅና ኋላቀር በሆነ መንገድ ነው የሚከናወነው ይከናወኑ የነበሩት። ሌላው ይቅርና እንደሥጋ መፍጫ ያሉ የማዕድ ቤት የኢንዱስትሪ እቃዎችን የሚጠግኑ ባለሙያዎች እጥረት ነበር፡፡ በዚህም እስከ ትላልቅ ሆቴሎች ድረስ የሚቸገሩበት ሁኔታ ነበር» በማለት ይጠቅሳሉ፡፡

ከዚህ በመነሳትም የሰው ኃይሉን ከማሠልጠን ጀምሮ የጥገና እና የተለያዩ የውሃና ኤሌክትሪክ ቴክኖሎጂዎች፤ እንዲሁም የመኖ ማቀነባበሪያ የመሳሰሉ የአግሮ ኢንዱስትሪ ማሽኖችን በማምረት ወደ ገበያው መግባታቸውን ያመለክታሉ፡፡ «ሰብ ኮንትራቶችን በመያዝ የውሃ ልማት፤ ኤሌክትሪክ፤ አግሮ ኢንዱስትሪ፤ የእንስሳት ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ማሽኖችን በማምረት በተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች አቅርበናል» በማለት ያስረዳሉ፡፡

በዋናነትም ኢትዮጵያ በቀንድ ሃብቷ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ መሪ ሆና ሳለ ከዘርፉ ተጠቃሚ አለመሆኗ የሁልጊዜ ቁጭታቸው ስለነበር ምርታማነታቸው የተረጋገጠ ቴክኖሎጂዎችን እንደሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እሴት በመጨመር በድርጅታቸው በስፋት ወደማምረት መግባታቸውን ነው የሚያብራሩት፡፡

«ኢትዮጵያ በቀንድ ሃብቷ ተጠቃሚ ያልሆነችበት አንዱ ምክንያት የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን እጥረት በመኖሩ ነው፤ እኛም ሥራ በጀመርንበት ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የነበሩት ማሽኖች ከ20 አይበልጡም ነበር» የሚሉት ጀነራል ማናጀሩ፤ ድርጅታቸው በዚህ ዘርፍ ላይ በቂ እውቀት ያለው በመሆኑ 30 በመቶ ማሽን የማምረት ሥራ፤ 70 በመቶ ደግሞ የማሽን ጥገና ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት መቀጠሉን ነው ያብራሩት፡፡ በተጓዳኝም ሌሎች ማሽኖችን የማምረት፤ የሠለጠነ የሰው ኃይሉንም የማበራከት፤ አዳዲስና ምርታማነታቸው የተረጋገጡ ማሽኖችን እየሠራ ለገበያው ማቅረብ መቀጠሉን ያነሳሉ፡፡



አቶ ኤፍሬም ኃይሉ

እንደ አቶ ኤፍሬም ማብራሪያ፤ ድርጅታቸው የሚያመርታቸው ማሽኖች በገበያው ተቀባይነት እያገኙ ሲመጡ በተለይም የመንግሥትና የተራድዖ ድርጅቶች በስፋት እንዲያመርቱ ግፊት ያድርጉባቸው ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት አዳዲስና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የዶሮና የከብት መኖ ማሽኖችን ለመሥራት ሰፊ ጥናት አድርገዋል፡፡ እስካሁንም ከ700 የሚልቁ ማሽኖችን በማምረት ለዘርፉ ያበረከቱ ሲሆን 11 የሚሆኑትን ለአዕምሯዊ ንብረት አስመዝግበው ለአራቱ እውቅና (ፓተንት) ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም 70 ዓይነት የተመጣጠነ የዶሮ መኖ ማዘጋጀት የሚችሉ ማሽኖችን ለተጠቃሚዎች አድርሰዋል፡፡

ድርጅታቸው በመላው ሃገሪቱ በሚከናወኑ ትላልቅ ልማቶች ላይ የመሳተፍ እድሉን ማግኘቱን ጠቁመውም «የአሜሪካ ኤምባሲ ግንባታ ሲከናወን ኤሌክትሮ መካኒካል ሥራውን ኮንትራት ወስደን ሠርተናል፤ ካጅማ ደጀን ላይ ሲሠራ የሲሚንቶ ማደባለቂያ ማሽኑን የሠራነው እኛ ነን፡፡ ደብረማርቆስ ውሃ ልማት ሥራ ላይ ሰፊ ተሳትፎ ነበረን» ሲሉ ያብራራሉ፡፡ አሁን ላይ ድርጅቱ ማሽኖችን ጥገና የማድረግ አቅሙ በከፍተኛ መጠን መጎልበቱን ጠቅሰው፣ ይህም በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት እንዳስቻለ ይናገራሉ። በተጨማሪም ነፃ የማማከር አገልግሎት በመስጠት ለዘርፉ እድገት ሚናውን እየተወጣ ነው ይላሉ፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜም ድርጅታቸው የሚያመርታቸው ማሽኖች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን እንዲጠብቁ በማድረግም በርካታ ሥራ መሥራቱን አመልክተው፤ በተለይም ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ መለያ(ብራንድ) ይዛ እንድትቀርብ የተሠራው ሥራ ውጤታማ የሚባል እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ «ባለፉት ሦስት ዓመታት ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለአፍሪካ ገበያም አቅርበናል፡፡ ይሁንና በገበያው ፍላጎት ቢኖርም የፋይንስ ውስንነት ስለነበረብን በስፋት አምርተን ማቅረብ አልቻልንም» ይላሉ፡፡ በዚህ ተስፋ ሳይቆርጡ ሌሎች አጋዥ ድርጅቶችን እያፈላለጉ መሆኑንም አጫውተውናል፡፡

እንደ ጀነራል ማናጀሩ ማብራሪያ፤ ድርጅቱ እስካሁን ባለው ጊዜ ከ300 እስከ 400 የሚሆኑ ባለሙያዎችን አፍርቶ ለኢንዱስትሪው ያስረከበ ሲሆን ለ40 ዜጎች ደግሞ ቋሚ የሆነ የሥራ እድል ፈጥሯል፡፡ ካፒታሉንም ከአምስት ሺ ተነስቶ ወደ 200 ሚሊዮን ብር አሳድጓል። በቅርቡም ድርጅታቸውን ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪነት ለማሳደግ የሚያስችለውንና ቦሌ ለሚ ላይ የሚገኝ 10 ሺ ካሬ መሬት ለመረከብ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

«አሁንም ኢንዱስትሪ የሚፈልገውን ባለሙያ፣ የመለዋወጫ ዕቃና ቴክኖሎጂ በጥናት ላይ ተንተርሰን በስፋት ለማምረት እየሠራን ነው፤ ኢንዱስትሪው የሚጠይቀውን የትኛውንም ጥያቄ ሃገራችን ውስጥ ባለ ግብዓት መፍትሔ እየሰጠንም ነው» ይላሉ። እስካሁንም ከአጠቃላይ አቅማችን 20 በመቶውን ብቻ ሠርተናል ብለው እንደሚያምኑ የሚናገሩት አቶ ኤፍሬም፤ «በቀጣይ የአቅማችንን 80 በመቶ ለማምረት በተለይ ቦታ፤ የፋይናንስ አቅርቦት የምናገኝ ከሆነ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ክልሎች ላይ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመት ውስጥ ከአንድ ሺ በላይ ሠራተኞችን ቀጥረን ለማሠራት ራዕይ አለን» ሲሉ አብራርተዋል፡፡ በቅርቡ ቦሌ ለሚ ላይ ሥራ ሲጀምር ደግሞ 20 በመቶውን ምርት ለወጭ ገበያ ለማቅረብ ድርጅቱ ማቀዱን ነው የጠቆሙት፡፡

በተጨማሪም ራሳቸው ያመረቷቸውን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በግብርና ሥራ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን የተናገሩት ጀነራል ማናጀሩ፤ የተለያዩ አዝርዕቶችን በስፋት በማምረትና ከብትና የዶሮ እርባታ ላይ በመሰማራት የሃገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ሥራ ላይ አወንታዊ ሚና ለመጫወት ተግተው እየሠሩ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

ድርጅታቸው መኖ ማቀነባበሪያ ማሽን ላይ በማተኮሩና ዘርፉ ሰፊ የእሴት ሰንሰለት በመኖሩ ተጨማሪ የሥራ እድል እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ «እኛ የምናመርተው አንድ ማሽን ቢያንስ ከ15 እስከ 20 ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ እድል ይፈጥራል» ይላሉ፡፡ ከዚህ ባሻገርም መኖ ልክ እንደ ነዳጅ በየጊዜውና አካባቢው ዋጋው እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ በየአካባቢው የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን ሲተከል የአካባቢውን ኅብረተሰብ ብቻ ሳይሆን ሃገርንም ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ድርጅታቸው ነባርና በዘርፉ መሥራች ኩባንያ እንደመሆኑ በሀገር ደረጃ ያሉ የኢንዱስትሪ ነክ ችግሮችን ለመፍታት በኃላፊነት ይሠራል፡፡ ይህም መንግሥትም ሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እምነት በማሳደር ትልልቅ ሥራዎችን እንዲሰጧቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ ድርጅቱ የሚያመርተው ምርት በየጊዜው የጥራት ደረጃ የሚለካ ሲሆን ይህንንም እንደመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል ካሉ ድርጅቶች ጋር በቅርበት እየሠራ ይገኛል። በተለይም ከምርምር ማዕከላት ጋር አብሮ የመሥራት ባሕሉን በማጠናከር በጤፍና በሌሎች ሃገር በቀል ምርቶችን ምርታማነት የሚያሳድግ ቴክሎጂዎችን ለማምረት እቅድ ይዟል፡፡

ቀደም ባሉት ግዜያት ኢትዮጵያ ያላትን የሰለጠነ የሰው ኃይል በአግባቡ የምትጠቀም ሃገር ያለመሆንዋ ትልቅ ቁጭት እንደሚያሳድርባቸው አቶ ኤፍሬም ያስታውሳሉ፡፡ «ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በእርሻ መሣሪያዎች ላይ ብዙ የሚሠሩ ባለሙያዎች ነበሩ። ነገር ግን አዲስ አበባ ውስጥ የሚቀጥራቸው ድርጅት በማጣታቸው አብዛኛዎቹ ባለሙያዎች ወደ ሹፍርና ገብተዋል፡፡ በተለይም በኢንዱስትሪ ዘርፉ ብዙ ሃብት ፈሶበት የሠለጠነው ይህ ኃይል ሰው ሃብቱን የሚሰበስብ የለም» በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችላት ልማት ላይ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

የፋይናንስ እጥረትና ባንኮች ለዘርፉ ተዋናዮች ድጋፍ የማድረግ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆንም ኢንዱስትሪው እንዳያድግ ሌላው ማነቆ እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ «በየከተማው ቁጭ ብለው 'አተረፍን' የሚሉ ባንኮች የፈጠራና ምርምር ሥራ ለሚሠሩ አካላት ማበደር አይፈልጉም፡፡ በዚህ ምክንያት ዘርፉ ማደግ አልቻለም። ሰው ከከተማ ወጥቶ እርሻ መሥራት ካልቻለ፤ ገበሬው ቴክኖሎጂ መጠቀም ካልቻለ እድገታችን ወደ ኋላ የሚሆነው» ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

ከአቢሲኒያ በኳሊቲ አዋርድ እንዲሁም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እውቅና እና ሽልማት ያገኙት አቶ ኤፍሬም፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘርፉ እንዲያድግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ያሳስባሉ። በተለይም የፋይናንስ ተቋማቱ አዳዲስ የፈጠራ ውጤት ይዘው ያለሥራ የተቀመጡ ባለሙያዎችንና ኢንዱስትሪያቸውን የማስፋፋቱ ፍላጎቱ ኖሯቸው በፋይናንስ እየጥረት የተገደቡ ድርጅቶችን እንዲደግፉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ስፖርት



## የአፍሪካ ዋንጫ ዛሬ በኮትዲቯር ይጀመራል

ብርሃን ፈይሳ

ኮትዲቯር ከ40 ዓመታት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የምታሰናዳው የአፍሪካ ታላቁ የእግር ኳስ ውድድር 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ዛሬ ይጀመራል። በደቡባዊቷ የሀገሪቷ ክፍል በሚገኘው አቢጃን ከተማ ላይ የተገነባው አዲሱ አላሳኔ ኦታራስታ ስታዲየም ደግሞ በመርሃ ግብሩ መሠረት የመክፈቻውን ጨዋታ በአዘጋጇ ኮትዲቯር እና ጊኒ ቢሳው መካከል ያስተናግዳል። ከሰሞኑ በባህላዊ አልባሳት ደምቀው ወደ ሀገሪቷ ሲያቀኑ የቆዩት የተለያዩ ሀገራት ብሄራዊ ቡድኖች ተጠቃለው የገቡ ሲሆን፤ የዋንጫ ፍልሚያቸውንም ከዛሬ አንስቶ ያከናውናሉ። በአምስቱ ከተሞቿ የሚገኙት ስድስት ስታዲየሞቿም 24ቱ ቡድኖች የሚያደርጓቸውን 52 ጨዋታዎች እየተጠባበቁ ይገኛሉ።

የዓለም እግር ኳስ አፍቃሪያን ዓይን ከዛሬ አንስቶ ወደ አፍሪካ የሚያማትር ሲሆን፤ ለወትሮ ሞቅ ደመቅ ብለው ይካሄዱ የነበሩት የአውሮፓ ሊጎችም ተቀዛቅዘው የአሠልጣኞቻቸውና አስተዳደሮቻቸው ትኩረት በአፍሪካውያን ወጣቶች ላይ ሊሆን ይገደዳል። የቀድሞ ቼልሲ እና ማንችስተር ሲቲ ተጫዋቾች የነበሩትን ዲድየር ድሮግባ እና ቱሬን ጨምሮ በርካታ የእግር ኳስ ከዋክብትን ያፈለቀችው ምዕራባዊቷ ሀገር በዚህ የውድድር መድረክ




ተሳትፎዋ ሁለት ዋንጫዎችን ስታነሳ፤ ሁለት ጊዜ ለፍጻሜ ደርሳ ተሸንፋለች። ለአራት ጊዜያት ደግሞ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ፈጽማለች። በአህጉረ አፍሪካ ጠንካራ ከሚባሉ ብሄራዊ ቡድኖች የሚመደበው ኮትዲቯር ባለፈው ወር የፊፋ ሀገራት ደረጃ መሠረት ከአፍሪካ 7ኛ ደረጃን ሲይዝ ከዓለም ደግሞ 49ኛ ላይ ነው የተቀመጠው።

በሀገሪቷ በነበረው ዝናባማ የአየር ሁኔታ ወራትን በማራዘም አሁን ላይ በሚካሄደው በዚህ ውድድር ላይም ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ የስፖርቱ ቤተሰቦች ይታደማሉ በሚል ይጠበቃል። ለዚህ ውድድር ሲባል አራቱ ስታዲየሞች አዲስ የተገነቡ ሲሆን፣ ሁለቱ ደግሞ እድሳት የተደረገላቸው ናቸው። ለዚህ ዝግጅት ሀገሪቷ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጪ በማድረግ ከስታዲየም ግንባታ ባለፈ ለመንገዶች፣ ሆስፒታሎች፣ ለአየር ማረፊያዎች እንዲሁም ሌሎች መሠረተ ልማት ግንባታ እና እድሳት ማዋሏንም የኮትቯር እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እድሪስ ዲያሎ ይገልጻሉ። ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ለዘለቀችው ሀገሪቷ የአፍሪካ ዋንጫውና እሱን ተከትሎ በተደረገው የመሠረተ ልማት ግንባታም አዲስ ምዕራፍን ይከፍታል በሚል ተስፋ የሰነቁም በርካቶች ናቸው።

ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ 24 ሀገራትን ወደ ማሳተፍ የተሸጋገረው የአፍሪካ ዋንጫ፤ ቡድኖቹን በ6 ምድብ ከፍሎ ያፎካክራል። በዚህም በኳታሩ ዓለም ዋንጫ ያልተጠበቀ አቋም በማሳየት የእግር ኳስ ቤተሰቡን ያስደመመችው ሞሮኮ፤ በተመሳሳይ የዚህ ውድድር ክስተት በመሆን ዋንጫውን ልታነሳ እንደምትችል የበርካቶች ግምት ሆኗል። የአፍሪካ ዋንጫን ሰባት ጊዜ የግሏ በማድረግ ቀዳሚ የሆነችው የፈርኦኖቹ ሀገር ግብጽም ለዋንጫ ቅድመ ግምት ያገኘች ሀገር ስትሆን፤ እአአ የ2021ዱን የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊዋ ሴኔጋል፣ ካሜሮን፣ ናይጄሪያ፣ ጋና እና ኮትዲቯርም ለዋንጫው ተጠባቂ ቡድኖች ናቸው። ይህንን የአፍሪካ ዋንጫ ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል አንዱ የሽልማት ገንዘቡ መጠን ማደጉ ሲሆን፤ አሸናፊ በመሆን ዋንጫውን የሚያነሳው ቡድን 7 ሚሊዮን ዶላር የሚያገኝ ይሆናል። ይኸውም ከቀድሞው በ40 ከመቶ ብልጫ ያለው ነው።

በምድብ ድልድሉ መሠረት የመጀመሪያው ምድብ የውድድሩን አዘጋጅ ሀገር ኮትዲቯርን ጨምሮ ናይጄሪያ፣ ኢኳቶሪያል ጊኒ እና ጊኒ ቢሳው ተካተውበታል። ምድብ ሁለት ግብጽ፣ ጋና፣ ኬፕቨርዴ እና ሞዛምቢክን ያቀፈ ሲሆን፤ በምድብ ሶስት ስር ደግሞ ሴኔጋል፣ ካሜሮን፣ ጊኒ እና ጋምቢያ ይገኛሉ። ቀጣዩ ምድብ አልጄሪያን ከቡርኪና ፋሶ፣ ሞሪታኒያ እና አንጎላ ጋር ያገናኛል። ቱኒዚያ በምትገኝበት ምድብ ደግሞ ማሊ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ናሚቢያ ተደልድለዋል። በመጨረሻው ምድብ ደግሞ ሞሮኮ፣ ዴሞክራቲክ ኮንጎ፣ ዛምቢያ እና ታንዛኒያ ይገኛሉ። በየምድቡ በሚኖራቸው ነጥብ መሠረት ሁለቱ ምርጥ ቡድኖች በቀጥታ ወደ ቀጣዩ ዙር የሚያልፉ ሲሆን፤ አራቱ ምርጥ ሶስተኛ ቡድኖችም 16ቱን የሚቀላቀሉ ይሆናል።

ከዛሬ አንስቶ እስከ የካቲት 3/2016ዓም የሚቆየው ውድድሩ ከ32ቱ ሀገራት ተውጣጥተው ጨዋታዎቹን የሚመሩ 68 ዳኞች ተዘጋጅተዋል። በውድድሩ ተሳታፊ የማትሆነው ኢትዮጵያ ደግሞ በኢንተርናሽናል ዳኛ ባምላክ ተሰማ በብቸኝነት ትወከላለች።


## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ይድነቃቸው ሀይሉ የተሽከርካሪ ዓይነት ባስ የሠሌዳ ቁጥር 3-84298 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር JTFB518751014018 የሞተር ቁጥር LHZ-0498113 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብን ብለው በቀን 26/04/2016 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡
በዚሁ መሠረት ይህን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የመልካ ኖኖ ክ/ከተማ ትራ/ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም መሐመድ ጀማል ያሲን የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-44126 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር XLERA4X2A04351764 ሞዴል 113m የሞተር ቁጥር 4105340 የሊብሬ ቁጥር 0241594 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ26/4/2016 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሚ/ር ጀምስ ነፍታሊ ብዊራኒ የሠሌዳ ቁጥር የተመ-01-1796* የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር 2T3ZFREV2DW012196 ሞዴል ASA42L-ANTKA የሞተር ቁጥር 2ARM345045 የሊብሬ ቁጥር 0226940 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ30/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከሣሽ አፄ ቴዎድሮስ የመጀ/ደ/ት/ቤት እና በተከሣሽ ካሮት ት/ኃ/የተ/የግ/ማኅበር የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመስጠት ልናገኛቸው ስላልቻልን ተከሣሽ ካሮት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ08/05/2016 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ እነ አቃ/ቃ/ክ/ከ/ጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ እና በተከሣሽ ብርሃኔ መልካሙና አብርሃም ፊኒሺንግ ሽርክና ማኅበር የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመስጠት ልናገኛቸው ስላልቻልን ተከሣሽ ብርሃኔ መልካሙና አብርሃም ፊኒሺንግ ሽርክና ማኅበር ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ08/05/2016 ዓ.ም. በ4፡15 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት**

በከሣሽ 1ኛ ወ/ሮ ቅድስት ምትኩ እና በተከሳሽ አቶ ብሩክ የማነ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ አውቀው መልስዎን በጽሑፍ ለ16/05/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

### Corrigendum

In a bid notice publicized by ORDA Ethiopia advertised on Addis Zemen Newspaper dated Tahisas 27, 2016 E.C Page 26 the list of materials to be purchased were erroneously missed. This is, therefore, to inform esteemed potential bidders to read it as, lot one office supplies and lot two different electric materials.

**ማስታወቂያ**

“ማለዳ ለ-ኢትዮጵያ” የተባለ ቦርድ መር ድርጅት ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መስሪያ ቤት የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 406 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**